ምዕራፍ አሥራ አራት።

የአብ ቃልና እስትንፋስ የተባሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ቀላይ ወይም ባሕር፥ ስለመባላቸው።

እግዚአብሔር አብ እንደምን ባለ ሁናቴ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ከራሱ እንደሚያወጣቸው፤ ወይም ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደምን ባለው ሁናቴ ከአብ እንደወጡ፥ አወጣጣቸውን የሚያሳይ መግለጫ የባሕር ወይም የውኃ ምሳሌ ነው። ይህንም ምሳሌ የቤተ ክርስቲያን አበው ተጠቅመውበት እናገኛለን።

የዚህ ምሥጢራዊ ምሳሌ መንሥኤ፦ «ወአሠርከኒ ውስተ ማይ ብዙኅ፦ ፍለጋህ በውኃ ላይ ነው» ከሚል ከዳዊት መዝሙር አብነቱ ተመሥርቶአል። መዝ. 76/77/፥19።

በኩነታት የሚገለጸውን ተድኅሮና ቅድምና ሳይኖር /ቅደም ተከተል የሌለበትን የሥሉስ ቅዱስ አወጣጥ ምክንያታዊ ማስረጃ አድርገው በብሔራውያን ሊቃውንቶቻችን ከዚህ ምሥጢራዊ ምሳሌ መጠቀማቸው የሚዘነጋ አይደለም። መዝ. 76/77/፥19። በመጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት ውኃ ምንጭ ነኝ ሲል ራሱ እግዚአብሔር ተናግሮአል።

ለምሳሌ፦ «በነቢዩ በኤርምያስ ነቅዐ ማየ ሕይወት የሕይወት ውኃ ምንጭ» ተብሎአል። ኤር. 2፥13። ም. 17፥13። እግዚአብሔር ወልድ «የሕይወት ውኃ ምንጭ» ይባላል። ዮሐ. 4፥12። ም. 6፥35።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ «የሕይወት ውኃ ምንጭ» ተብሎአል። ዮሐ. 7፥38፤ 39።

ይኸውና፦ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በውኃ መመሰላቸውን ከውኃም ውኃ፥ የሕይወት ውኃ ምንጭ በመሆን መገለጻቸውን ከእግዚአብሔር ቃል ለመረዳት ተቻለ።

እንግዲህ በተጠቀሱት በቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ልዑለ ባሕርይ የሆነ ሥሉስ ቅዱስ የራሱ የሕይወት የውኃ ምንጭ አድርጎ ለእኛ ማስታወቁን አየን።

ይህን ካየን ወዲያ፦ ከቤተ ክርስቲያን መምህራን አንዱ ዐረጋዊ መንፈሳዊ በቀላይ ወይም በባሕር፥ በውኃ ኩነታት፥ የተከሥቶ ህልውና አቋም በሚታይ ምሳሌ የህልውና አንድነትና የጊዜ ቅደም ተከተል የሌለበት ልዑለ ባሕርይ የሆነ የሥሉስ ቅዱስ የተከሥቶ ህልውናን ለማስረዳት ማስቻሉን ሲገልጽ፦

«ነጽርኬ በእንተ አበ ኩሉ ከመ መሰልዎ በዛቲ ባሕር እንተ ትገሥሥ። ለወልድኒ ዘይሰገድ እምኀበ ኩሉ ከመ መሰልዎ በርጥበተ ማይ። ወለመንፈስ ቅዱስኒ ዘይሴባሕ እምኀበ ኩሉ መሰልዎ በሁከተ ማይ ዘውስተ ባሕር። ለመኑ ይትከሀሉ ከመ ይፍልጥ ኃይለ ባሕር እምጠባይዑ። የትከሀልኑ ከመ የሀሉ ባሕር እንበለ ርጥበት ወእንበለ ትህውኩ። ወለመኑ ይትከሀሉ ይፍልጥ ሁከተ ባሕር ወያቅማ በባሕቲታ። ወለማይኒ ወለርጥበትኒ በበባሕቲቶሙ። አው መኑ ዘርእየ አሐደ እምኔሆሙ እንዘይቀውም በባሕቲቱ ዘእንበለ በትሥልስቱ። እስመ አሐዱ እሙንቱ እንዘ ሠለስቱ። ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ ይትበሀሉ። ወሶበ ይትኔጸር ወይትሔለይ በሠለስቱ አካላት፥ ይትሔለይ ይትሔለይ ምስለ ኃይላቲሁ ወኢይትሔለዩ ኃይላቲሁ እመ ጠባይዑ፥ ወኢጠባይዑ እምኃይላቲሁ። መከመዝ እሔሊ በእንተ ጠባይዐት ስቡሐት።

የሁሉ አባት የሆነ አብን በምትዳሰስ በዚህች ባሕር እንደመሰሉት፤ በሁሉ ዘንድ የሚሰገድለት ወልድንም በውኃ ርጥበት እንደመሰሉት፤ በሁሉ ዘንድ የሚመሰገን መንፈስ ቅዱስንም በባሕር ባለው በውኃ ሁከት እንደመሰሉት ተመልከት።

የባሕርን ኃይል ከጠባዩ ለመለየት ለማን ይቻለዋል? ባሕር ያለ ርጥበትና ያለ መታወክ ሊኖር ይቻለዋልን? የባሕርንስ ሁከት ለይቶ ለብቻዋ ማቆም ለማን ይቻለዋል? ውኃንና ርጥበትንስ ለየብቻዋ ማቆም ለማን ይቻለዋል? ስፍሐትንና ርጥበትንስ ከውኃ አንዱን ለብቻው ቆሞ ያየው ማነው? ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸውና፤ አንድም ሲሆኑ ሦስት ይባላሉና። በሦስት ሲታይና ሲታሰብ ከኃይላቶቹ ጋር ይታሰባል። ኃይላቶቹም ከጠባይዑ፥ ጠባይዑም ከኃይላቶቹ አይለዩም። /ኃይሉን የሚገልጥባቸው ርጥበትና ሁከት ከስፍሐቱ አይለዩም። ስለተመሰገኑ ጠባይዐትም እንደዚሁ አስባለሁ።» ብሎአል። /ዐረጋዊ መንፈሳዊ ገጽ 216 ም ድርሳን 36።

እነሆም ከዚህ በላይ በተነገረው ገለጻ በሥሉስ ቅዱስ ቅደም ተከተል የሌለ መሆኑን፤ በህልውናቸውም መለየት /መለያየት/ የሌለባቸው መሆኑን ለመረዳት የሚያስችል ሐተታ አየን።

ምዕራፍ አሥራ አምስት።

የአብ ቃልና የአብ እስትንፋስ አወጣጥ በእሳት ምሳሌ ስለ መገለጹ።

ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ያለ ቅደም ተከተል ወጡ ሲባል፤ አወጣጣቸው እንዴት እንደሆነ ለማሳየት ከሚረዱ ምሳሌዎች መካከል «የእሳት ምሳሌ» አንዱ ነው።

ይህም «እስመ አምላክነ እሳት በላዒ፤ አምላካችን የምታቃጥል እሳት ነውና» ዘዳግ. 4፥20። ዕብ. 12፥19። ኢሳ. 3፥14። ሚልክ. 3፥2። ወአርአያ ሣርሁ ለእግዚአብሔር ከመ ነደ እሳት። የእግዚአብሔር የክብሩ መልክ /መታየት/ እንደሚነድ እሳት ነበረ። ዘጸአ. 24፥17። ዘፍጥ. 15፥17፤ 18።

በዚሁ አብነት ብሔራውያን መምህራን የሥሉስ ቅዱስ ልዑለ ባሕርይ ህልውናን ለማስረዳት መጠቀማቸውን፥ መገንዘብ ይገባል።

በመሠረቱም አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ እሳት መባላቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦ ይገኛል።

ሀ፥ አብ እሳት ስለመባሉ፦ ዕብ. 12፥19።

ለ፥ ወልድ እሳት ስለ መባሉ፦ ሚልክ. 3፥2፤3። ራዕ. 1፥14።

ሐ፥ መንፈስ ቅዱስ እሳት ስለ መባሉ፦ የሐዋ. 2፥3-4። እነዚህን ተመልከት።

እንዲህም በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ፦ «አብ እሳት፥ ወልድ እሳት፥ መንፈስ ቅዱስ እሳት አሐዱ ውእቱ እሳተ ሕይወት ዘእምአርያም፦ አብ እሳት ነው። ወልድም እሳት ነው። መንፈስ ቅዱስም እሳት ነው። አርያማዊ የሚሆን የሕይወት እሳት አንድ ነው።» ተብሎ ተነግሮአል። /ቅዳሴ ዘአባ ሕርያቆስ/ ገጽ 78፤ ቍጥር 94።

ይህም ዕሪናቸውንና /እኩልነታቸውን / በአንድ ጠባይዕና ራዕይ መመሰላቸውን ጕላ አድርጎ የሚያሳይ ትምህርት ነው።

ከዚህ በላይ የተገጸው ትምህርታዊ ማስረጃ በተገለጸበት አቋም ይጸናል።

በእሳት ምሳሌ የተከሥቶ ህልውና አቋም ሲገለጽ።

አሁን በዚሁ በእሳት ምሳሌያዊ አቋም፥ የተከሥቶ ህልውናን ትምህርት እንዴት እንደሚገለጽበት እንይ፦

የተከሥቶ ህልውናን ትምህርት በምንወስድበት ጊዜ፣ ጸአትንና /መውጣትን/ አለመለየትን ወይም ጸአትንና /መውጣትንና/ ያለ ተድኅሮ መሆንን የተመለከትን እንደሆነ፣ እሳት አንድ አካል ሲሆን፣ ሦስት ከዊን እንዳለው እናስተውላለን። ሦስት ከዊን የተባለውም፦ ነበልባል፥ ብርሃን፥ /ብልጭታ/ ዋዕይ፥ /ግለት/፥ነው።

በነበልባሉ አብ፥ በብረሃኑ፥ /በብልጭታው/ ወልድ፥ በዋዕዩ፥ ወይም በትኩሳቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ። መኃ. 8፥6። ያዕ. 1፥11። መዝ. 17/18/፥8።

ይኽውም ተከፍሎ ወይም መለየት ሳይኖርበት በአንድ ህልውና የሚኖር ነው። ይህን ከቤተ ክርስቲያን አበው ለመረዳት የተፈለገ እንደሆነ፣ «አቡየ እሳት፥ ወብርሃኑ አነ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ዋዕዩ፥ አባቴ እሳት ነው እኔም ብርሃኑ ነኝ፤ መንፈስ ቅዱስም ዋዕዩ ሙቀቱ ነው።» ሲል ጌታ ተናግሮአል በማለት ቀሌምንጦስ ጽፎታል። መጽሐፈ ሲኖዶስ

አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ እሳት ወነበልባል ወፍሕም። አባቴና እኔ መንፈስ ቅዱስም እሳትና ነበልባል፥ ፍህም ነን» ብለዋል፦ ቀሌምንጦስ ም. 1።

ዐረጋዊ መንፈሳዊ ገጽ 216 ቍጥር 36።

በራዕየ ሲናዳም፦ «ቅዱስ ሥሉስ አምላክነ ዋሕድ በትሥልስቱ ሥሉስ በተዋሕዶቱ። ለእመ ኀሠሥኮ ትረክቦ በኀበ ወልድ ወለእመ ኀሠሥኮ ለፍሕም ትረክቦ በኀበነድ ወእምነ ክልዔሆን ኢይትፈለጥ ዋዕይ። ከማሁ መንፈስ ቅዱስኒ ህልው በአብ ወወልድ። ከመዝ ምሥጢረ እምነትነ በመለኮት፦

ቅዱስ ሥሉስ አምላካችን አንድ ነው። በአንድነቱ ተዋሕዶ ሳለ፤ በሦስትነቱ ሥሉስ ነው። ብትፈልገው በወልድ ታገኘዋለህ። ፍሕምን ብትፈልገው ከነድ ታገኘዋለህ፤ ከሁለቱ ዘንድ ዋዕይ /ግለት/ አይለይምና። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ ህልው ሆኖ ይኖራል። ስለ መለኮት የሚኖረን የሃይማኖት ምሥጢር እንደዚሁ ነው። /ራዕየ ሲኖዳ/ ገጽ 1 ክፍል 1 ተብሎአል።

እስከዚህ ድረስ የነገረ ነፍስ ኩነታት፥ በብርሃንና በፀሐይ ኩነታት፥ እንዲሁም በቀላይና በእሳት ኩነታት፥ የጊዜ ቅደም ተከተል የሌለና የማይኖር መሆኑን በሚያሳይ ሁናቴ፥ ጸአት /አወጣጥ/ በጸአትነት መኖሩ ሳይቀር፤ ቅድምና ተድኅሮ /ቅደም ተከተል/ ወይም መለየት የሌለበትን የሥሉስ ቅዱስ ህልውናንና አንድነትን ለማየት ቻልን።

የእነዚህም ቅደም ተከተል ልዩነት የሌለበትን የልደትና የጸአት መታወቂያ ምሳሌዎች አቅርበን በምናስረዳበት ጊዜ፤ ከገዛ ራሳችን አዲስ አሳብ አፍልቀን አለመናገራችን እንዲታወቅልን ያስፈልጋል።

ምሳሌዎቹ ከኢትዮጵያውያን አበው ሊቃውንት አተረጓጐምና ጽሑፎች ለዚህ ትምህርት ማስረጃ እየሆኑ ሲቀርቡ እንደነበሩ የታወቀ ነው። ለምሳሌ ያህል ምዕላድ ከተባለ መጽሐፍ የሰፈረውን በግዕዙ እንዳለ ለማየት እንደሚከተለው አቅርበናል።

«እመቦ ዘይብል በምንት ይትዐወቁ ልደት ወጸአት እንበለ ተድኅሮ ንብሎ በቃልነ ወበእስትንፋስነ ዘይወፅኡ እምልብነ እስመ ኢይቀድሞሙ ልብ፥ ዘያወፅአሙ፤ ወኢይዴኅሩ ቃል ወእስትንፋስ ዘይወፅኡ እምኔሁ። ወዳዕሙ አሐደ ጊዜ ይትፈጠሩ።

ወካዕበ ይትዐወቅ በፀሐይ እስመ ቦቱ ለፀሐይ ክበብ ወብርሃን ወዋዕይ። ወይወፅኡ እምክበብ ብርሃኑ ወዋዕይ እንዘ ኢይቀድሞሙ ውእቱ ወኢይዴኅሩ ውእቶሙ። አላ ተረክቦቶሙ አሐደ ጊዜ።

ወካዕበ ይትዐወቅ በማይ እስመ ቦቱ ለማይ ስፍሕ ወርጥበት ወሁከት ርጥበትኒ ወሁከት ይትረከቡ እምነ ስፍሐ ማይ ወኢይዴኅሩ ርጥበት ወሁከት አላ ተረክቦቶሙ አሐደ ጊዜ።

ወካዕበ ይትዐወቁ በእሳት። እስመ ቦቱ በእሳት ፍሕም ወነበልባል ወዋዕይ። ወይትረከቡ እምነ ፍሕም ነበልባል ወዋዕይ እንዘ ኢይቀድሞሙ ፍሕም ወኢይዴኅሩ ነበልባል ወዋዕይ እምነ ፍሕም። አላ ተረክቦቶሙ አሐደ ጊዜ።

ወንሜስሎ ለአብ በክበበ ፀሐይ፥ ወበፍሕመ እሳት ወበስፍሐ ማይ። ወንሜስሎ ለወልድ በብርሃነ ፀሐይ /ፀዳሉ ፀሐይ/ ወበነበልባለ እሳት ወበርጥበተ ማይ። ወንሜስሎ ለመንፈስ ቅዱስ በዋዕየ ፀሐይ ወበሁከተ ማይ፥ ወበዋዕየ እሳት።

ትርጓሜውም፡- ልደትና ጸአት /አወጣጥ/ ያለቅደም ተከተል ለመገኘታቸው በምን ይታወቃል? ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር፤ ከልባችን በሚወጡት በቃላችንና በእስትንፋሳችን ይታወቃል። ይኸውም የሚያወጣቸው ልብ አይቀድማቸውም፤ ቃልና እስትንፋስ ከሚወጡበት ልብ ወደኋላ አይቀሩምና። ነገር ግን አንድ ላይ ይገኛሉ /ይፈጠራሉ/ እንለዋለን።

እንዲሁም በውኃ ይታወቃል። ውኃ ስፍሐትና ርጥበት ሁከት አለው። ርጥበትና ሁከት ከውኃ ስፍሐት የሚገኙ ሲሆኑ፣ ርጥበትና ስፍሐት ከውኃ ወደኋላ ቆይተው አይገኙም። ነገር ግን መገኛቸው አንድ ላይ ወይም አንድ ጊዜ ነው።

እንዲሁም ደግሞ፡- በእሳት ይታወቃል። በእሳት ፍሕም ነበልባል ግለት ይገኛል። ነበልባልና ግለትም ከእሳት ፍም ይገኛሉ። ይኸውም ፍም ሳይቀድማቸው ነው። ነበልባል ነበልባልና ግለትም ከእሳት ፍም ይገኛሉ። ይኸውም ፍም ሳይቀድማቸው ነው። ነበልባልና ግለትም ከእርሱ /ከፍሕም በኋላ አይመጡም፣ ነገር ግን አንድ ላይ ወይም በአንድ ጊዜ ይገኛሉ»።

ምዕራፍ አሥራ ስድስት።

የውኃ ኩነታትና የእሳት ኩነታት እንደ ፀሐይ ኩነታት ናቸው።

አሁን ልዩነቱን በሚቀጥለው አፍታተን ለማብራራት እንሞክር፡-

ይኸውም የብርሃን፥ የፀሐይ ኩነታት /የባሕር ወይም የውኃን ኩነታትና የእሳት ኩነታት ጠቅሰን ሳንነጋገርባቸው ቆይተናልና፣ አሁንም በመሠረቱ እንዴት እንደሆኑ አተኵረን ብንመለከታቸው፣ እያንዳንዳቸው አካል ሳይኖራቸው፣ መነሻ ከሚሆናቸው ከአንዱ አካል ብቻ ተገኝተው፥ ሁሉም ለዚያው አካል ኃይላት ወይም ግብራት ወይም ጠባይዓት ብቻ በመሆን፣ የሚታወቁ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ለምሳሌ ያህል ከተጠቀሱት ምሳሌዎች የአንዱን የፀሐይን ምሳሌ ወስደን ብንመረመር፣ ፀሐይ በከበቡ አካላዊነት እንደሚታወቅ እንገነዘባለን። ከከበቡ የሚገኙ ፀዳልም /ንጸብራቅ/ ሙቀት ግን ኃይላቱ ወይም ግብራቱ ከመሆን በቀር፥ በየራሳቸው አካል እንደሌላቸው እናያለን።

የውኃ ኩነታትና የእሳት ኩነታት እንደ ፀሐይ ኩነታት ናቸው። ርግጥ ነው እነዚህ ምሳሌዎች የሥሉስ ቅዱስ የባሕርይንና የህልውናን አንድነት መግለጫ ሆነው ለማስገንዘብና በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ መካከልም የጊዜ ቅደም ተከተል አለመኖሩን በማስታወቅ ረገድ ለመረዳት ያስቻሉን ከእግዚአብሔር የተሰጡን ትምህርታውያን መግለጫዎች ናቸው። በዚህም ሁናቴያቸው የነጳውሎስ ሳምሳጢን ሰፊ አፍ ሊዘጋ ያስቻለ፥ ታላቅ ቁም ነገር የተመላ ሙያ ማስገኘታቸው የማይካድ ነው።

ይሁን እንጂ፣ በምሳሌዎቹ ኩነት መጠን አብን ብቻ አካል ያለው አድርጎ በመመደብ፥ ቃልንና አስትንፋስን ግን በራሳቸው ጥንተ አካል እንደሌላቸው መቍጠር ፈጽሞ አይገባም።

እንግዲህ በፀሐይ ከበብና በውኃ ስፋት በእሳት ፍም አብን እንመስለዋለን። በፀሐይ ብርሃንና በውኃ ርጥበት በእሳት ነበልባልም ወልድን እንመስለዋለን። መንፈስ ቅዱስንም በፀሐይ ሙቀትና በውኃ ሁከት በእሳት ግለት /ትኩሳት/ እንመስለዋለን። /ምዕላድ ዘዐ. ሰዓ ከብቴ፡- ገጽ 24፣25።

ይህን ካየን ዘንድ፣ በእነዚህ ምሳሌዎች ማስረጃነት፡-

1ኛ፥ «ቦ አመ ኢሀለወ ወልድ። ወልድ ያልነበረበት ጊዜ አለ» ሲሉ ጳውሎስ ሳምሳጢ ተከታዩም ፎጢኖስ አስነሥተውት የነበረው ክህደት ወድቆ፥

2ኛ፥ «ቦ አመ ኢሀሉ መንፈስ ቅዱስ፡- መንፈስ ቅዱስ ያልነበረበት ጊዜ አለ» በማለት፥ መቅዶንዮስና አብሰለዲስ አስነሥተውት የነበረው ክህደት ተዘግቶ፥ ባጭሩ ይወልደዋል አይቀድመውም፣ ያሠርፀዋል አይቀድመውም የሚል አብነት ትምህርት ይታመንበት ዘንድ ያስቻለ መሆኑን ተገንዝበን፥ በመሠረቱም የተነገረውን ማስገንዘቢያ ለአንባብያን አቅርበናል። ፍኖተ እግዚአብሔር የአለቃ ጎሩይ ፈንታ መጽሐፍ፡-

ይኸውም፡- «ህልው አብ ምስለ ወልዱ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ እምቅድመ ሰዓት ወዕለት እምቅድመ አውራኅ ወዓመታት። አልቦ ቀዲመ ህላዌ ለአሐዱ እምካልዑ፥ ወለካልዑ እምኀልዩ፡- አብ ከልጁና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከሰዓትና ከዕለት አስቀድሞ

ከወራት ከዓመታት አስቀድሞ ህልው ነው። የአንዱ ከሁለተኛው የሁለተኛው ከሦስተኛው የህላዌ ቅድምና የላቸውም» /ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት ገጽ 98 ቍጥር 31።

ባስልዮስ፡- «ኢሀሎ አብ አሐተ ሰዓተ ወኢከመ ቅጽበተ ዓይን እንበለ ወልዱ ወእንበለ መንፈስ ቅዱስ፡- አላ ህልው ምስሌሆሙ በኩሉ ጊዜ፡- አብ ያለ ልጁና ያለ መንፈስ ቅዱስ አንዲት ሰዓት ወይም የቅጽበተ ዓይን የምታህል ጊዜ አልኖረም። ነገር ግን ከእነርሱ ጋር ሁልጊዜ እንደኖረ ነው።» ብሎአል። /ሃ.አበ.ባስ ዘቂ ገጽ 116 ክፍል 1 ቍጥር 4።

አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፡- «ንሕነሰ ነአምን ከመ ውእቱ ቃል አምላክ ዘበአማን ዘተወልደ እመለኮተ አብ ወልድ ዋሕድ ቀዳማዊ ምስለ አብ በኩሉ ጊዜ ወአልቦ መዋዕል እንዘ ኢሀሎ ውእቱ ምስለ አብ፤ ወከማሁ መንፈስ ቅዱስኒ። እኛ ግን እርሱ ቃል እውነተኛ አምላክ እንደሆነና ከመለኮተ አብም እንደተወለደ እናምናለን። በጊዜም ሁሉ አንዲያ ልጅና ቀዳማዊ ሆኖ ከአብ ጋር ነው። እርሱ ከአብ ያልነበረበት ጊዜ የለም፤ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው»። ሃይ አበ አትናቴዎስ ገጽ 84 ክፍል 14 ቍጥር 8።

ኪራኮስም ዘአንጾኪያ፡- «እስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እምነ አብ ወጥንተ ቅድሞና እሙንቱ ዘከመ አብ፤ ወአሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ፡- ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ተገኝተዋልና፣ እንደ አብም የቅድምና መሠረት ናቸውና፣ የሥላሴም ቅድምናቸው አንዲት ናትና» ብሎአል። ሃይ አበ. ኪራኮስ 398 ክፍል 1 ቍጥር 5።

ባስልዮስ ዘቂሣርያ፡- «ንእመን በሃይማኖት ከመ ይትዋሐድ መለኮት በአብ እስመ እምአብ ተወልደ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስኒ ወፅአ እምኔሁ እንዘ ኢይቀድም አሐዱ እምካልዑ ወካልዑ እምኃልሱ፡- መለኮት በአብ እንደሚዋሐድ በእምነት እንመን። ወልድ ከአብ ተወልዶአልና። መንፈስ ቅዱስም ከእርሱ ወጥቶአል። ግን አንዱ ሁለተኛውን፥ ሁለተኛውም ሦስተኛውን አልቀደመም» ብሎአል። ሃይማ አበ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ገጽ 107 ክፍል 1 ቍጥር 6።

ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ «ኢሀሎ አብ ግሙራ ወኢከመ ቅጽበተ ዓይን ዘእንበለ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢሀሎ ወልድ ግሙራ ወኢከመ ቅጽበተ ዓይን ዘእንበለ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢሀሎ መንፈስ ቅዱስ ግሙራ ወኢከመ ቅጽበተ ዓይን ዘእንበለ አብ ወወልድ፥ አላ ሥሉስ ቅዱስ ዕሩያን ህልዋን ወትረ ዘእንበለ ጥንት ወኢተፍጻሜት።

አብ አካቶ ለቅጽበተ ዓይን እንኳ፣ ያለወልድና ያለመንፈስ ቅዱስ አልነበረም። ወልድም አካቶ ለቅጽበተ ዓይን እንኳ ያለ አብና ያለመንፈስ ቅዱስ አልነበረም። መንፈስ ቅዱስም አካቶ ለቅጽበተ ዓይን እንኳ ያለ አብና ያለ ወልድ አልነበረም። ነገር ግን ሥሉስ ቅዱስ የተተካከሉና ምን ጊዜም ያለ መጀመሪያና ያለ መጨረሻ የሚኖሩ ናቸው» ሲል አብራርቶ ተናግሮአል። /ሃ.አ.ሳዊ ገጽ 357 ክፍል 1 ቍጥር 7።

ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ፡- «ይትኃፈሩ እንከሰ ወይጎሠሩ እለ ይትቃረኑ ወየአምኑ ከመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኢኮነ እምህላዌ አብ ዘአልቦ ካልዕ አምላክ ዘእንበሌሁ፡- እንኪያስ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ ከሌለበት ከአብ ባሕርይ እንዳልሆኑ እየተቃረኑ የሚያምኑ ፈጽመው ይፈሩና ጎሣር ይውደቅባቸው» ሲል አልባት አድርጎበታል።

እንዲህ ተደርጎ ለሚታመንበት እምነት፥ የመሠረቱን ጥልቀትና ጽናት ብሩህ አድርጎ የሚያሳይ ምስክር የምሳሌዎቹ ማስረጃዎች ናቸው። ዲዮና ዘአንጾ ሃ. አበ. ገጽ 450 ቍጥር 9 ክፍል 1።

እነሆም ከአበው ሊቃውንትና ከብሔራውያን መተርጕማን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት ተመርተው ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጡበት ጸአት /መውጣት/ ጕላ አድርገው ለማሳየት ያስቻሉ ምሳሌዎች፥ መሠረታዊ ትምህርቱን በግልጽ ለማስረዳት የቱን ያህል እንደረዱን፤ እኛም ራሳችን ተገንዝበናል።

ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጡበት ጸአት /መውጣት/ ከነገረ ነፍስ እንደ ቃልና እንደ እስትንፋስ፥ ከፀሐይ /ከመብራት/ እንደ ጸዳልና /ነጸብራቅ/ እንደ ሙቀት /ትኩሳት / ከእሳትም እንደነበልባልና እንደ ዋዕይ፤ ከውኃ እንደ ርጥበቱና እንደ ሁከቱ ያለውን የባሕርይ ጸአትን እንጂ፤ ከባሕርይ ውጭ እንደሆነው እንደሌላው ዓይነት ጸአት አለመሆኑን አስተውለናል።

በተከሥቶ ህልውና ትምህርታችን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ስለወጡበት መውጣት ነባቤ መለኮት ጎርጎርዮስ «ኢየኃልቅ ልደቱ እምኔሁ» ካለው ጋር አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ» ካለው ጋር ተመትሮ ተከፍሎ /ተፈልጦና/ ተሌልዮ ተድኅሮና ቅድምና በማያሳይ ሁኔታ የተጠቀምንባቸው የባሕርያዊ ህልውናን ይዞታ ሊያሳውቁን የበቁ ምሳሌዎች የነገረ ነፍስንና፥ የፀሐይን፥ የእሳትንና የቀላይን ያህል ጠቃሚ መግለጫ ሊሰጡን እንዳልበቁ እንደማይበቁም ዐውቀናል።

ምዕራፍ አሥራ ሰባት።

ቃልና እስትንፋስ እንደ አብ አካላውያን ናቸው።

በመሠረቱ ከአብ የሚሆን የወልድ ጸአት፥ /አወጣጥ/ እንደ ብዙኃን ጠባይዓዊ ልማድ /ሰው ወይም እንስሳ ልጁን በሚወልደው አኳኋን/ በብዙኃን ጠባይዓዊ ልማድ ወላጁ ወይም አባቱ ከልጁ ይቀድማልና፤ እንደዚህ እንዳልሆነ ተገልጸአል።

አንድም እንደ ብዙኃን ጠባይዓዊ ልማድ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን ካህናት ነገሥት ነቢያት ተብለው ሀብተ ወልድናን በማግኘታቸው «አማልክት አንትሙ ወደቂቀ ልዑል ኩልክሙ። አማልክት ናችሁ፤ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ» የሚሰኙበት የጸጋ ልደት ነበረና ሊቁ ዮሐ አፈወርቅ እንደ ግዕዘ ብዙኃን ያለው ይህንኑ ሲመለከት ነው። መዝ. 82፥8።

ይልቁንም አዳም በሀብት ወልደ እግዚአብሔር ተብሎ የለምን? እሥራኤልስ ወልድየ ዘበኵርየ ተብሎ የለምን? እንዲያውም ክርስቲያኖች ሁሉ በጥምቀት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ስመ ክርስትናን ሀብተ ወልድናን ነሥተው የለምን? ሉቃ. 3፥38። ዘጸአ. 4፥22። ዮሐ. 1፥12። ቲቶ 3፥4-8።

ስለዚህ ወልድ ከአብ የወጣበት የልደት ጸአት የባሕርይ መሆኑን፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበት ጸአትም /አወጣጥ/ ለአብ ሕይወቱና የሕይወቱ መታወቂያ ማኅተም በመሆን እንጂ፤ እንደ ብዙኃን ጠባይዓዊ ልማድ ከሰው ወይም ከእንስሳ እንደሚተንና ከአየር ጋር ተቀላቅሎ እንደሚበን እሳት ነፋስ እንዳልሆነ በጕላ በተረዳ አኳኋን ከዚህ በፊት ታትቶአል።

በጠቅላላ አገላለጽም፣ ቃልና እስትንፋስ ከአብ ወጡ ሲባል፣ በተከፍሎ ሳይለይ፥ በባሕርይ በህልውና አንድ እንደሆኑ ቅደም ተከተል ሳይኖርባቸው መውጣታቸው ለእነ ቦርፎሪስ ለእነጳውሎስ ሳምሳጢ፥ ለእነመቅዶንዮስና ለእነ አብስለዲስ ተተንትኖ በቀረበው ትምህርት በቂ መልስ ተሰጥቶአል።

ይህም የእነ ጳውሎስ ሳምሳጢንና የወገናቹን አፍ ሊዘጋ የቻለና፣ መልስ ወይም ማስረጃ የማይገኝለት መስሎአቸው ለሰነዘሩት የውጠራ ጥያቄ በቂ ማስረጃና መልስ ሆኖ የተሰጣቸው ትምህርት፦ ወልድ ከአብ የተወለደበት ልደት /ጸአት/ በከዊነ ቃል በከዊነ ብርሃን ወይም በከዊነ ነጸብራቅ፥ በእሳትና በነበልባሉ እንዲሁም በውኃ ርጥበት አምሳል በተሰጠ ምሳሌ መገለጫነቱ ሊታይ የሚቻል መሆኑን፥ ዳግመኛ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን ወይም የሠረፀበትን ሥርፀት /ጸአት/ በከዊነ እስትንፋስ፥ በፀሐይ ሙቀት፥ በእሳት ግለት /ዋዕይ/ እንዲሁም በውኃ ሁከት ምሳሌ ለመረዳት የሚቻል መሆኑን በቅዱሳት መጽሕፍት በተገኘ ግልጽ ማስረጃ መሠረት እንደነበረ የማይካድ መሆኑ ነው።

እነዚህ ምሳሌዎች ይኸውም የነገረ ነፍስ ኩነታት የፀሐይ ኩነታት የቀላይ ወይም የውኃ ኩነታትና የእሳት ኩነታት የጊዜ ተድኅሮና /ቅደም ተከተል/ መለየት በሌለበት ሁናቴ፥ የሥሉስ ቅዱስ የባሕርይንና የህልውናን አንድነት በማያጠራጥር ገለጻ ሊያሳዩ መቻላቸው የተፈተነ ማስረጃ ነው።

በመሠረቱም መርቄሎስና አቡሊናርዮስ አባ ጊዮርጊስ የሚጠቅሱት ስብልያኖስም፥ እነዚህን እላይ የጠቀስናቸው የኩነታት ምሳሌዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት መሆኑን፥ ተረድተዋል። ደግሞ በሥሉስ ቅዱስ ውስጥ የባሕርይና የህልውና አንድነት ብቻ እንጂ፣ ቅደም ተከተል እንደሌለ፣ የሚገልጹ መሆናቸውን በማየት ያለውዴታቸው ሊቀበሉዋቸው ተገደዋል።

ይሁን እንጂ፣ ምሳሌዎቹ የጳውሎስ ሳምሳጢን አፈ ሰፊነት ሲዘጉ ባዩዋቸው ጊዜ፣ በምሳሌዎቹ የተደሰቱባቸው አልመሰሉም። ይህም በስሜታዊ ቅርታቸው ሊታወቅ የሚችል ነው።

መቼም ቢሆን መናፍቃን ዞር ዞር በክፋት ስለማይተጣጡ ከቅዱሳት መጻሕፍት በሚገኝ ማስረጃ መሠረት አንዱ ጓደኛቸው ሲረታና፣ አፉ ሲዘጋ ደስ አይላቸውምና፣ የዚያን ቁጭት ለመወጣት ጓደኛቸው ከተረታበት ማስረጃ አንድን ነገር ፈጥረው በግጠማዘዝ በእውነተኛ ትምህርት ላይ እንከን ለማውጣት ሲጥሩ መገኘታቸው ከጥንት ጀምሮ ልማድ ኖሮአል።

በዚህም አኳኋን ደኅና አድርገው የተመለከቱዋቸውና የተከታተሉዋቸው አትናቴዎስ ሐዋርያዊና አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፦ የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ ሰጥተውናል።

«ወዘንተ ረከብነ ውስተ ትምህርተ ዐላውያን እለ ኢየኅብሩ በበይናቲሆሙ ወለኩለሙ አሐዱ ንባቦሙ በከህደት ዘያጸንን ኀበ ርስዐት። ወበእንተዝ ይጸልኡ በበይናቲሆሙ ወይትቃወሙ ወይትሜከሁ ላዕለ ነገረ ትምህርቶሙ ለአበዊነ እለ ተጋብኡ በኒቅያ።

በመናፍቃን ትምህርት ያገኘነው ይህ ነው። እርስበርሳቸው የማይተባበሩ ቢሆኑም እንኳ፣ ወደ መዘንጋት በሚያጋድል በከህደታዊ አነጋገራቸው አንድ ናቸው። ስለዚህ እርስ በርሳቸው ይጣላሉ፤ ይልቁንም በኒቅያ ጉባኤ በተወሰነው በአባቶቻችን ትምህርት

ላይ ይቃወሙና ይመካሉ» ብሎአቸዋል። ሃ አበ አትና ገጽ 93 ክፍል 15 ቍጥር 24።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡- «ለፎጢናስ ወለሰብልያናስ ወለአርዮስ አሐቲ ፍትወተ ሕሊናሆሙ ወእመሰ በአፉሆሙ ኢየኀብሩ ፍካሬ ሃይማኖት። በዓይነ ልቦሙሰ ይትናጸሩ ለአእኩዮ ህላዌሁ ወለአሐፅዖ ከዋኔሁ ለወልድ፡- ፎጢናስና ሰብልያናስ አርዮስ የአሳባቸው መሻት አንዲት ናት። ስለ እምነት ትርጓሜ ምንም በአንደበታቸው ባይተባበሩም እንኳ፣ የወልድን ባሕርይና ኩነት በመተናኰል ለማሳነስ አቃልሎ ለማሳየት ግን፣ በልባቸው ዓይን ይተያያሉ» ሲሉ ተናግረዋል። መጽ ምሥጢ ገጽ 116።

ይህም የመናፍቃን አስተሳሰብ ምንም እንኳ መንገዱ የተለያየ ቢመስል፣ ሄዶ ሄዶ በመጠቃቀስና በማምታታት ከአንድ አሳሳች ዓላማ የሚያርፍ ሆኖ ሳለ፣ አነሣሡን ግን በቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርት ላይ የሽምቅ ጦርን ከመወርወር የማይመለስ ሆኖ ይታያል።

እነሆም መርቁሎንና አቡሊናርዮስ፡- «ወልድና መንፈስ ቅዱስ፡-

1፥ ከነገረ «ነፍስ በተወሰደው ምሳሌና ማስረጃ በቃልነትና በእስትንፋስነት፡-
2፥ ከፀሐይ በተወሰደው ምሳሌና ማስረጃም በፀሐይ ነጸብራቅና ሙቀት፡-
3፥ ከእሳት በተወሰደው ምሳሌና ማስረጃም በነበልባሉና በሙቀቱ፡-
4፥ ከውኃ ወይም ከቀላይ በተወሰደው ምሳሌም በርጥበቱና በሁከቱ ከአብ መውጣታቸው የተገለጸ ሆኖአል።

እንዲሁም በአወጣጡ ረገድ የዘመን መቀዳደምና የህልውና መለየት አይኑር እንጂ፣ ምሳሌዎቹ የቃልና የእስትንፋስ አውነኢ /አስገኝ/ የተሰኘው አብ፥ ጥንተ አካል እንዳለው ሊያሳዩ ይችላሉ። ወነአኵ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግን ጥንተ አካልነት እንዳላቸው ሊያሳዩ አይችሉም» አሉ።

ይህ ከተባሉት መናፍቃን የተቃጣው አባባልም፡- «በአካላዊ አብ ልቡና መካከል፣ ከአካላዊ አብ ልቡና ወነአኵ ሆነው በተገኙት በቃልና በእስትንፋስ መካከል፥ የጊዜ ቅደም ተከተል ሊኖር አለመቻሉን ተቀበልን ብለዋል»።

ዳሩ ግን ይህን ቢቀበሉም ቅሉ፣ ቃልንና እስትንፋስን ከአካላዊ አብ ልቡና አሳንሰው ለመለየት፥ ከአካል በማስራቁትና ቃልንና እስትንፋስን ዝርዋን ወይም አካል-አልቦ በማድረግ፥ መዓረገ ርቱት የሚባለውን ደረጃ ፈጥረው፥ በሥሉስ ቅዱስ ዘለዓለማዊ ህልውና ላይ በመለጠፍ፥ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ከአብ ዝቅ አድርገው ለማሳየት ብቻ ይሆንኝ ብለው መነሣሣታቸው ስውር አይደለም።

ይህም የተሳሳቱበትን ጕዳና በጕልህ ለማሳየት ያህል ከሚያቀርቡአቸው አስተያየቶች ብቻ ቀጥሎ ባሉት እንይ፡-

1ኛ፥ ወልድ ከአብ የወጣበት አወጣጥ በልብና በቃል እንደሚገኙ አወጣጥ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ፡- በአወጣጡ የተገለጸው ምሳሌ ቅደም ተከተል የሌለበት አንድነቱም የባሕርያዊ ህልውና አንድነት መሆኑን መቼም ተቀበልን ብለዋል። ዳሩ ግን «አተርጋምን፥ በርፎሪኮን፥ አትሪኮን» የተባሉ ቃላተ እግዚአብሔር ዝርዋንና አካል-አልቦ መሆናቸው ስለሚታመን፣ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ የእነዚያን ያህል ይብቃው ማለታቸው ነው። /ሃ. አበ. ጎር ገባሬ መንክራት ገጽ 42፥ ክፍል 1፣21-25።

2ኛ፥ ወልድ የፀሐየ ጽድቅ ነጸብራቅ ወይም ፀዳል ስለመሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ጐልቶ መጻፉንና በነጸብራቁና በፀሐዩ መካከል ያለው ተረክቦ ቅደም ተከተል የሌለበት በባሕርይም የህልውና አንድነት ያለበት መሆኑን ተቀበልን ካሉ በኋላ፣ ነገር ግን ፀዳል ወይም ነጸብራቅ ወልድ ከፀሐየ ጽድቅ ከአብ ተገኝቶ አካላዊ /ክበብ/ በሚሆን ከአብ ህልው ሆኖ ይኖራል እንጂ፣ ራሱ አካል እያለው አይደለም። አሉ። ይኸውም፦

«እስመ ፀዳል ኢኮነ ጥንተ አካል፦ ፀዳል ወይም ነጸብራቅ አካል ያለው አይደለም። አላ ህልው ውስተ ካልዑ፣ ነገር ግን ከሚኖርበት አካል ጋር ይገኛል» ሲሉ ምገዱ፦ ድርሳን ዘዮሐንስ አፈወርቅ ገጽ 27፥ ድር 2።

3ኛ፥ መንፈስ ቅዱስም በከዊነ እስትንፋስ መውጣቱን ተቀበልን ካሉ በኋላ ዳሩ ግን መንፈስ አስትንፋሱ እግዚአብሔር ነውና አካል ያለው አይደለም። ወይም ደግሞ ለቁመተ ሥጋችን ከውጭ ስበን እንደምንተነፍሰው አየር ብቻ ነው አሉ። /ሃ. አበ. ዲዮናስዮስ ገጽ 440 ክፍል 1 ቍጥር 10።

4ኛ፥ መቅዶንዮስ የተባለ መናፍቅ «መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ እስትንፋሱ ነው እንጂ፣ በራሱ አካል የለውም» እንዳለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ጽፈውበታል። /መጽሐፈ ምሥጢር ይህ ሁሉ የምገደኛነት ሥራ እንጂ፣ ቁም ነገር ያለው አይደለም።

1፥ ይህ አባባል ተጠቃሎ የአነርሱ አስተሳሰብ ተንኰል እንዳለበት ያሳያል። እንደምን ቢሉ በምሳሌዎቹ /በነገረ ነፍስ፥ በብርሃን፥ በእሳት በውኃ/ በመጠቀም ከጀመርን፣ እስከ መጨረሻ ድረስ የሥሉስ ቅዱስ ልዑለ ባሕርይ አቋምን በምሳሌዎቹ መወሰን አለብን ስለማለት ያህል የተቃጣ አስተሳሰብ እንደሆነ ነው የሚታየው።

2፥ ምሳሌዎቹን በተዛባና በተጣመመ አስተሳሰብ አጀዙሮ በመተርጐም የእነጳውሎስ ሳምሳጢን ቁጭት በዚሁ ሊወጡላቸው መከጀላቸውን ያሳያልና ነው። እንደምን ቢሉ፦ ግዕዛን ከሌላቸው ፍጥረታት ማለት ከፀሐይ፥ ከእሳት፥ ከቀላይ ወይም ከውኃ ኩነታት ለመግለጫ ያህል እንድንጠቀምባቸው በጎ ፈቃዱ ሆኖ ሲሰጠን፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ከተፈለገው ትምህርት ሳንወጣ፣ በተወሰነ አእምሮአችን የገባንን ያህል በመጠቀም ፈንታ ምሳሌዎቹን ከምሥጢረ ሥላሴ ጠቅላላ አቋም ጋር በማስተካከል፥ መላ ለመላ ጠምደው ሊያመዛዝኑና ሊወስኑ መቃጣታቸው ነው።

ምነው የቤተ ክርስቲያን ደጋጎች መምህራን፦ «እስመ ምሳሌ ከሣቴ ገጸ ነገር ውእቱ፥ ምሳሌ የነገርን መልክ ገልጾ የሚያሳይ ነገር ነው» አላሉምን? ምሳሌ የነገርን መልክ ገልጾ የሚያሳይ መሆኑ ሲታወቅም ደግሞ፦

«ወሕገ ምሳሌሰ ይቴሐት እምነ ራዕይ እሙን፦ የምሳሌ ሕግ ግን ከእውነተኛ ተገላጭ ዋና ነገሩ ዝቅ ያለ ነው» ሲል አፈወርቅ አልተናገረምን?

ሊቁ ቄርሎስም «እስመ ምሳሌ ይውኅድ እምአማን ወይንዕስ እምተጠናቅቆ ምሳሌ ከእውነተኛ ነገር ያንሳል፣ ጥንቁቅ ሆኖ ከመታየት ይጐድላል» ብሎ አላስረዳምን?

አዎን፥ እነዚህ ወገኖች ስለ ምሳሌ አቋም፥ ይኸውም ምሳሌ ሲባል ከሚገልጸው አማናዊ ተገላጭ ትምህርት ሲነጻጸር፥ መላ ለመላ የማይመጣጠን መሆኑንና ሙሉ በሙሉ ተተካክሎ ሊወጣ የማይችል መሆኑን፥ ደግሞ ከታላላቆቹ የቤተ ክርስቲያን መምህራን የተሰጠ ምሳሌያዊ ደንብ መኖሩን አስተካክለው ባለመስማት ዋናው ምሥጢሩ ያመለጣቸው ናቸው ልንል እንችላለን።

እንዲህ ማድረግ በእውነቱ በምሳሌውና በአማናዊ ተገላጭ መካከል ተገልጾና ታውቆ ያደረገው ያልተስተካከለ ልዩነት እንዲያው በማድብስበስ ተሸፋፍኖ እንዳይታወቅ ለማድረግ፥ ከቤተ ክርስቲያን አበው የተጣራውን ትምህርትና መሠረታዊን እምነት በግብዝ አቋም የተተከለ ሥር ነቀልን ዛፍ አስመስሎ ለማሳየት እንደመሞከር ያህል ነው። እንዲያውም የጠማሚት መንገድ ተጉዞ አሻፈረኝ በማለት ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ከአካላዊው አብ ለይቶ ከአካል በማስራቆት አሳንሶ ለማሳየት በባለጋራነት የተወሰደ እርምጃዊ አስተሳሰብ ነው።

ስለዚህ ነገር ቢቈጫቸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ውግዘት እስከ መሰንዘር ሲደርሱ እናያለን። «እመቦ ዘይብል አብ ከመ ፀሐይ ወወልድ ከመ ብርሃኑ ወመንፈስ ቅዱስ ከመዋዕዩ ይትወገዝ እስመ አምጽአ ካልአ ሥርዓተ... ወአርአየ አሐደ ገጸ ዘኢይሜለስ በመጽሔተ ክበቡ ለፀሐይ፦ አብ እንደ ፀሐይ ነው፥ ወልድ እንደ ብርሃኑ፥ መንፈስ ቅዱስም እንደ ሙቀቱ የሚል ቢኖር ይወገዛል። ሌላ ሥርዓት አምጥቶአልና... በፀሐይ ክበብ መስተዋትም ሦስትነት የሌለበትን አንድ ገጽ ብቻ እንዳለ አሳይቶአልና ነው። ብለዋል»። መጽ. ምሥጢር ገጽ 123።

ይህ ምሳሌ በከፊሉ ሁሉም የሚናገርበትና የሚያምንበት ነውና አባ ጊዮርጊስ ስለምን እንዲህ አሉ? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። እንዲህ ያሉበት መክንያት በገዛ ራሳቸው ሲገልጹ፦

«እስመ አምጽአ ካልዐ ሥርዓተ... ወአርአየ አሐደ ገጸ ዘኢይሜለስ በመጽሔተ ክበቡ ለፀሐይ። ሌላ ሥርዓት ወይም ፈሊጥ አምጥቶአልና... በፀሐይ ክበብ መስታወትም ሦስትነት የሌለበትን አንድ ገጽ ብቻ እንደሚኖር አሳይቶአልና ስለዚህ ነው» ብለዋል።

አዎን፥ የመናፍቃኑ አባባል አብን ብቻ አካል ያለው አድርገው በማቆም፥ ቃልንና እስትንፋስን ግን ዝርዋን /አካለ-አልቦ/ አድርጎ መዐርገ ርቀትን የሚፈጥርና በሥሉስ ቅዱስ አቋም የአካል ዕሪናን /እኩልነትን/ የሚያጠፋ እንዲያውም አንደ ሰባልዮስ ባህል ሥላሴን አዋውጦ አንድ አካል የሚያደርግን አባባል ስላመጡባቸው ነው።

ስለዚህ አባ ጊዮርጊስ ባቀረቡት ምክንያት እንደ ገለጹት ሁሉ፥ የተቃወሙት ከምሳሌው አያያዝ ላይ ተጠግቶ የሸመቀውን ጠንቀኛ የእነሰባልዮስ አሰነዛዘርን እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም።

እነሆም ከአያያዝ ጕድለት የተነሣ፥ ታላላቅ ቁም ነገርን እንደሚጐዳ የታወቀ አይደለምን?

እርሱም ማንኛውም የአያያዝ ጕድለት ሊታረም የሚችለው መሳሌውን በሚጠቀሙበት ጊዜ፣ ከመጽሐፍ ትመህርታዊ ጉባኤ እንደሚነገረው ሁሉ ምሳሌው በየመልኩና በየአገባቡ እንደሚመጥን ተደርጎ ሲሰጥ፣ በአቀባበሉም ደግሞ የጉባኤውን ትምህርትና መመሪያ ከመሠረቱ በፅሙና ጥንቃቄ ባልተለየው ሕሊና ለመከተል ፈቃደኛነት ሲኖር ነው።

ምሳሌው በቅዱሳት መጻሕፍት የጸናውን ተገላጭ ዓምድ ለትምህርት በመግለጽ መጠኑን ጠብቆ ሊያገሳ ይመስላል። ዳሩ ግን የጸና ይዘት እንዳይወድቅ በምሳሌው አቋም ላይ መዝኖ ማየት ምን ጊዜም ያስፈልጋል።

«እስመ ውስተ ምይንት ነፍስ ኢተጎድር ጥበብ፤ እስመ ምሥጢራት ይትከሠታ ለትሑታን፡-» እየተባለ ከየወንበሩ መምህራን የሚሰጠው ትምህርታዊ መመሪያ በዚሁ ጊዜ መታወስ ይኖርበታል።

ግንም ቢሆን ይህን የሀገራችን መተርጉማን የሚያሰምሩትን ጠንቅቆ ቢያስተውለው፤ የፀሐይ የእሳት የቀላይ /የውኃ/ ምሳሌ በየመልኩና ከየአገባቡ በሚፈለግበት ትምህርታዊ ማስረጃ አጥቅም ላይ መዋሉን ለመረዳት ይችላል።

እነሆም ምሳሌ፥ ከአማናዊ ተገላጭ ጋር በተመሳሳይነት ሄዶ የአማናዊን አቋም በሚገባ እየገለጸ የሚያስረዳበት ጊዜ አለ። እንዲሁም የማይመሳሰልበት ሁኔታ አለ ማለት ይኸው ነው።

የአእምሮ ግዕዛን የሌላቸው የተጠቀሱት የፀሐይ፥ የእሳት፥ የቀላይ /የውኃ/ ኩነታት ይቅሩና፤ የአእምሮ ግዕዛን ያላት ነፍስ /መንፈስ/ እንኳን ብትሆን ቅሉ በምሳሌነትዋ ረገድ ሙሉ በሙሉ የሥላሴን ፍጹምነት አስተባቅታ የሥላሴን ፍጹምነት ወስና ልታሳይ ትችላለች ወይ? አዎን፥ እንዲህ ተብሎ ቢጠየቅ፤ መልሱ በእውነቱ አትችልም የሚል እንደሚሆን አያጠራጥርም።

መቼም ስለዚህ ነገር አስቀድመን ስንናገርበት መቆየታችን የሚታወስ ነው። ይሁን እንጂ፤ ከዚህ ተጣርቶ የሚገለጽበት ዋና ቦታው ሆኖ ስላገኘነው ከሥር ከመሠረቱ አቅርበን ብንከልሰው የሚያወርሰውን ነገር እንዲብራራ ያደርገዋል እንጂ፤ በምንም ሁኔታ የሚያሰለች ሁናቴ አይኖረውም።

ነፍስ የአንድነትና የሦስትነት አቋም ያላት በመሆንዋ፥ ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት በሚነገረው መሠረታዊ ተምህርት ረገድ የምንጠቀምባት ምሳሌ እንደሆነች ተገልጾአል። ታዲያ ብትሆንም ቅሉ፥ በምዕዋዳተ አካላት ትምህርት የማይገናዘቡ ሦስት ኩነታት፥ ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ ብቻ ያሉዋት ወይም በሌላ አገላለጽ ኩነታቶችዋ የሚገናዘቡባቸው ሌሎች ቀዋምያን አካላት የሌሉዋትና በአንድ አካል ብቻ ጸንታ የምትገኝ ናት። ስለዚህ ኩነታተ ነፍስ የሚባሉት ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ የአንዲት የነፍስ አካል ጠባይዐት እንደሆኑ ብቻ ይታያሉ።

በቅድስት ሥላሴ ግን እንዲህ አይደለም። የሥላሴ አካላት አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ሦስት ሲሆኑ፤ መጀመሪያ ነገር የእነዚህ አካላት ኩነታት /ጠባይዓት/ ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ እያንዳንዳቸው የሦስት አካላት ኩነታት በመሆን የታወቁ ናቸው። እንደዚሁም ደግሞ እያንዳንዱ አካል ለምሳሌ አብ በራሱ ልቡና ቀዋሚ ሆኖ በወልድ ቃልነት በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት የአካሉን ፍጹምነት ያስተባቃል።

ወልድም በራሱ ቃል ቀዋሚ ሆኖ በአብ ልብነት በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ፍጹምነት ያስተባቃል።

መንፈስ ቅዱስም በራሱ ሕይወት ቀዋሚ ሆኖ በአብ ልብነት በወልድ ቃልነት ምልዓተ አካሉን ፍጹምነት ያስተባቃል።

ማሳሰቢያ፡-

አንባቢም ያስተባቃል፤ ስለ መባሉ በኩነታትና በአካላተ ሥላሴ ቅደም ተከተል እንዳለ አድርጎ እንዳያስብ አደራ እንለዋለን። እንዲህ መባሉ ትምህርቱን ለመግለጽ እንዲያመች ብቻ ነው።

እንዲሁም ሦስቱ አካላት በኩነታት በልብነት፥ በቃልነት በእስትንፋስነት እርስ በርሳቸው የሚገናዘቡና በአንድ ህልውና የሚኖሩ ናቸው።

ይህም ስለ ነገረ ነፍስ አቋም በተገለጸበት ከፍል በሰፊው መመልከታችን የሚታወስ ነው። በምሳሌነትዋ የምንጠቀምባት ነፍስ በአካልዋ አንዲት ስትሆን ኩነታተ ነፍስ የሚባሉ ልብ ቃል እስትንፋስ ለዚህች ለአንዲት አካለ ነፍስ ጠባይዐት ሆነው መገኘታቸውን ብቻ ማየት ነው። በሌላ አቀራረብ ደግሞ የሥላሴ ኩነታት የሚሆኑ ልብነት፥ ቃልነት፥ እስትንፋስነት፥ እያንዳንዳቸው የሦስት አካላት ኩነታት እንደሆኑ መገኘታቸውን በጥንቃቄ መመልከት ነው።

«ነአምን ከመ አብ ልብ፥ ወወልድ ቃል፥ ወመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ» ሲል ያዕ. ዘእል. የተናገረውን እዚህ ላይ ማስታወሱ ትምህርቱን ለማገናዘብ ይረዳል። እነዚህም እንደምናያቸው የተለያየ አቀማመጥ ያላቸው እንደሆኑ የነፍስ ኩነታት የሥላሴ ኩነታት የተለያየ የአገላለጽ አቀራረብ እንደሚያስፈልጋቸው አያጠራጥርም፦

ለምሳሌ፦ በነገረ ነፍስ አንጻር ያቀረብናቸው የሥሉስ ቅዱስ ኩነታት ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ ማንጸሪያ በሆነች በነፍስ የማይገኘውን ልዩ ልዩ ባሕርያዊ ጠባይና ግብር ያሳያሉ።

ይኸውም የሥሉስ ቅዱስ ኩነታት ልብ ቃል እስትንፋስ የሦስት አካላት ኩነታት እንደመሆናቸው መጠን፦

1ኛ፥ ሦስቱ አካላት በኩነታት እየተገናዘቡ የየአካላታቸውን ፍጹምነትንና ምልዓትን ያስተባቁባቸው መሆኑን፦

2ኛ፥ የሥላሴ በህልውና መገናዘብ ትርኢትን በሚያሳይ ትምህርት፦ እርስ በርሳቸው ተገናዝበው የሥሉስ ቅዱስን አንድ ሕይወትነት ወይም አንድ ባሕርየ መለኮት የሚገልጹ ናቸው፦

3ኛ፥ የተከሥቶ ህልውናን ትርኢት በሚያሳይ ትምህርት የአካላዊ አብን በልብነት መሠረት አድርገው የየራሳቸውን አካል /በየአካላቸው/ በማንጸባረቅ ፍጹም በሆነ ዕሪና /በተካከለ እኩልነት/ አንድ ዓይነት አርአያ፥ አንድ ዓይነት አምሳልን አንድ ዓይነት ገጽ፥ አንድ ዓይነት መልክ እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው። ይህም እየገለጽነው ላለው ትምህርት ዓይነተኛ ውጤት ነው።

ምሳሌ አድርገን ባቀረብናት በነፍስ ግን በልብነት በቃልነት በእስትንፋስነት እየተገናዘቡ በህልውና አንድነትን፥ በጸአት ደግሞ ሦስትነትን የሚያሳዩና በእያንዳንዱ ኩነት ምድብ የሚታዩ ልዩ ልዩ አካላት የሉዋትም።

እንግዲህ መሠረታዊ ልዩነቱ እንደዚህ መሆኑ ታወቀ። ከታወቀም ዘንዳ፣ ሦስቱን የሥላሴን አካላት ምንጊዜም አንዲት አካል እንደሆነች በምትኖር በሰው ነፍስ አስተካክሎ መመሰል፤ በእውነቱ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ላይ፥ ጥብርብር የሚያደገውን ትርኢት ፈጥሮ የገዛ ራስን አእምሮ ወደ አስቸጋሪ ዐዘቅት ስለመጣል ያህል ነው የሚቈጠር።

የቤተ እስጢፋኖስ ወገኖች፥ ቀጥሎም በአጼ ፋሲል ዘመነ መንግሥት እምነታቸውን ለመመርመርና በኢትዮጵያዊነት አቋምና ትምህርት ለማጽናት ደንቀዝ ላይ ተሰብስበው የነበሩ የኢትዮጵያ ሊቃውንት መዝገበ ሃይማኖት በተባለው መጽሐፍ የእምነታቸውን መግለጫ ወስነው ሲያስታውቁ፥ ፍሬውን ከገለባው በመለየት ከምሳሌው የሚገኘውን ጥቅም ተገቢ በሆነ አቀራረብ እንዳስገነዘቡ እናገኛለን።

«ይሜለስ ብእሲ በቃሉ ወበእስትንፋሱ ወበእንተዝ ይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፤ ብእሲ ውእቱ ምሳሌሁ ለአብ፥ ወቃሉ ምሳሌሁ ለወልድ፥ ወእስትንፋሱ ምሳሌሁ ለመንፈስ ቅዱስ፥ ወባሕቱ አልቦቱ ለብእሲ ኃይል ከመ ይነጽሮሙ ለቃሉ ወለእስትንፋሱ። አላ ይሰምዖሙ እንዘ ይደምፁ በውሳጤሁ። እስመ አልቦሙ መልክዕ ወአልቦሙ ኃይል ለቃል ዉለእስትንፋስ ከመ ይነጽርዎ ለብእሲ እስመ ኢሀለዎሙ መልክዕ ወገጽ። ወባሕቱ ዕውቅ ከመ ህልዋን እሙንቱ እንበለ መልክዕ ወገጽ እስመ ምሳሌ የሐፅፅ እምዘይሜስሉ ቦቱ በከመ የሐፅፅ ሰምዕ እምወርቅ ከማሁ የሐፅፅ ብእሲ እምእግዚአብሔር አምሳሉ።

ወገጻተ ሥላሴሰ አኮ ከማሁ። ቦቱ ለአብ መልክዕ ፍጹም ዘኢይትማሰል ምስለ ፍጥረት። አላ ይመስሎሙ ለመልክዐ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለወልድኒ ዘውእቱ ቃሉ ቦቱ መልክዕ ዘይመስል መልክዐ አብ ወመንፈስ ቅዱስ። ወለመንፈስ ቅዱስኒ ዘውእቱ እስትንፋሱ ቦቱ መልክዕ ዘይመስል መልክዐ አብ ወወልድ።

ሰው በቃሉ በእስትንፋሱም እንደሚሠለስ /ሦስት እንደሚሆን/ እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በምሳሌያችን እንፍጠር» ብሎአል። ዘፍጥ. 1፥27።

ሰው የአብ ምሳሌ ነው። ቃሉም የወልድ ምሳሌ ነው። እስትንፋሱም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ነገር ግን ሰውዬው ቃሉንና እስትንፋሱን ለማየት ችሎት የለውም። ሆኖም ከውስጡ ድምፃቸው ይሰማዋል። ይኸውም መልክ የላቸውምና ነው። ቃልና እስትንፋስም ችሎታ የላቸውም። ሰውዬውን ሊያዩት አይችሉም። ይኸውም መልክና ገጽ ስለሌላቸው ነው። ይሁን እንጂ እነርሱ ያለመልክና ያለ ገጽ ሲሆኑ በህልውና መኖራቸው ደግሞ የታወቀ ነው። ምሳሌ ከሚመስሉበት ያንሳልና ሰም ከወርቅ እንደሚያንስ፥ ሰውስ ከተመሰለበት ከእግዚአብሔር ያንሳልና።

የሥላሴ ገጻት /አካላት/ ግን እንደዚህ አይደሉም። ለአብ ከፍጡራን መልክ የማይመሳሰል መልክ አለው። በዚህ መልኩ ግን የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን መልክ ይመስላል። ለወልድም እርሱ ቃሉ የሚሆን የአብንና የመንፈስ ቅዱስን መልክ የሚመስል ፍጹም መልክ አለው። ለመንፈስ ቅዱስም እርሱም እስትንፋሱ የሚሆን የአብንና የወልድን መልክ የሚመስል ፍጹም መልክ አለው።» ይላል። ሃይ. ገጽ 55 እና 56 ትምህርተ ሃይማኖት ዘቤተ አስጢፋኖስ።

አባ ጊዮርጊስ ለስብልያኖስ ሲናገሩ ተቃወሙበት እንጂ፣ በሌላ ቦታ ይህን ምሳሌ ተጠቅመውበታል።

አሁን በምሳሌው አያያዝ እንደሚገባ ባለማጠናቀቅ ተፈጥሮ የነበረው ስሕተት ምን መሆኑን ካስገነዘብን፣ የትምህርቱ ምዕማድ /መደላድል/ ተስተካከለ ማለት ነው።

እንግዲህ ከአብ አካላዊ ባሕርይ የሚወጡ ቃልና እስትንፋስ ከአካል ያልተራቆቱ ዝርዋን ያይደሉ፣ ነገር ግን እንደ አብ አካል ያላቸው ፍጹማነ አካል፥ ፍጹማነ መልክዕ፥ ፍጹማነ ገጽ እንደሆኑ ከቅዱሳት መጻሕፍት የተገኘውን መሠረታዊ አብነት እንዴት እንደሚያስረዳ መመልከት ይኖርብናል።

ምዕራፍ አሥራ ስምንት።

ዘርእየ ኪያየ፥ ርእዮ ለአብ /እኔን ያየ አብን አይቶአል።

ዮሐ. 14፥9።

1ኛ፥ አስቀድመን ስለ እግዚአብሔር ቃል አካላዊነት እንማራለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል ወልድን «ዘውእቱ አምሳሊሁ ለእግዚአብሔር ዘኢያስተርኢ፦

እርሱ የማይታይ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው» ሲል የተናገረውን አስቀድመን እንይ። ቈላ. 1፥15።

እዚህ ላይ የማይታይን ከማይታይ በማመሳሰል ይዞታ የሚያነጻጽር አቀራረብ ይገኛል። ይኸውም ወደ ዘይቤው ብናተኵር እግዚአብሔር የማይታይ እንደመሆኑ መጠን፥ ምሳሌው የሆነ እግዚአብሔር ወልድም /በትሥጉት መንገድ ካልሆነ በቀር/ ልክ እንደ እግዚአብሔር አብ የማይታይ መሆኑን ነው። ዘይቤው እየጠቆመ ወደሚያመለክተን ምሥጢር ወይም ጎይለ ቃል ብናተኵር ደግሞ መመሳሰሉን በባሕርያዊ አካል ሆኖ ይታየናል።

እነሆም ጳውሎስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ የአብ አከል መሰል ስለመሆኑ በተለያዩ ጥቅሶች ተናግሮአል።

ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ ይህን ጥቅስ በተረጐመ ጊዜ አጠናቅቆ ያብራራውን ትምህርት ብንመለከት፥ የዘይቤውን ጎይለ ቃል ማስረጃነት ግልጽ አድርጎት እናገኛለን።

«ነጽሩ መጠነ ዝንቱ ዕበይ ይቤ አምሳሊሁ ለእግዚአብሔር ዘኢያስተርኢ» ያጤይቅ ከመ ውእቱ መምሰሉ ለአብ በመለኮት... ወበከመ እግዚአብሔር አብ ዘኢያስተርኢ ጻድቅ ውኄር ዘለዓለም ባሕቲቱ ዘኢይመውት ከማሁ ለወልድኒ አምሳሊሁ ለአብ ቦቱ ኩሉ ዘተናገርነ በእንተ እግዚአብሔር አብ እስመ አምሳሊሁ ውእቱ። ወኢይትማሰል ዝንቱ አካል ካልዓነ በምንትኒ ወዝንቱ አምሳል።

ዘአምላከ ጽድቅ ውእቱ ዘኢይመውት ኄር ወቅዱስ ወአምሳልሂ ይሜህረነ ከመ እግዚአብሔር አሐዱ ውእቱ ወዝንቱኒ አምሳሊሁ ለዘኢያስተርኢ» ሃይ አበው ቄርሎስ ገጽ 296 ክፍል 36 ቍጥር 4-6።

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ፦ «ውእቱ አምላከ ጽድቅ ዘውእቱ ቃል ዘተወልደ እምአብ ወውእቱ ዕሩይ አምሳለ አብ ለዓለም ወውእቱ ቀዳማዊ በህላዌሁ ወለሌሁ ያበርህ በልዕልና ዕበዩ ባሕቲቱ መምሰሉ ወዕሪናሁ ለዘወለዶ»። ሃይ ቄር ገጽ 298 ክፍል 34 ቍጥር 289።

እርሱ የማይታይ የእግዚአብሔር ምሳሌ ብሎታልና፣ የዚህን ከፍተኛ መዓረግ መጠን ተመልከቱ። ይህም የሚያስረዳው፥ እርሱ /ወልድ/ በመለኮት አብን የሚመስል መሆኑን ነው።... የማይታይ እግዚአብሔር አብ እውነተኛ፥ ቸር ብቻውን የማይሞት ዘለዓለማዊ እንደሆነ ሁሉ፥ ስለ እግዚአብሔር አብ የተናገርነው ሁሉ የአብ መሰሉ ለሆነ ለወልድ አለው። እርሱ መሰሉ ነውና። ይህም አካል በማናቸውም ረገድ ሌሎችን የሚመስል አይደለም። ይህ አምሳል የማይሞት ቸር፥ ቅዱስ የሚሆን የእውነት

/የባሕርይ አምላክ/ መመሳሰልን ብቻ የሚመለከት ነው። ይህ መመሳሰል እግዚአብሔር አንድ እንደሆነና እርሱ ግለት ወልድ ምሳሌው እንደሆነ ያስተምራል።»

ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮትም፦ «ቀዳማዊ ዘሀሎ እምቅድም፥ መቅድመ ኩሉ መዋዕል ዘአልቦቱ ሥጋ ወልድ ዘእምአብ ብርሃን ዘእምብርሃን ነቅዐ ሕይወት ዘኢይመውት አምሳሊሁ ለአብ ዘኢይትዌለጥ፦ ከዘመናት ሁሉ አስቀድሞ የኖረ ቀዳማዊና ሥጋ ያልነበረው ከአብ የተገኘ ወልድ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ የማይሞት የሕይወት ምንጭ ለማይለወጥ አብ ምሳሌው ነው» ሲል አስረድቶአል። ሃይ አበው ጎርጎ ነባቤ መለኮት ገጽ 218 ክፍል 1 ቍጥር 1።

እዚህ ላይ ጎርጎርዮስ «የማይታይ በግለት ምትክ» የማይለወጥ የአብ ምሳሌ ብሎ መናገሩ፥ ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን ሲጽፍ ከዳዊት መዝሙር አመሣጥሮ በማገናዘብ የተናገረውን መሠረት በማድረግ ይሆናልና «ወልድ የማይለወጥ የአብ ምሳሌ» በሚል ገለጻ ላይ ማተኮር ይገባል። መዝ. 21፥25-27። ሚልክ. 3፥6። ዕብ. 1፥10-12። አንድም ሥጋ ያልነበረው ግለቱ ሥጋን ሳይለብስ የኖረበትን ሁኔታ ሲያመለክት መናገሩን መገንዘብ ነው።

ባስልዮስ ዘቂሣርያ፦ «ወልድ ዘተወልደ እምአብ አምላለ እግዚአብሔር ዘኢያስተርኢ ወዘኢይትዌለጥ ቃል ሕያው እግዚአብሔር ዘእም እግዚአብሔር ዘሀሎ ምስሌሁ ወኢኮነ እምድኅረሁ፤ ዘሀሎ እምቅድመ ኩሉ ዓለም ወኢኮነ ድኅረ፤ አላ ውእቱ ቀዳማዊ ወልድ ገባሪ ዘኢተገብረ ወውእቱ ፈጣሪ ዘኢተፈጥረ ዘቦቱ ኩሉ ዘአቡሁ ዕቀብ ሊተ አካላተ በበህላዌሆሙ በተዋሕዶ ወአሐደ አሐደ እምኔሆሙ በፍጹም ህላዌ አካሉሙ።

ከአብ የተወለደ ወልድ የማይታይ የማይለወጥ የእግዚአብሔር አምሳያ ነው። ሕያው የሆነ ቃል፥ ከእግዚአብሔር የተገኘ እግዚአብሔር። ከእርሱ በኋላ የተገኘ ሳይሆን፤ ከእርሱ ጋር ህልው ሆኖ የሚኖር ከዓለም ሁሉ አስቀድሞ የኖረ እንጂ፤ በኋላ ያልተገኘ፤ ነገር ግን እርሱ ሠሪ ነው እንጂ፤ የተሠራ አይደለም። ፈጣሪ እንጂ የተፈጠረ አይደለም። ለአባቱ ያለው ሁሉ ገንዘቡ የሚሆን ነው፤ አካላትን በየአቋማቸው በተዋሕዶ ጠብቅልኝ ከእነርሱም እያንዳንዳቸው በየአካላቸው ህላዌ ጠብቅልኝ» ሲል አምልቶ አስፍቶ ተናግሮአል። ሃ አበ ባስልዮስ ገጽ 112 ክፍል 4 ቍጥር 24፣25።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ብቻ ሳይሆን ቃለ አብ የአብ አከል መሰል ስለመሆኑ በብዙ ቦታ ተናግሮአል።

2ኛ፥ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ፦ «ዘውእቱ አርአያሁ ለእግዚአብሔር አኮ ኅይዶ ዘኮነ እግዚአብሔር እርሱ በእግዚአብሔር አምሳል የሚኖር ሲሆን፤ ቀምቶ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም።» በማለት ከፈተኛው ይበልጥ ጐላ አድርጎ ተናግሮአል። ፊልጵ. 2፥6።

ይህን ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ አውናምዮስ ለተባለ አርዮሳዊ ከፍ ባለ ችሎታ በተሞላ አቀራረብ ተርጉሞ ባብራራለት ጊዜ፤ የተናገረውን እንዳለ ጽፈአለሁ። «አንሰ አብል እስመ ዘተብህለ በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘውእቱ አምሳለ እግዚአብሔር ይተረጉም ከመ ውእቱ እምህላዌ መለኮቱ ለእግዚአብሔር ይትማሰሎ ለእግዚአብሔር አቡሁ በዕበየ መለኮት ወበስነ ኂሩት በፍጹም ገጽ ወበመልክዕ፦

እኔ «እርሱ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው ስለተባለለት ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ከህላዌ መለኮቱ እንደመሆኑ ሁሉ በመለኮት ታላቅነት በቸርነት ውበትና በፍጹም ገጽ በመልክና አባቱን እግዚአብሔርን

እንደሚመስለው ይተረጉማል እላለሁ።» ሃ አበ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ገጽ 106 ክፍል 1 ቊጥር 2።

ይህም የቅዱስ ባስልዮስ ገለጻ ቃለ አብ በባሕርይ ብቻ ሳይሆን፣ በአካልም እግዚአብሔርን አባቱን እንደሚመስለው ያረጋግጣል።

ባስልዮስ ዘአንጾኪያም «በከመ ውእቱ አምሳሊሁ ለእግዚአብሔር በመለኮት ወለሊሁኒ እግዚአብሔር ውእቱ ወአኮ በምትሐት ወአምሳል ከንቱ ዘአልቦ አካል» አለ። ገጽ 423 ክፍል 1 ቊጥር 21።

ፈላታዎስ ዘእስክንድርያ፡- «ንትአመን በወልደ እግዚአብሔር ዋሕድ ዘተወልደ እምአብ እምቅድመ ኩሉ መዋዕል ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ጽድቅ ዘእምአምላክ ጽድቅ አርአያ መልክው ወአካሉ ለአብ፡-

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ፡- «እስመ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር ውእቱ ናሁ ተአመነ በአካለ ህላዌ መለኮቱ ለወልድ ዘከመ አካለ ህላዌ መለኮቶሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ።

የእግዚአብሔር የፊቱ መልክ መባሉ ለወልድ ባለው በአካሉ የህላዌ መለኮት ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ባላቸው በአካላቸው የህላዌ መለኮት ልክ መሆኑ፥ እነሆ ሊታመን የተቻለ ሆነ»። ብሎአል ባስልዮስ ዘቂሣርያ ሃይ አበ ገጽ 106 ክፍል 1 ቊጥር 3።

ከጊዜያት ሁሉ አስቀድሞ ከአብ በተወለደ ተቀዳሚ ተከታይ በሌለበት /አንዲያ/ በእግዚአብሔር ልጅ እናምናለን። እርሱ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነት አምላክ የተገኘ አምላክ የአብ የመልኩና የአካሉ ምሳሌ ነው» ብሎአል። ሃይ አበ ፈላታዎስ ገጽ 473 ክፍል 2 ቊጥር 6።

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቴዎዶስዮስም፡- «ነአምን በእግዚአብሔር ቃል ከመ ውእቱ ዕሩይ በመለኮት ምስለ እግዚአብሔር አቡሁ ዘሀሎ ምስሌሁ በኩሉ መዋዕል ብርሃን ዘእምብርሃን ጽድቅ ዘእምጽድቅ አርአያሁ ለአብ ሕያው ዘቦቱ አካል።

የእግዚአብሔር ቃል ምንጊዜም ከእግዚአብሔር አባቱ ጋር የሚኖርና በመለኮቱ ከእግዚአብሔር ከአባቱ ጋር የሚተካከል መሆኑን እናምናለን። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን በእውነት ህልው የሆነ እውነት አካል ያለው የሕያው አብ አምሳያ መሆኑን እናምናልን።» በማለት አስረድቶአል። ሃይ አበው ቴዎዶስዮስ ገጽ 340 ክፍል 1 ቊጥር 21።

3ኛ፥ ሐዋርያ ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ የእግዚአብሔር ቃል ወልድን፡- «ዘውእቱ ጸዳለ ስብሐቲሁ ወአምሳለ አርአያሁ የክብሩ ነጸብራቅ የአካሉ ምሳሌ» ብሎት ይገኛል። ዕብ. 1፥3።

እነሆም፡- «የአካሉ ምሳሌ ሲል የክብሩ ነጸብራቅ» ከሚለው ጋር በዋዌ አያይዞ መናገሩ ታውቆአል።

«የክብሩ ነጸብራቅ» ባለ ጊዜ፣ ስለ ባሕርዩ አንድነት ለመግለጽ አስቦ እንደ ተናገረ ሁሉ፥ ስለባሕርይ አንድነት በተናገረበት መሠረትም ስለ አካል አቋም መናገሩ አስፈላጊ ሆኖአልና የእግዚአብሔር ቃል ወልድ በባሕርዩ ከአባቱ ጋር በአንድ ህልውና መኖሩንና በተለየ አካሉም ደግሞ እግዚአብሔር አባቱን የሚመስልና የሚተካከል መሆኑን ይኸው ኃይለ ቃል ይገልጻል።

ዮሐንስ አፈ ወርቅ፡- እግዚአብሔር ቃል ወልድን «የአካሉ ምሳሌ» ሲል ሐዋርያው የተናገረውን በተረጐመበት ክፍል እንደምን ባለ አገላለጽ እንዳስረዳ እንመልከት።

«ናሁ ይቤ ሐዋርያ «አርአያ አካሉ ዘባሕርይሁ» ዝብሂል በከመ አብ ህልው በአካሉ ዘእንበለ ሕፀት ወወልድኒ በአካሉ ከማሁ ውእቱ። ወበዝንቱ ቃል አሰሰለ ኦፋቄሆሙ ለዕልዋን ወአያቀ ከመ ውእቱ አምሳለ አቡሁ በአካለ ባሕርይሁ፡-»

እነሆም ሐዋርያ «የባሕርዩ አካል ምሳሌ» አለ። ይህም ማለት፥ አብ ያለምንም ሕፀፅ /ጕድለት/ በራሱ አካል ህልው /ቅዱም/ እንደሆነ ሁሉ፥ ወልድም እንደዚሁ በገዛ አካሉ ህልው /ቅዱም/ ሆኖአል ማለት ነው። በዚህ ቃል የመናፍቃንን ጥርጥር ሊያስወግድ ችሎአል»። አለ። ድርሳን 2፥ ገጽ 28።

አንድም «የባሕርዩ አካል ምሳሌ» ሲል ሐዋርያው የተናገረውን በድጋሜ ሲያስረዳ፥ የሚቀጥለውን ትርጓሜ ሰጥቶ አብራርቶአል።

«እስመ አርአያ ባሕርይ ካልዕ ውእቱ እምቀዳሚ ሥርው ወባሕቱ ኢፍሉጥ እምኔሁ በግዕዘ ጠባይዕ ወሥምረት ዘእንበለ በአካል ባሕቲቱ፡- የባሕርይ ምሳሌ ሲባል፥ ከመጀመሪያ ግንዱ ሁለተኛ ወይም ከዚያ ሌላ መሆኑ ግልጽ ነው። እነሆም በአካል ብቻ የተለየ ነው እንጂ በግዕዘ ጠባይዕና በፈቃድ ግን ከመጀመሪያ ግንዱ የተለየ አይደለም» አለ። ድርሳ 2 ገጽ 37።

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ስኑትዩም፡- «ይህን ጳውሎስ «የክብሩ ብርሃን የአካሉ ምሳሌ» ሲል የተናገረውን እንደሚከተለው ተርጕሞ አብራርቶታል። ዕብ. 1፥2፣3።

«ዘተወልደ እምአብ እምቅድመ ኩሉ መዋዕል ብርሃን ዘእምብርሃን አምላከ ጽድቅ ዘእምአምላከ ጽድቅ ዘውእቱ ብርሃነ ስብሐቲሁ ወአርአያ አካሉ፡- ከዘመናት ሁሉ አስቀድሞ ከአብ የተወለደ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከባሕርይ አምላክ የተገኘ የባሕርይ አምላክ እርሱ የክብሩ ብርሃንና የአካሉ ምሳሌ ነው» ብሎአል። ሃይ አበ ስኑትዩ ገጽ 509 ክፍል 2 ቍጥር 22።

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ዘካርያስም፡-

«ዝንቱ ቃል ወልዱ ወአርአያ አካሉ ለአብ፡- ይህ ቃል ለአብ ልጁና የአካሉ ምሳሌ ነው።» ሲል ተናግሮአል። /ሃይ አባ ዘካርያስ ገጽ 496 ክፍል 2 ቍጥር 31።

የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስም፡- ብርሃነ ስብሐቲሁ ዘይትማሰሎ ለአካለ አብ። /ወአምሳለ አካሉ/

ከብርሃን የተገኘ የክብሩ ብርሃን፣ የአብን አካል ፈጽሞ የሚመስል ነው» አለ። ሃይ አበ. ዮሐ ዘአንጾ ገጽ 542 ክፍል 2 ቍጥር 10።

ይህንም ሁሉ፥ በማጠቃለል ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፡-

«ወኩሉ አምሳል ዘተናገርነ በእንተ አብ ለወልድኒ ቦቱ እስመ አምሳሌሁ ውእቱ፡- ስለ አብ የተናገርነው ምሳሌ ሁሉ ለወልድም አለው፣ እርሱ መሰሉ ነውና» ካለው ጋር አባባሉ ያልራቀ ሆኖ ይገኛል።

ሃይ አበ ባስልዮስ ዘቂ ገጽ 112 ክፍል 4 ቍጥር 2።

እነሆም ከዚህ በላይ ከሐዋርያ ጳውሎስ ለተነገረው ሁሉ አሣሪ የሆነ ዓይነተኛ ገለጻ በወንጌል እናገኛለን። እርሱም ራሱ ባለቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ ዘርአየ ኪያየ ርእዮ ለአብ፦ እኔን ያየ አብን አይቶአል» ሲል የተናገረውን አዛማጅ ማስገንዘቢያ ነው። ዮሐ. 14፥9። ም. 12፥45።

ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ከተናገረው ጠቅሰ፦ ዲዮናስዮስም፦ «ዘርአየ ኪያየ ርእዮ ለአብ» ያለውን ሲተረጉም «እስመ ለአብ ቦቱ አካል ለርእሱ በባሕቲቱ፥ ወልድኒ ዘያስተርኢ በአካሉ ወቦቱ ያስተርኢ አካሉ ለአብ ወፀዳሉ ለእለ ይሬእይዎ ለአብ ለምንትኑ ትትኀሠሡ ይእዜ ውእቱሰ ወልዱ በህላዌ ዘቦቱ ወበእንቲአሁ ይትአመር ዚአሁ ለአብ፦ አብ በራሱ በብቻው አካል አለው። ወልድም ከአካሉ ይገለጻል። ለሚያዩት የአብ አካሉና ነጸብራቁ በእርሱ ይታያል። አሁን ስለምን ትከራከራላችሁ እርሱ ከባሕርዩ ልጁ ነው። /በአብ ያለ ህልውናም/ የአብ ገንዘብነቱም በእርሱ ይታያል።»

ወልድ ቃለ እግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ መሆኑን ባስገነዘበበት ባሕርዩ የማይታየውን አባቱን እንደሚገልጽ፣ በአካሉና በመልኩም ልክ አባቱን እንደሚመስል በዚሁ ገለጻው በማያወላውል ሁኔታ ተናግሮአል። ዲዮ ዘአንጾኪያ ገጽ 440 ክፍል 1 ቍጥር 9።

ይህ የወልድ አካል የአብን አካል መምሰሉንና መመሳሰሉም የባሕርይ መሆኑን የሚያስረዳ ምሥጢር ይዞ ለመገኘቱ አያጠራጥርም።

አብን የሚመስለው በአካል ብቻ ሳይሆን፣ በባሕርይ አካልም መሆኑን ያሳያልና ነው። የአካሉ ባሕርይ ከአብ የአካል ባሕርይ ተመሳሳይ ባይሆን ኖሮ፦ «እኔን ያየ አብን ፈጽሞ አየ» ብሎ ባልተናገረም ነበር።

ይህም ስለ ተባለ የአንዱ እግዚአብሔር ባሕርያት ብዙ ሆነው እነርሱ እንደሚመሳሰሉ የተነገረ እንዳይመስለው ለአንባቢ እናሳስበዋለን። የእግዚአብሔር መለኮት ሲባል ወይም ባሕርይ ሲባል አንድ ነው እንጂ ብዛት የለውም። ደግሞ ባሕርዩ የተለያየ ሆኖ የሚመሳሰል የሚመስለው ሰው ይኖር ይሆናል። ስለ ባሕርዩ መመሳሰል የተነገረ ሳይሆን ስለ ባሕርዩ አካላት መመሳሰል የተነገረ መሆኑን ማስተዋል እንዳለበት ልናሳስበው እንወዳለን። ዮሐ. 5፥37።

አምን፦ ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጥሮአል። ዳሩ ግን ቃለ እግዚአብሔር ወልድ በአካሉ አብን በሚመስለው ልክና መጠን፥ ሰው እግዚአብሔርን ይመስላልን?

ነሐስ ወርቅን ቢመስል፣ በባሕርዩ ዓይነቱ ወርቅን እንደማይመስል ሁሉ፥ ሰውም ለባዊ ነባቢ ሆኖ በመፈጠሩ እግዚአብሔርን ይመስላል ተባለ እንጂ፣ በባሕርዩ እግዚአብሔርን ይመስላል አልተባለም።

በመሠረቱ ማንም ሰው ሰውን ቢያይ፣ እግዚአብሔርን አይቶአል ሊባል አይቻልም። ከዚህ ጋር «እስመ ምሳሌ የሐፅፅ እምዘይሜስሉ ቦቱ በከመ የሐፅፅ ሰምዕ እምወርቅ፣ ከማሁ የሐፅፅ ብእሲ እምእግዚአብሔር አምሳሉ» የተባለውን ማስተወስ ጠቃሚ ነው።

ወልድ ግን «ዘርአየ ኪያየ ርእዮ ለአብ፣ እኔን ያየ አብን ፈጽሞ አይቶአል» ይላል። ዮሐ. 14፥4።

ሊቁም፡- «ርእይሰ ዘመለኮት አኮ ዘሥጋ አላ በኃይል ወበስብሐት ዘይደሉ ለመለኮት። የመለኮት መታየት የሥጋን መታየት የሚመለከት አይደለም። ነገር ግን ለመለኮት በሚገባ በኃይልና በክብር መታየት ነው። ሲል የተረጐመውን በዓይነ ልቡና እየቃኙ ለይቶ ማወቅ ይገባል።

ይህን እያሰላሰሉ፡- ዮሐንስ አፈወርቅ፡- «ተብህለ በእንተ እግዚአብሔር ከመ አልቦ ዘይመስሎ ዘእንበለ ዘተወልደ እምኔሁ ዘውእቱ ፀዳለ ስብሐቲሁ፡-

ስለ እግዚአብሔር የተነገረው ነገር ከእርሱ ከተወለደውና የክብሩ ነጸብራቅ ከሆነው በቀር፥ እግዚአብሔርን የሚመስለው እንደሌለ ነው» ያለውን ይገነዘቧል። /ድርሳን ዮሐ አፈ ወርቅ ገጽ 38 ድርሳን 2።

ጌታችን «እኔን ያየ አብን ፈጽሞ አየ» ብሎ ሲናገር የሰማና ክብሩን ያየ ወንጌላዊ ዮሐንስ፡-

«ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ አሐዱ ዋሕድ ለአቡሁ፡- ለአባቱ እንደ አንድ ልጅ የሚሆን ባለው ክብር መጠን የሆነውን ክብሩን አየን።» ሲል መስክሮአል። ዮሐ. 1፥14-16።

ለዚህም ለዮሐንስ ምስክርነት ሊቁ ባስልዮስ ዘቂሣርያ የሚከተለውን ትርጓሜ ሰጥቶ አብራርቶታል።

«ወበዝንቱ ይትዐወቅ ከመ ኢተውህቦ ዝንቱ ስብሐት በጸጋ ወኢበሃብት አላ በተዋሕዶ አሐዱ መለኮት እሰመ ወልድ ቦ ልዕልና» ስብሐት ዘአቡሁ። እስመ በሀብት ይነሥኡ እምሉዓሌ ኩሎሙ ፍጡራን ልዕልና፥ ለወልድሰ ቦቱ ኩሉ ዘተናገርነ በእንተ ስብሐተ ህላዌ አብ ዘበድልወት፣ ዝንቱ ውእቱ ዘተወልደ እምአብ እሰመ ወልድ ዋሕድ ኅቡረ ህላዌ በመለኮት ውእቱ።

ይህ ክብር ወይም የጌትነት ምስጋና በአንዱ የመለኮት ተዋሕዶ አንጂ፣ በጸጋና በስጦታ እንዳልተሰጠው በዚህ ይታወቃል። ወልድ የአባቱ የክብር ልዕልና አለውና ነው። ፍጡራን ሁሉ ግን ልዕልናን የሚያገኙት በጸጋ ስጦታ ነው። ስለ አብ ባሕርያዊ ክብር በሚገባ የተናገርነው ሁሉ ለወልድ ደግሞ አለው እርሱ ነውና ከአብ የተወለደ፥ በህላዌ መለኮት አንድ የሚሆን /የባሕርየ መለኮት አንድ ህልውና የሚሆን/ አንዲያ ልጅ ነውና»። ሃይ አበ ባስልዮስ ገጽ 112 ክፍል 4 ቍጥር 27-33።

በዚህ ዮሐንስ ወንጌላዊ በተናገረው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስም የሚከተለውን ገለጻ ሰጥቶአል።

«ከመ አብ ቀዳማዊ እሰመ ኃይሉ ውእቱ ወጥበቡ ለአብ ወብርሃነ ስብሐቲሁ ወአምሳለ አካሉ ወበዝንቱ የትሌበው ዘዕሩይ ምሌሁ በክብር ዘይደሉ ለመለኮት በከመይቤ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ፡- እንደ አብ ቀዳማዊ ነው። እርሱ ኃይሉና ጥበቡ የአብ የክብሩ ብርሃን የአካሉ አምሳያ ነውና፣ በዚህም ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ እንዳለው ሁሉ፥ ለመለኮት በሚገባ ክብር ከእርሱ ጋር እኩል ነው»። ዮሐ ዘአንጾኪያ ገጽ 440 ክፍል 1 ቍጥር 9።

ኪራኮስም «አሐዱ አካል እምሠለስቱ አካላት ዘውእቱ እግዚአብሔር ቃል ጥበቡ ለአብ ወኃይሉ ውብርሃነ ጽድቅ ዘያበርህ እምብርሃነ አብ ብሩህ፣ አምላክ ዘኢይትዌለጥ እምአምላክ ዘበአማን ዘተወልደ እመለኮተ አብ። ሃይማ አበው ኪራኮስ ገጽ 400 ክፍል 1 ቍጥር 17። የአብ ጥበቡና ኃይሉ የሚሆን ከብሩህ አብ ብርሃን ሆኖ የተገኘ የማይለወጥ እውነተኛ አምላክ ከመለኮተ አብ የተወለደ ነው»።

«እምቅድመ ዓለም ወውእቱ ይመልዕ ኩሎ ወየዐቅብ ኩሎ ወበቱ መለኮተ እግዚአብሔር አቡሁ እምቅድመ ኩሉ ሚመታት በህላዌ ዘኢይትዌለጥ። ሎቱ ስብሐት ምስለ አቡሁ ኄር ወመንፈስ ቅዱስ ሥሉስ ቅዱስ ዕሩይ በኩሉ ግብር ኢፍጡር ውእቱ ወኢይትዌለጥ አልቦቱ ጥንት ወኢተፍጻሜት በህላዌ አሐዱ መለኮት እንዘ ሠለስቱ ገጻት ወእንዘ ሠለስቱ አካላት ወእንዘ ሠለስቱ መልከዐት»። ሃይ አበ አትና ገጽ 79 ክፍል 1 ቍጥር 30፣ 31።

እንደተገለጸው ሁሉ፥ እርሱ የአባቱ አከል መሰል መሆኑ፥ በዚህም ከአብ ጋር የመተካከል /የዕሪና/ አንድነት ያለው መሆኑ፥ ሊታወቅ ተችሎአል።

እንግዲህ ይህ ሁሉ ማስረጃ በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጾ ሲኖር ሳለ፣ እነ ሰባልዮስና መርቄሎን አብሰለዲስ፡- ቃለ አብን ከአካላዊ አብ ነጥለው አካል እንደሌለው ዝርው ነገር በመቍጠር ወይም ከአካል የተራቈተ በማድረግ ማሰብ ይገባቸው እንዳልነበረ ይታያል።

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ።

አተርጋዎን፥ በርፎሪኮን፥ አአትሪኮን።

እንዲሁም ደግሞ «አተርጋዎን፥ በርፎሪኮን፥ አአትሪኮን» እንደሚባሉ ቃላት ቈጥረው ቃለ አብን ዝርው ለማድረግና ከአካል የተራቈተ ለማድረግ መሞከራቸው የሚያስደንቅ ነው። ይህንም ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት በተነጻጻሪ ጠቁሞት ይገኛል።

አተርጋዎን፥ በርፎሪኮን፥ አአትሪኮን የተባሉ ቃላት ምንም እንኳ በአወጣጣቸውና በአገባባቸው ሁኔታ በተለያየ ስም ቢነገሩም፣ የምሥጢራቸው መሠረታዊ አቋም የአካል ውጤቶች እንደሆኑ ይገልጻቸዋል እንጂ፣ የገዛ ራሳቸው አካላውያን ቃላት መሆናቸውን አይገልጽም። ይኸውም በሰዋስው ደንብ የግብር ስም ሆነው የምናገኛቸው ናቸው። 1ቆሮ. 13፥1-3።

ለምሳሌ፡-

ሀ፥ አተርጋዎን የተባለው፥ ድምፅ ፍሬ ነገር ያለበት የመላእክት ቃል ነው። ይህም «ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ በሚል በመላእክት ቅዳሴ ይታወቃል»። ኢሳ. 6፥3። ራዕ.4፥8።

ደግሞ በርፎሪኮን፥ አአትሪኮን በተባሉት ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት ብንሞክር፣ እንደምን እንደሚቀራረቡና እንደሚራራቁ ሳይገልጽልን አይቀርም።

ለ፥ በርፎሪኮን ነቢያት የሰሙት፥ ቃለ እግዚአብሔር ነው። ዕብ. 1፥1።

እነሆም፡- በአሪት፡- «ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡- እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው አለውም... ዘጸአ. 19፥3። ም. 33፥1-3። ዘኍል. 28፥1 በማለት እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር አምስት መቶ ሰባ አምስት ጊዜ፣ የተናገረው ቃል «በርፎሪኮን» ተብሎአል። በጠቅላላውም እግዚአብሔር ለአበውና ለቅዱሳን ነቢያት ለባለራዕዮች ሁሉ የተናገራቸው ቃላት በሙሉ «በርፎሪኮን» ተብለዋል። ሕዝ. 18፥1።

ታዲያ በርፎሪኮን ነቢያት የሰሙት ቃለ ትንቢት ሲሆን፣ ይኸውም ቃለ እግዚአብሔር የተነገረና የተገለጸ እንደመሆኑ መጠን፥ ግብር ሆኖ በመውጣቱ የግብር ስም ይሆናል እንጂ፣ ለብቻው ወይም በብቻው ሲታይ፣ አካላዊ ቃል አይደለም። ይህ ባጭሩ አወጣጡ ከእግዚአብሔር ሆኖ ወደ ነቢያት ጆሮ መግባቱን የሚያመለክተን ገለጻ ነው ያለው።

ሐ፥ አአትሪኮን ደግሞ፦ ከአንድ አካላዊ ባለግዕዛን /እንደ ሰው ወይም እንደ መልአክ ያለ/ ወይም ግዕዛን አልቦ ከሆነ /እንደ እንስሳ ወይም አንድ ነገር ከሆነ/ አቅዋም ውጪታዊ ግብር ሆኖ መጥቶ ወደ አየር የሚበንና በአየርም ተቋጥሮ የሚላክ ቃል ነው።

ለምሳሌ፦ ከሰው እንደሚነገር ወይም ከደወልና ከመሰንቆ እንደሚወጣ ድምፅ ያለው ነው። 1ቆሮ. 13።

እንግዲህ ይህ ዓይነቱ ቃል በአየር ላይ መላኩን ለመግለጽ «አአትሪኮን» ተባለ እንጂ፣ ከአንድ አካላዊ ነገር በመውጣት የግብር ስም መሆኑን ከመግለጽ ሊዘል አልቻለም።

ዓቃቤ ሰዓት ከብቴ ሲፈላሰፉ «ቃል ዘሀሎ ምሉዐ ውስተ አየር ዘውእቱ ጠባይዐ እሳት»።

«በአየር ላይ ሞልቶ የእሳት ጠባይ ያለበት ቃል ቢሉትም እንኳ፣ የተፈጥሮ ጠባይውንና ሞገዳዊ ጕዞውን በማብራራት፥ በተፈጥሮ እንደ ብርሃን ነጸብራቅ /ጨረር/ አብነት መልዓተ አካል በሚያሰኝ በለባዊነት፥ በነባቢነት፥ በእስትንፋስነት የተገናዘበ ፍጹመ አካል ወይም ምልዐተ አካል ይኖረዋል አላሉምና፣ አካላዊ እንዳይደለ ታውቆአል»። መጽሐፈ ምዕላድ ዘዐቃቤ ሰዓት ከብቴ ትምህርተ ሥላሴ ተመልከት።

ይህን ካየን ዘንዳ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ወልድ ቃል በሚባልበት ስሙ እላይ በተወሰኑ ቃላት አቋም የማይወሰን መሆኑን፥ ራሱ አካላዊ ቃል መሆኑን እያነጻጸረ ከሥር ከመሠረቱ አጣርቶ ያብራራውን ገለጻ እንመልከት።

«ወለዝንቱ ስም ዘውእቱ ቃል ንሌብዎ እምሠለስቱ ቃላት ወእምሠለስቱ ግብራት። አተርጋዎን፥ በርፎሪኮን፥ አአትሪኮን እሉ እሙንቱ ቃላተ እግዚአብሔር በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ወአኮ እሙንቱ ህልዋን በአካላት።

አተርጋዎን አኮ ውእቱ ህላዊ በአካል። ወበርፎሪኮንኒ ውእቱ ቃል ዘሰምዕዎ ነቢያት እምኀበ እግዚአብሔር ወውእቱ ቃለ ትንቢት። ወአኮ ውእቱ ህላዊ በአካል አአትሪኮን ውእቱ ቃል ዘይትከዐው ውስተ አየር ወእምኔሁ ይትፈኖ ንባብ ወአኮ ውእቱ ህላዊ በአካል።

ወቃለ እግዚአብሔርሰ ህልው በአካሉ እምህላዌ ልዑል ወፅኑዕ ወውእቱ ቀዳማዊ ብሎየ መዋዕል። ህልው ምስሌሁ እምቀዲሙ ወኢይትፈለጥ እምኔሁ። ወኢየኀልቅ ልደቱ እምኔሁ። አላ ውእቱ ብሎየ መዋዕል ምስሌሁ በኩሉ ጊዜ ዘእንበለ ፍልጠት።

ወኢታምስልዎ ለዝንቱ ቃል ከመ ቃላት እለዘከርናሆሙ ዘእንበለ ህላዌ ወአካል። አላ ውእቱ ፍጹመ መልክዕ ወአካል ከመ ገጸ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ።

ይህንም ስም፥ እርሱም ቃል የሚሆን፦ አተርጋዎን፥ በርፎሪኮን፥ አአትሪኮን ከተባሉ ከሦስት ቃላትና ግብራት ልናስተውለው እንችላለን። በቅዱሳት መጻሕፍት

እንደተጻፈው፥ እነዚህ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው። እነዚህ በአካላት የሚኖሩ አይደሉም።

አተርጋዎን በአካል ነዋሪ አይደለም። ወይም የአተርጋዋን አኗኗር አካላዊ አይደለም። በርፎሪኮንም ነቢያት ከእግዚአብሔር የሰሙት ቃል ነው። እርሱም የትንቢት ቃል ነው። ይኸውም በአካል ነዋሪ አይደለም። አአትሪኮንም የተባለው ቃል ድምፅን ተሸክሞ የሚላክ አየር ላይ የሚበን ቃል ነው። እርሱ በአካል ነዋሪ አይደለም።

የእግዚአብሔር ቃል ግን ልዑልና ጽኑዕ ከሚሆን ባሕርዩ በአካል ህልው ነው። እርሱም ቀዳሚና የዘመን አሮጌ ነው። ከዘለዓለም ጀምሮ በህልውና ከእርሱ ጋር የሚኖር የማይለይ ነው። ልደቱም ከእርሱ አያልቅም አይቋረጥም። ነገር ግን ሁልጊዜ ያለ መለየት ከእርሱ ጋር የዘመን አሮጌ እንደሆነ ይኖራል።

ይህም ቃል ያለ አካልና ያለ ባሕርይ እንደሚኖሩ እንደእነዚያ እንዳስታወስናቸው ቃላት ልታመሳስሉት አይገባም። ነገር ግን እርሱ እንደ አባቱና እንደ መንፈስ ቅዱስ በአካል በመልክ በገጽም ፍጹም ነው»። ጎርጎ. ገባሬ መንክራት 42 ክፍል 21 ቍጥር 22-27።

ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት እንደገለጸው ሁሉ፥ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ዲዮናስዮስ እንደሚከተለው ተናግሮአል።

«ውእቱሰ ወልድ ውእቱ ዋሕድ ቃሉ ለእግዚአብሔር ኢኮነ ቃሉ ለአብ ዘይትማሰል በአምሳለ ንባብ ዘይትከዐው ውስተ ነፍሰ ወኢይትማሰል ቃላተ እለ አልቦሙ አካል አላ ቃል ሕያው ውእቱ። እርሱ ግን ወልድ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የእግዚአብሔር ቃል ነው። የአብ ቃልም በነፍስ ላይ እንደሚፈስስ ንባብ በሚመስል አኳኋን የሚመሳሰል አይደለም። ደግሞ ሕያው ቃል ነው እንጂ፣ አካል እንደሌላቸው ቃላት የሚመሰል አይደለም»። ዲዮና ገጽ 439 ክፍል 1 ቍጥር 8።

ቄርሎስም፦ «ወለቃለ እግዚአብሔር ዘውእቱ እምህላዌ አብ ቡቱ አካል ጽኑዕ። ወለሊሁ ጥበብ ጎቡዕ ወወልድ ዋሕድ ዘቦቱ ኩሉ ኮነ፣ ወለሊሁ ፍጹም ፍጹመ ስብሐት ወኃይል በከመ ይደሉ ለዕበየ መለኮት ወኢየሐፅፅ በምንትኒ እምአብ ወመንፈስ ቅዱስ። ከአብ ባሕርይ የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ግን ፅኑዕ የሆነ አካል አለው። እርሱ ራሱም ሥውር ጥበብ ነው። ሁሉ በእርሱ የሆነ ወልድ ዋሕድም እርሱ ነው። ለመለኮት ታላቅነት እንደሚገባም በክብርና በኃይል ፍጹም የሆነና ራሱ ፍጹም ነው። ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ በምንም በማናቸውም ረገድ የሚጐድለውና የሚያንስበት ምክንያት የለውም»። ሃይ አበ ቄርሎስ ገጽ 74 ክፍል 1 ቍጥር 19።

ቴዎዶጦስ ዘዕንቁራም፦ «ወህየንተ ቃል ዘዝየ ነአምሮ ለቃለ እግዚአብሔር ከመ ቡቱ ህላዌ ወቡቱ አካል በፍጹም ገጽ ወበመልክዕ በከመ ገጸ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ እስመ ወልዱ ውእቱ ለአብ። ወሶበ ናስተግስሎ ለቃለ እግዚአብሔር በቃለ ዚአነ ኢይምሰልከ ዘአልቦቱ ገጽ ወኢህላዌ፦ ከዚህ ስላለው ቃል እንደ አባቱና እንደ መንፈስ ቅዱስ ገጽ ያለ በፍጹም ገጹና በመልክ ባሕርይ አካል እንዳለው የእግዚአብሔር ቃል እናውቀዋለን። የአብ ልጁ ነውና። የእግዚአብሔር ቃልን በእኛ ቃል ብንመስለው እንደኛው ቃል ገጽና ህላዌ የሌለው አይምሰልህ» ሃይ አበ ገጽ 74 ክፍል 1 ቍጥር 19።

ዮሐንስ አፈወርቅ ሐዋርያ ጳውሎስ በቃልነቱ ችሎት ሁሉን የሚይዝ ሲል የተናገረውን በግድነት ወስዶ ሲተረጕም፦

«ምንተ ይሜኒ በብሂሎቱ በቃለ ኃይሉ፣ እስመ ቃልሰ ቀሊል ውእቱ በጎበ ሰብእ። ወበእንተዝ ከሠተ ሐዋርያ ከመ ኢኮነ ከማሁ ቃለ እግዚአብሔር ልዑል ወአጠየቀ ከመ ውእቱ አጎዜ ኩሉ። በቃልነቱ ክሂል ማለቱ ምንኛ የሚያምር ገለጻ ነው። ቃል በሰው ዘንድ ቀላል ነገር ነውና። ስለዚህ የልዑል እግዚአብሔር ቃል እንደዚያ እንዳልሆነ እርሱ ሁሉን የሚችል እንደሆነ አስረዳ» ዮሐ አፈ ወርቅ ድርሳ 25 ገጽ 32።

እንግዲህ ቃለ አብ አካል ያለው ፍጹመ አካል መሆኑን ካስረዳን ዘንድ የአብ እስትንፋስ የተሰኘው መንፈስ ቅዱስም አካላዊና ፍጹመ አካል መሆኑን በሚያስረዳ ገለጻ እንነጋገር፡-

«አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ዘይረድኦሙ ለኩሎሙ ወይከፍሎሙ በከመ ፈቀደ። ሁሉን የሚረዳ እንደ ፈቃዱም ለሁሉ የሚከፍል አንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው»። መጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ በከዊነ እስትንፋስ ከአብ እንደወጣ ብቻ ቢያስቡና አካል እንደሌለው አድርገው ለሚያስቡት ወደ መሠረተ ትምህርቱ ጠልቀን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር እስትንፋስ አካላዊነት ምን ዓይነት ገለጻ እንደሚሰጥ ልናቀርብ እንወዳለን።

እነሆም ጌታችን በወንጌል፡- «ወአነ እስእሎ ለአብ ወይፈኑ ለክሙ ጸራቅሊጦስሃ ካልዐ ከመ ይንበር ምስሌክሙ፡- እኔም አብን እለምናለሁ ለዘለላም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል።» ብሎአል። ዮሐ. 14÷16።

ከዚህ ኃይለ ቃል ምንጭ በተለይ «ሌላ አጽናኝ» የሚለውን ቃል ብንመለከት የእግዚአብሔር እስትንፋስ ዝርው /ግውዝ/ ነገር ሳይሆን፣ አካል ያለው እንደሆነ ያስረዳናል።

ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በዚሁ ገለጻ ተስማምተዋል። ለምሳሌ፡- የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ዘካርያስ ይህን ቃል በሚተረጕምበት ጊዜ፡-

«ይትኀፈሩ እንከሰ ዝየ ይእዜ፥ አብስለዲስ ወመቅዶንዮስ እለ ኢይሁቡ ክብረ ወስብሐተ ለመንፈስ ቅዱስ። እስመ ብሂልሰ ካልዕ ዘከማየ ይከሥት ለነ ፍልጠተ አካላት»፡-

እንግዲህ አሁን እዚህ ላይ ለመንፈስ ቅዱስ ክብርና ምስጋና የማይሰጡ አብስለዲስና መቅዶንዮስ ይፈሩ ይኑሩ «እንደ እኔ የሚሆን ሌላ ማለቱ፥ አካላት ልዩ ልዩ መሆናቸውን ይገልጻልና።» ሲል አብራርቶአል። ሃይ አበ ዘካ ገጽ 493 ቊጥር 26 ክፍል 2።

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ቆዝሞስም እንደአባ ዘካርያስ ገለጻ አድርጎ ተርጕሞታል። /ሃይ አበ ቆዝሞስ ገጽ 416 ቊጥር 7።

ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የኢትዮጵያ ሊቃውት ትርጓሜም አባ ቆዝሞስና አባ ዘካርያስ እንደተናገሩት ሆኖ ይገኛል፡-

ይኸውም፡- «ካልዐ ሌላ» ባለው አንድ ገጽ የሚል ሰባልዮስ ይረታል። «ዘከማየ እንደ እኔ» የሚል አብነት ይገኛል። መንፈስ ቅዱስ ሕውፅ /አነስተኛ/ የሚል መቅዶንዮስ ይረታበታል» የሚል ነው። /ትርጓ ወንጌል ገጽ 483።/

ሆኖም ካልዐ /እንደ እኔ /የሚል በአንዳንድ የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ አብነት ተጠቅሶ ሲገኝ፣ በአብዛኛው ትርጕሙ አይገኝምና፣ እርሱን አቆይተን «ሌላ» ስለሚል ብቻ እንነጋገር።

«ሌላ» ስለሚል ቃልም ቢሆን፣ «ሌላ» መባሉ ከወልድ የተለየ መሆኑን እንጂ አካላዊ መሆኑን ላያሳይ ይችላል። «ሌላ» ሲባል ለአንድ ዝርው /ግዑዝ/ ነገርም ሊነገር ይችላል። በግለት «ሌላ» የሚል ቃል መንፈስ ቅዱስን በአካልነቱ ፍጹመ አካል ሊያሰኘው አይበቃም፣ የሚሉ ተጠራጣሪዎች አሉ።

ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ፍጹመ አካል ስለመሆኑ፥ «ሌላ» በሚል ቃል ብቻ ተናግሮ አላከተመም።

መንፈስ ቅዱስ በአንድ ፍጹመ አካልና በባለ ግዕዛን ፍጹመ አቋም ስለ መገኘቱ፥ በልዩ ልዩ ቦታ ሲነገርለት ተገኝቶአል።

እነሆም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመንፈስ ቅዱስን ሁኔታ ለሐዋርያቱ ሲገልጽላቸው፦

እስመ ኢይነግር ዘእምኀቤሁ ወዘሰምዐ ጸዕሙ ይነግር፦ ከራሱ አይናገርምና፣ የሰማውን ይናገራል እንጂ» ብሎአል። ዮሐ. 16፥13።

ይህ ጥቅስ «ሌላ» አጽናኝ ከሚል ጋር ሲተባበር፣ አካላት ልዩ ልዩ ስለመሆናቸው መንፈስ ቅዱስም በአካሉ እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹመ አካል ስለመሆኑና በተዋሕዶተ መለኮት ረገድም በህልውና አንድነት ከአብ ከወልድ ጋር ጸንቶ ስለመኖሩ የሚያብራራ ጥቅስ ነው።

እንደምን ቢሉ፦ አስቀድመን ስለተዋሕዶተ ሥላሴ በተናገርነው ትምህርታዊ ገለጻ «መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋስነቱ ሕይወት እንደሆነ በአብ ልብነት፥ በወልድ ቃልነት፥ ፍጹመ አካል ባለ ግዕዛን አካል ወይም ምልዐተ አካል ነው።» ስንል ያቀረብነው ሙሉ አሳብ እዚህ ላይ በድጋሚ ጥቅሱ ያዘለውንም ምሥጢር ሊተረጕምልን ይችላልና ነው።

እነሆም ወደ ቃላቱ አቀማመጥ ይዞታ ብናተኵር፣

ሀ፥ «ከራሱ አይናገርም» የተባለበት ነባቢነቱ በወልድ ቃልነት መሆኑን እያስረዳ፦

ለ፥ «የሰማውን ይናገራል።» የተባለበትም በአብ ልብነት ወይም ዕውቀትነት ያወቀውን በወልድ ቃልነት እንደሚነገር እየገለጸ፣

ሐ፥ «ከራሱ» እያለ የሚጠቀመውም ፍጹመ አካል ሆኖ በአካልነት ጽንዕ ቀዋሚነቱን ስለሚያስገነዝብ ነው።

የሀገራችን ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም፦

«ዓዲ ከመ ኢንበል ኢሀሎ መንፈስ ቅዱስ በአካሉ ፍጹም ትቤሎሙ ለሐዋርያቲከ እፈኑ ለክሙ ካልዐ ጸራቅሊጦስ። ወበዝ አእመርነ ከመ ህልው መንፈስ ቅዱስ ኀበ አብ ወወልድ፥ ለህልው ካዕበ በህላዌሁ። አኮ ዘይትከፈል መንፈስ ቅዱስ ኀበ አብ ወወልድ ወኀበ ህላዌሁ ካዕበ። አላ አሐዱ ውእቱ ህልውኒ በህላዌሁ ወህልውኒ ኀበ አብ ወወልድ።»

መንፈስ ቅዱስ ፍጹም በሚሆን አካሉ፥ መንፈስ ቅዱስ የለም እንዳንልም ደግሞ፥ ለሐዋርያትህ ሌላ ጸራቅሊጦስ እልክላችኋለሁ ብለሃቸዋል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ በራሱም ህልው እንደሆነ ዐወቅን። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ ወደ አብና ወደ ወልድ ወደ ራሱም ህላዌ የሚከፈል አይደለም። ነገር ግን እርሱ ራሱ አንድ ሆኖ በህላዌው ጸንቶ በአብና በወልድ ህልው ነው» አባ ጊዮ. አርጋኖን ዘቀዳሚት።

ከዚሁም ጋር መንፈስ ቅዱስ ፍጹመ አካል ስለመሆኑ የሚያስረዳ፥ ሐዋርያ ጳውሎስ የሰጠውን ማስረጃ እንመለከታለን።

«ወለኩሉ ዝንቱ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ዘይረድአሙ ለኩሎሙ ወይከፍሎሙ በከመ ፈቀደ፡- ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ ቅዱስ እንደሚፈቅድ እያደለ ለእያንዳንዱ ይከፍለዋል። 1ቆሮ. 12÷11። እዚህ ላይ የተጠቀሰው በተለይም እንደሚፈቅድ ወይም እንደወደደ አድርጎ ለእያንዳንዱ ስጦታን የሚያከፋፍል» ሲል፤ በመንፈሳዊ ምልዐተ አካል የሚገኝ ባለ ግዕዛን ወይም ፍጹመ አካል መሆኑን እንጂ፤ ዝርው ወይም ግውዝ ነገር መሆኑን አያሳይም። መቼም ዝርውን ወይም ግውዝን ነገር የፈቀዱትን የወደዱትን ያደርጉበታል እንጂ፥ የፈቀደውን የወደደውን ለማድረግ አይችልም። ፈቃድ ሥምረት የለውም፡-

እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ ፈቅዶ ሠምሮ የፈቀደውን የወደደውን ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ፥ ፍጹመ አካል መሆኑን ያስገነዝባል።

ይህንን የተረዳ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፡- ጳውሎስ የተናገረውንና ጌታ በወንጌል የተናገረውን በማስገንዘብ፤ መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔራዊ አካል መሆኑን አስረድቶአል።

«አሐዱ ውእቱ እግዚአሔር መንፈስ ቅዱስ መንፈሰ አብ ወወልድ ዘይነፍሕ ኀበ ፈቀደ።

መንፈሰ አብና መንፈሰ ወልድ የሚሆን ወደ ወደደው ወደ ፈቀደው የሚነፍስ አንዱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው» አለ። 1ቆሮ. 12÷6፤ 11። ከዮሐ. 3÷8 ጋር አገናዝብ፡- /ሃ.አበ.ገጽ 74 ክፍል 4 ቍጥር 2።

ባስልዮስ ዘቂሣርያም፡- «ወዝንቱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ዘይሄሉ ላዕለ ኩሉ፤ ወውእቱ ኩለንታሁ ህልው ላዕለ ኩሉ አሐዱ አሐዱ ለዘይትዌከፎ ወውእቱ ኩለንታሁ። ህልው በእግዚአብሔር አብ፥ ወበእግዚአብሔር ወልድ፥ እስመ መንፈሶሙ ውእቱ። አኮ ዘይሁብ ህብታተ ከመላእክት፤ አላ ውእቱ እግዚአብሔር ይሁብ ህብታተ ወይሰፍሕ ወየሐውር በከመ ሥልጣኑ። በሁሉ ዘንድ የሚኖር መንፈስ ቅዱስ ይህ ነው። እርሱ ሁለመናው በሚቀበለው በእያንዳንዱ ሁሉ ይኖራል። እርሱ ሁለመናው በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ ህልው ነው፤ መንፈላቸው ነውና። ስጦታዎችን ሲሰጥም እንደ መልእክተኛ ሆኖ አይደለም። ነገር ግን እርሱ ራሱ እግዚአብሔር እንደመሆኑ ስጦታዎችን ይሰጣል። እንደወደደም ለሁሉ ጸጋውን ያከፋፍላል። በሥርዓቱም እንደ ሥልጣኑ ይዘረጋል /ይሞላል/ ይሄዳልም»። ባስ. ዘቂሣ ሃ. አበ. ገጽ 114፤ 115 ክፍል 4 ቍጥር 44-49። ዘፍጥ. 1÷2። ማቴ. 3÷17። ሉቃ. 1÷35። መዝ. 138÷7። 1ቆሮ. 12÷6፤ 11።

ዳግም፡- «እስመ መንፈስ ቅዱስ ህልው በአብ ወወልድ አለ አልቦሙ ጥንት ወኢተፍጻሜት ወኢይትኤለቍ ምስለ ብዙኃን። ኢተአምሩኑ ከመ ሥሉስ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ በህላዌ መለኮት፤ ወኢይትማሰል በብዙኃን በከመ አብ አሐዱ ውእቱ በህላዌ መለኮት ከማሁ መንፈስ ቅዱስኒ አሐዱ ውእቱ... ዝንቱ ውእቱ ንጉሠ መላእክት ወሊቃነ መላእክት ወይ አኀዝ ጎይላተ ወያነጽሕ ኩሎ ወይመልክ ኩሎ ፍጥረተ።

መነሻና ፍጻሜ በሌላቸው በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። ከሌሎች ከፍሎች የሚቈጠር አይደለም። የሥሉስ ቅዱስ ህላዌ መለኮት አንድ እንደሆነ አታውቅምን? ከሌሎች እንደማይቈጠርስ ታውቁ የለምን? እንግዲያውስ መንፈስ ቅዱስ እንደዚሁ አንድ ነው። አብ አንድ እንደሆነ፤ ወልድም አንድ እንደሆነ፤

ከሌሎችም እንደማይቈጠር፥ መንፈስ ቅዱስም አንድ ነው እንጂ ከብዙዎች እንደ አንዱ አይቈጠርም... እርሱ የመላእክትና የሊቃነ መላእክት ንጉሥ ነው። ኃይላትንም የያዘ ሁሉን የሚረዳ፥ ፍጥረትንም ሁሉ የሚገዛ ነው»። ብሎአል። ባስል ዘቂሣ ሃ. አበ. ገጽ 114 ክፍል 4 ቍጥር 44-46።

ምንም እንኳ ቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ስፍራ ፀአቱን /አወጣጡን / በሚያስረዳ ሁኔታ ለመግለጽ ሲሉ፤ መንፈስ ቅዱስ በኩነት ስሙ «የእግዚአብሔር እስትንፋስ» እያሉ ቢናገሩም ቅሉ፥ «የእግዚአብሔር እስትንፋስ» አካል የሌለው ዝርው /ግዑዝ/ ነገር፥ ወይም ግቡር /የተሠራ/ እንዳልሆነ ገልጸው ከማስረዳታቸው፥ የተቈጠቡበት ቦታና ጊዜ የለም። መዝ. 2፥5፤6። 1ተሰ. 4፥8።

አስቀድመን እንደገለጽነው «እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ» ፈቃድ ስላለው የፈቀደውን ለማድረግ የሚችል መሆኑን እያስታወስን፤ እንደዚሁም ሁሉ የሚከተሉትን ሲፈጽም መገኘቱን መጽሐፍ ቅዱስ ያብራራል።

ምዕራፍ ሃያ።

መንፈስ ቅዱስ በሚከተሉት ግብራት ሁሉ ይገኛል።

መንፈስ ቅዱስ ይሰበስባል።	ኢሳ. 34፥16።
መንፈስ ቅዱስ ይፈጥራል።	ኢዮብ 33፥4።
በመንፈስ ቅዱስ ሰማያት ውበትን አገኙ።	ኢዮብ 26፥13።
መንፈስ ቅዱስ ወደ ዕረፍት ያመጣል።	ኢሳ. 63፥10።
መንፈስ ቅዱስ ይጠብቃል።	ኢሳ. 11፥1-10።
መንፈስ ቅዱስ ይሰጣል።	የሐዋ. 4፥4።
መንፈስ ቅዱስ ያድላል።	1ቆሮ. 12፥16። የሐዋ. 13፥2።
መንፈስ ቅዱስ ያካፍላል።	1ቆሮ. 12፥11።
መንፈስ ቅዱስ ይቀድሳል።	1ቆሮ. 6፥11። 2ተሰ.2፥13።
መንፈስ ቅዱስ ያነጻል።	1ቆሮ. 6፥11።
መንፈስ ቅዱስ ያድራል።	1ቆሮ. 6፥19፤20። ም. 3፥16።
መንፈስ ቅዱስ ይመራል።	ዮሐ. 16፥13። ሚክ. 2፥7።
መንፈስ ቅዱስ ይታገሣል።	ሮሜ 15፥13፤ 14።
መንፈስ ቅዱስ ያጽናናል።	ዮሐ. 15፥26።
መንፈስ ቅዱስ ያስተምራል።	ዮሐ. 14፥26።
መንፈስ ቅዱስ ያሳስባል።	ዮሐ. 14፥26።
መንፈስ ቅዱስ ይቈጣል።	ኤፌ. 4፥30።
መንፈስ ቅዱስ ውሸትን ይጠላል።	የሐዋ. 5፥3-4።
መንፈስ ቅዱስ ይዘልፋል።	ዮሐ. 16፥8፤9።

መንፈስ ቅዱስ ይፈርዳል።	ኢሳ. 4፥4። ም. 28፥6። ዮሐ. 16፥11።
መንፈስ ቅዱስ ለአምላክነቱ ይቀናል።	ማቴ. 12፥32።
መንፈስ ቅዱስ ይሸከማል።	የሐዋ. 20፥28።
መንፈስ ቅዱስ ይመሰክራል።	ዮሐ. 16፥26። ዮሐ. 20፥23።
መንፈስ ቅዱስ ይናገራል።	ማር. 13፥16። የሐዋ. 28፥25።
መንፈስ ቅዱስ የሚሰማውን ይናገራል።	ዮሐ. 16፥13።
መንፈስ ቅዱስ የሚመጣውን ይናገራል	ዮሐ. 16፥13፤ 14።
መንፈስ ቅዱስ ያዝዛል።	የሐዋ. 16፥13፤ 14።
መንፈስ ቅዱስ ይጸልያል።	ሮሜ 8፥26፤ 27።
መንፈስ ቅዱስ ያዝናል።	ኢሳ. 63፥10።
መንፈስ ቅዱስ ይመረምራል።	1ቆሮ. 2፥10።

በዚህና በሚመሳሰለው ሁሉ አንድ በምልዐተ አካል የሚኖር፥ ባለ ግዕዛን ፍጹመ አካል የሚያደርገውን እነሆ፥ መንፈስ ቅዱስ ሲያደርግ መገኘቱን እንገነዘባለን።

እንዲህ ዓይነቱን ግብር ሊያመነጭና ሊያስገኝ የሚችል በለባዊነት፥ በነባቢነት፥ በሕያውነት ባለ ግዕዛን ፍጹመ አካል መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት አሳብ ታውቆ ያደረ አይደለምን?

በትምህርተ መለኮት አባባል በረቂቅነት ማለት በመንፈስነት አቋም ለሚኖር አንድ ህሉና «የምልዐተ አካል አቋም አለው ወይም ባለግዕዛን ነው፤ ወይም ፍጹመ አካል ነው።» የሚባልበት መሠረታዊ ፈሊጥ፥ ለባዊ፥ ነባቢ፥ ሕያው ሆኖ እላይ የተጠቀሱት ከባለ ግዕዛን የሚመነጩትን ግብራት ሲያስገኝ መሆኑ ዋና ማስረጃ ነው።

እነሆም መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ለባዊ፥ በወልድ ቃልነት ነባቢ፥ በራሱ እስትንፋስነት ሕያው ሆኖ ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች ሲፈጽም በመገኘቱ ዝርው /ግውዝ/ ነገር ሳይሆን፤ በመንፈሳዊ ምልዐተ አካል የሚኖር ፍጹመ አካልና ባለ ግዕዛን መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።

ስለዚህም ነገር ሊቁ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ሲያስረዳ፡- «ወህየ በውእቱ መካን ንኄጽሮ ለመንፈስ ቅዱስ በመካን ዘሀለዉ ቦቱ አብ ወወልድ። ወሎቱ ኩሉ ዕብየ መለኮት ዘሀሎ በአብ ወወልድ ዘውእቱ ምሕረት ወሣህል አእምሮ ወቅድሳት ወሕይወት ወንጽሕና... ሃ አበ. ባስልዮስ ዘቂሣርያ ገጽ 114 ክፍል 4 ቍጥር 39።

ወዝንቱ ንባብ ዘተናገርነ በእንቲአሁ አልቦ ውስቴቱ ፍድፋዴ ወኢኮነ ሎቱ ድኅረ። ወባሕቱ በከመ ነበልባል ኢይትፈለጥ እምእሳት ወኢይትፈለጥ ፀዳል እምብርሃን፤ ከማሁ ንጽሕና ወሕይወት ወምሕረት ወአእምሮ ኢይትፈለጥ እምነ መንፈስ ቅዱስ። እስመ መንፈስ ቅዱስ ህልው ውእቱ በአብ ወወልድ አለ አልቦሙ ጥንት ወኢተፍጻሜት።

ከዚያ አብና ወልድ ባሉበት ቦታም መንፈስ ቅዱስን እናየዋለን። ይኸውም፡- የመለኮት ክብር የሚሆን በአብና በወልድ ያለው ምሕረት፥ ይቅርታ፥ ዕውቀት፥ ቅድስና፥ ሕይወት፥ ንጽሕናም ሁሉ ገንዘቡ ነው።...

አስቀድሞ ስለ እርሱ የተናገርንለት ነገርም ትርፍ ጭማሪ የለበትም። ኋላም የመጣለት አይደለም። ነገር ግን፤ ነበልባል ከእሳት፥ ፀዳልም /ነጸብራቅም/ ከብርሃን

እንደማይለይ ሁሉ፥ እንዲሁም ንጽሕና፥ ሕይወት፥ ምሕረትና፥ አእምሮ ከመንፈስ ቅዱስ አይለይም። መንፈስ ቅዱስ መነሻና መድረሻ በሌላቸው በአብና በወልድ ህልው ነውና»። በማለት አስረድቶአል።

/ሃይ አበ. ባስል ገጽ 114 ክፍል 4 ቍጥር 30-34።/

አትናቴዎስ ሐዋርያዊም፦ «ወነአምሮ ለመንፈስ ቅዱስ ከመ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ፍጹም ዘከመ ዕበየ ባሕርየ አብ ወወልድ በገጹ ወበአካሉ ወበመልክዑ፦

መንፈስ ቅዱስ በገጹ፥ በአካሉ በመልኩ እንደ አብና እንደ ወልድ የባሕርይ ክብር እንዳለውና ፍጹም አምላክ እንደሆነ፣ መንፈስ ቅዱስን እናውቀዋለን።» ብሎአል።

/ሃይ አበ. አትናቴ ገጽ 85 ክፍል 14 ቍጥር 14።/

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ዘካርያስም፦

«ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ዘሠረፀ እምአብ ወዘስንዕው ምስለ አብ ወወልድ ወቡቱ አካል ፍጹም ከመ አብ ወወልድ፦

ከአብ በሠረፀና ከአብና ከወልድ ጋር አንድነት ባለው በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። እርሱም እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹም አካል ያለው ነው።» ብሎአል። /ሃይ አበው ዘካርያስ ገጽ 491 ክፍል 1 ቍጥር 20።

ጎርጎርዮስ ዘደሴያትም፦

«እሰመ አብ ህልው በአካሉ ወበገጹ፥ ወወልድኒ ህልው ከማሁ በአካሉ ወበገጹ፥ ወመንፈስ ቅዱስሂ ህልው በአካሉ ወበገጹ። ወዓዲ ነአምን በመንፈስ ቅዱስ ከመ ውእቱ ዕሩይ ምስለ አብ ወወልድ ወአኮ ነኪር ውእቱ እምህላዌ መለኮተ አብ ወወልድ ሐሰ።

አብ በአካሉና በገጹ ህልው ነውና ወልድም በአካሉና በገጹ ህልው ነውና መንፈስ ቅዱስም በአካሉና በገጹ ህልው ነውና።

ዳግመኛም ከአብ ከወልድ ጋር እኩል መሆኑን እናምናለን። ከአብ ከወልድ ባሕርየ መለኮት ውጭ አይደለምና። መቼም መች እንዲህ አይሆንም»። ሲል አባ ዘካርያስ ተናግሮታል። /ሃ.አበ. ገጽ 491 ክፍል 1 ቍጥር 20።/

ቴዎዶስዮስ ዘእስክንድርያም ስለ መንፈስ ቅዱስ አካል ሲናገር፦ «ወካዕበ አጤይቅ ካልዐ አካለ ዘውእቱ አሐዱ ዘእምቅድስት ሥላሴ ዘውእቱ መንፈስ ቅዱስ እግዚእ ግሕየዊ ዘወፅአ እምአብ ዘይሴባሕ ዘልፈ በአሐዱ ዕሪና ምስለ አብ ወወልድ።

ዳግመኛም ስለ ሌላ አካል አስረዳለሁ። ይኸውም በቅድስት ሥላሴ ካሉት ስለ አንዱ አካል እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም ከአብ የወጣ አዳኛና ጌታ ነው። እርሱም ዘለዓለማዊ ከአብና ከወልድ ጋር በእኩልነት የሚመሰገን ነው» ብሎአል።

ሃይ አበ ቴዎዶስዮስ ገጽ 356 ክፍል 3 ቍጥር 43።

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ክርስቶዶሉም፦ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካል ተናግሮአል።

«ወመንፈስ ቅዱስሂ ወፅአ እምአብ ውእቱ እምቅድመ ኩሉ መዋዕል ህልው ውእቱ እስከ ለዓለም በአካሉ ወበገጹ። ወሎቱ ሥርዓተ መንፈስ ቅዱስና፦ መንፈስ

ቅዱስም ከአብ የወጣ ነው። ከዘመናት አስቀድሞና ለዘላለም በአካሉ በገጹ ይኖራል። በራሱ በመንፈስ ቅዱስነት ሥርዓታዊ አቋም ይኖራል»።

አበ ዘአክርስቶዶሉስ ገጽ 526 ክፍል 1 ቍጥር 2።

እነሆም እስከዚህ ድረስ፥ መንፈስ እግዚአብሔር በመንፈስነት /በረቂቅነት/ ለሚኖር አንድ ሀሉና የምልዓተ አካል አቋም አለው። ባለ ግዕዛን ነው። ፍጹመ አካል ነው» በሚያሰኝ በለባዊነቱ፥ በነባቢነቱ በሕያውነቱ ምንጭነት በሚያስገኛቸው ግብራት እንደ አብና እንደ ወልድ ያለ የሚሆን፣ ፍጹምም አካል ያለው መሆኑን በሚያስገነዝብ ትምህርታዊ ማስረጃ ተመለከትን።

አሁን ደግሞ አካል ቋመት ነው በሚያሰኝ ማስረጃ፥ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት ለመግለጽ እንወዳለን።

አካል ማለት አለ ሊሉት የሚቻል ቋመት ነው። ሲሉ በሚያውጁት የፈሊጥ ትርጓሜ መሠረትም ቢሆን፣ መንፈስ ቅዱስ አምላካዊ ረቂቅ መንፈስ ሲሆን፣ ሳይወሰን በምልዓት የሚኖር ነውና፣ በዚህም ረገድ ምልዓተ አካል አቋም ያለው ፍጹመ አካል ሆኖ ይገኛል። /መጽ ምዕላድ/ ገጽ 3።

እነሆም በመዝሙር ዘዳዊት፡- «አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ ወአይቴ እጐይይ እምቅድመ ገጽከ እመኒ ዐረጉ ውስተ ሰማይ ህየኒ አንተ፤ ወእመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ።»

«ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ፤ ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ፤ ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ ከዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ»። መዝ. 138፥7፣8። ተብሎ ተነግሮአል። በዚህም የእግዚአብሔር መንፈስ በምልዐትና በርቀት የማይገኝበት ቦታ አለመኖሩ ተገልጾአል። ሐጌ. 2፥5።

አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፡- «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ዘይመልዕ ኩሎ ወየሐውስ ኩሎ ወውእቱ ውስተ ኩሉ ወይነፍሕ ውስተ ኩሉ እንዘ ኢያስተርኢ ወውእቱ መንፈስ አብ ወወልድ። ማሕየዊ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፤ እርሱ ሁሉን የሚሞላ፥ ሁሉን የሚያገናኝ፣ በሁሉም ዘንድ የሚገኝና ሳይታይም ወደ ሁሉ የሚነፍስ ነው። እርሱም የአብና የወልድ መንፈስ ነው»። ሲል ምልዓቱን ርቀቱን በሚያጠቃልል ገለጻ አስረድቶአል። ሃይ አበ አትናቴዎስ ገጽ 84 ክፍል 14 ቍጥር 6።

«ወደ ወደደው የሚነፍስ፥ ሳይታይ ወደ ማናቸውም የሚነፍስ» ስለ ተባለም እንደ አየር፥ እንደ ነፋስ ግዑዝ ወይም ዝርው ነገር ሳይሆን፣ ራሱ በፈቀደውና በወደደው መልክና ሁኔታ ሲገለጽ መገኘቱን ከሚከተሉት ጥቅሶች የሚገኘውን ገለጻ ማስተዋል ነው። ማቴ. 3፥17። የሐዋ. 2፥2። ዘፍጥ. 1፥2።

ስለዚህም ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ሰጥቶአል። «ውእቱኒ /መንፈስ ቅዱስ/ ዓዲ በአሐዱ ህላዌ ወበአሐዱ ክብር ምስለ አብ ወወልድ፤ ወአኮ ዘከመ እስትንፋስ ዘሀሎ ውስቴትነ ዝንቱ ዝንስሕቦ ኀቤነ እምነፋስ ለቋመተ ሥጋነ፤ ወባሕቱ ነአምን ጥዩቀ ከመ ውእቱ መንፈሰ እግዚአብሔር። ዝንቱ ዘኮነ ቃል ስምዐ በእንቲሁ ወከሠተ ግብሮ አመ ፈነዎ ላዕለ ሐዋርያቲሁ ዘከመ ነበልባል እምዝንቱ አሐዱ ህላዌ እምዘቦቱ አካል ወይትአመር በዘዚአሁ። ዮሐ. 3፥4-8። የሐዋ. 2፣2-19። ም. 4፥31። እርሱ /መንፈስ ቅዱስ/ ከአብና ከወልድ ጋር በባሕርይ አንድ ነው። በክብርም አንድ ነው። እርሱ ለቋመተ ሥጋችን /ለሰብአዊ ህሉናችን/ ወደ እኛ እንደምንሰበውና አውሰጣችን እንደሚገኝ እስትንፋስ አይደለም። ነገር ግን እርሱ

የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ በእርግጥ እናምናለን። እርሱ ቃል ስለ እርሱ የመሰከረለትና አካል ካለውም ከዚህ አንድ ባሕርይ በነበልባል አምሳል ወደ ሐዋርያት በላከው ጊዜ ሥራውን የገለጠ በራሱ አቋምም ነው»።

ሃ. አበ. ዲዮና ገጽ 440 ክፍል 1 ቍጥር 10።

ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስም፦ «ወለምንት በአምሳል ይቤ መድኅን ለአርዳኢሁ እፈኑ ለክሙ ጰራቅሊጦስሃ ዘውእቱ መንፈስ ቅዱስ ዘይመልዕ ኩሎ ወበእንተዝ ለሊሁ ይቤ ከመ መንፈሰ እግዚአብሔር ይመልዕ ኩሎ ዓለመ እንዘ ኢይወፅእ እምዕበየ መለኮቱ ወኢይትመየጥ እምህላዌሁ። ወውእቱ ከመ መንፈሰ እግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም»።

መድኃኒታችን ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉን የሚመላ መንፈስ ቅዱስ የሚሆን ጰራቅሊጦስን እልክላችኋለሁ ሲል በአምሳል ለምን ተናገረ? ስለዚህ ራሱ ጌታ ከልዕልና መለኮቱ ሳይወጣና ከህላዌውም ተናገረ። እርሱ ነው ፈጽሞ ለዘላለሙ የእግዚአብሔር መንፈስ የሆነ።» ሃይ አበ ቄር ገጽ 320 ክፍል 50 ቍጥር 17። ሠለስቱ ምእትም አጠቃለው ሲደመድሙ።

«እስመ አብ ኢይትረከብ፣ ወወልድ ኢይትረከብ ወመንፈሰ ቅዱስ ኢይትረከብ ወኢይትአመር ወኢያገምሮ መካን ወውእቱ መንፈሰ እግዚአብሔር ዘበአማን ወአኮ በሕሊና ወበሥምረት።

አብ አይወሰንም፤ ወልድም አይወሰንም፤ መንፈስ ቅዱስ አይወሰንም፤ አእምሮ አይደርስበትም። ቦታም አይመስነውም አይችለውም። እርሱ ነው የእግዚአብሔር እውነተኛ መንፈስ ይህም በሕሊናና በስሜት አይደለም።» ብለው አስረድተዋል። ሃይ አበ ዘሰለስቱ ምእት ገጽ 54 ክፍል 2 ቍጥር 30፣31።

ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ፦

«ወነአምን በመንፈሰ ቅዱስ ነባቢ በውስተ ሕግ ወሰባኪ በነቢያት ዘወረደ በዮርዳኖስ ወተናገረ በሐዋርያት ውኅደረ በቅዱሳን ወነአምን ቦቱ ከመውእቱ ህላዌ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም ጰራቅሊጦስ ዘኢተፈጥረ ዘሠረፀ እምአብ ወነሥአ እምወልድ። በሕግ ተናጋሪ በነቢያት በኩልም ሰባኪ በዮርዳኖስ የወረደ በሐዋርያት የተናገረ በቅዱሳን ያደረ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። እርሱም አንድ አካል ህላዌ እንደሆነ እናምንበታለን። እርሱ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም ጰራቅሊጦስ እንደሆነና እንዳልተፈጠረ ከአብ የሠረፀ ከወልድም የሚወስድ እንደሆነ እናምንበታለን።» ብሎአል።

ኤጲፋንዮስ ሃይ አበ. ገጽ 193 ክፍል 11 ቍጥር 30።

እዚህ ላይ እንደተመለከትነው፥ ለአብ ባለው አካል መጠን ቃልና እስትንፋስ እንደ አብ ፍጹማን አካላት መሆናቸውና ባለ ግዕዛን ምልዐት ያላቸው አካላት በመሆን ፍጹምነት እንዳላቸው በብዙ ማስረጃዎች መረጋገጡን ይገነዘቧል።

እነሆም በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት የሰባልዮስና የመርቄሎስ የሰብልያኖስም አፈንጋጭ አሳብ ውድቅ መሆኑን በቀላሉ ለማየት እንችላለን።

አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፦ «ወኢንክህድ ሠለስተ አካላተ ከመ ፎጢኖስ ወመርቅሎስ ርጉማን እለ ኢየአምኑ በአስማተ ሠለስቱ አካላት ወኢናሰትት አሐተ መለኮተ ዘሥሉስ ቅዱስ ከመ ከህደ አርዮስ።

ወባሕቱ ንለቡ በርትዕ ዕበዮ ለመለኮት ወንትአመን በሠለስቱ አካላት ወኢንክህድ ግሙራ አሐደ መለኮተ ዘቅድስት ሥላሴ።»

«በሦስቱ አካላት አስማት እንደማያምኑና ርጉማን እንደሆኑ እንደ ፎጢኖስና እንደ መርቅሎስ አንካድ። የሥለስ ቅዱስ መለኮትንም እንደ አርዮስ አንከድም። አንድ መለኮትን አናቃልልም።

ነገር ግን በቅንነት የመለኮትን ታላቅነት እናስተውል። በሦስቱ አካላትም እንመን። የቅድስት ሥላሴ አንድ መለኮትንም ፈጽመን አንካድ። ያለንን ምክር በመከተል እምነታችንን ማጽናት እንደሚኖርብን የተገባ ነው»።

ሃይ አበ አትናቴ ገጽ 15 ክፍል 4 ቍጥር 13፣ 14።

እስከዚህ ድረስ ስለ ወልድና ስለመንፈስ ቅዱስ ባሕርያውያን አካላት ስለመሆናቸው በዝርዝር የተናገርነውን ተገንዘብን።

ቃልና እስትንፋስ ከልብ እንደሚወጡ ሁሉ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስም በከዊነ ቃልና በከዊነ እስትንፋስ ከአብ ልብነት ስለ መውጣታቸውና አወጣጣቸውም፥ ባሕርያዊ በመሆኑ ሦስቱም ሁሉ እያንዳንዳቸው አካላውያን በእየአካላቸው ፍጹማን ስለ መሆናቸው፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት መረጋገጡን ነበረ።

አሁን ደግሞ ስለዚህ ሁሉ ሐተታ የተሰጠውን ማብራሪያ ከቤተ ክርስቲያን አበው በማስተዋል እንመራበት ዘንድ ብንመለከት አይከፋም።

እነሆም ዐረጋዊ መንፈሳዊ፦ «እሉ እሙንቱ አካላት ዕሩያን እለ አልቦሙ ጥንት ወኢ ፍጻሜ ወኢሀገር ወኢመካን ወኢዓለም ወኢዘመን አብ ህልው በአካሉ ወልድኒ ወመንፈስ ቅዱስ ህልዋን ቦቱ እንዘ ይሄልው ካዕበ በበአካሉሙ። እነዚህም አካላት በዕሪና የተተካከሉ ናቸው። መነሻና ፍጻሜ /መጨረሻም/ የላቸውም። አገርና ቦታም የላቸውም። ዓለምና ዘመንም አይወስናቸውም። አብ በአካሉ ህልው ነው፤ ወልድና መንፈስ ቅዱስም በየአካላቸው እንደሆኑ በእርሱ ህልዋን ናቸው»። ብሎአል። ዐረጋዊ መንፈሳዊ ገጽ 116 ድርሳን 12።

አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፦ «ዝንቱ ሥላሴ ቀዳማዊ በገጻት ወበአካላት ወበመልክዓት ነአምሮ ለአብ በከመ አብ ፍጹም አምላክ ዘበአማን በገጹ ወበአካሉ ወበመልክዑ ወኢይትረከብ በከመ ስምዐ ኮኑ መጻሕፍት። ወነአምሮ ለወልድ ከመ ውእቱ ወልድ ፍጹም አምላክ ዘበአማን ወቦቱ ኩሉ ዘተናገርነ በእንተ አብ እምህላዌሁ ውእቱ ወኢየአምር ካልዐ አበ ዘእንበሌሁ። ወውእቱ አሐዱ ገጽ እምሠለስቱ በአካሉ ወበመልክዑ በኩሉ፦ ወነአምሮ ለመንፈስ ቅዱስ ከመ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ፍጹም ዘከመ ዕበየ ባሕርየ አብ ወወልድ በገጹ ወበአካሉ ወበመልክዑ፦ ይህ ሥላሴ በገጻት በአካላትና በመልክዓት ቀዳማዊ ነው። አብ ፍጹምና የእውነት አምላክ እንደሆነ በገጹ በአካሉ በመልኩ አብን እናውቀዋለን፦ በዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደመሰከሩት የማይወሰን ነው። ወልድም እርሱ ፍጹም እውነተኛ ልጅ እንደሆነ እናውቀዋለን፤ ስለ አብ የተናገርነው ሁሉ የእርሱ ነው። ከባሕርዩ ነውና፣ ከእርሱ በቀርም ሌላ አባት አያውቅም። እርሱ ከሦስቱ አንዱ ገጽ ነው። በአካሉ በመልኩ በሁሉም ከሦስቱ አንዱ እርሱ ነው። መንፈስ ቅዱስንም እናውቀዋለን። እርሱ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናውቀዋለን። በገጹ በአካሉ በመልኩም እንደ አብና እንደወልድ የባሕርየ ልዕልና ፍጹም አምላክ ነው።» እያለ ያጠቃልላል።

ሃይ አበ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ገጽ 85 ክፍል 12 ቍጥር 12-14።

እነሆም የወልድ ጸአት ከአብ መሆኑን፤ የመንፈስ ቅዱስንም ጸአት ከአብ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ አረጋግጦ ገልጾአል። ዮሐ. 16፥28። ም. 15፥26።

ከዚህም መሠረት ጸአት /መውጣት/ የሚል ቃል ከአብ የወጡትን /ወፃእያኑን/ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን የሚያስተባብር ሆኖ ተገኝቶአል ማለት ነው።

እንግዲህ ጸአት /መውጣት/ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን የሚያስተባብር ከሆነ ዘንድ፥ የቃልና የእስትንፋስ ከዊንም ጭምር ምንም ልዩነት በማያሳይ ሁኔታ ሸፍኖ ይወሰናል።

የሁለቱም አወጣጥ አንድ ዓይነት ፍቺና ምሥጢር ያዘለ ነው ለማለት ያስችላልን? «/መውጣቱ/ የቃልና የእስትንፋስ ከዊን ሳይለይ አጠቃሎ አንድ ፍቺ አድርጎ በማሳየት ይወስናልን?» የሚል ጥያቄ ይኖራል።

በእውነቱ ይህን ጥያቄ ሊያስከትል የቻለ ስለ ጸአት /መውጣት/ የተነገረውን ብሂላዊ ገለጻ በአንድ መንገድ ወይም መልክ በመውሰዱ ነው። ሆኖም እንደዚህ አይደለም። የአባባሉን ፈሊጥ ጠንቅቆና ለይቶ ማወቅ ይገባል።

ርግጥ ነው፥ ጸአት ሲባል ቃልና እስትንፋስ ከምንጫቸው /ከመገኛቸው/ ከአብ በአንድ ህልውና መኖራቸውን ከአንዱ መለኮተ አብ ወይም ከባሕርዩ መገኘታቸውን፤ ይህም ማለት ተረክቦአቸውን በሚያሳይ ሁኔታ ሲነገር፥ አነጋገሩ ሁለቱን አገናችቶአቸዋልና ነው።

በመሠረቱም የመለኮትን ተዋሕዶም ፀአቱ /መውጣቱ/ ነው ሊያብራራው የቻለ። በምሥጢር ረገድም ቢሆን፤ ጸአት /መውጣት/ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ከአንድ ከአብ ምንጭ መውጣትን ወይም ተረክቦን /መገኘትን/ ባያስገነዝብ ኖሮ፥ የቅድስት ሥላሴ ተዋሕዶተ መለኮትን ለመረዳት ባልተቻለም ነበር። ይህም ይታወቅ ዘንድ፦ ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፦

«እንእመን በሃይማኖት ከመ የትዋሕድ መለኮት በአብ እስመ አምአብ ተወልደ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወፅአ እምኔሁ እንዘ ኢይቀድም አሐዱ እም ካልዑ ወካልዑ እምሣልሱ ወበልደተ ወልድ ወጸአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትዋሐድ መለኮተ ሥላሴሁ ለአምላክነ።»

መለኮት በአብ እንደሚዋሐድ በሃይማኖት እንመን። ይኸውም ወልድ ከአብ እንደሚወለድ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ወጥቶአልና ነው። አንዱ ከሁለተኛው ሁለተኛውም ከሦስተኛው ሳይቀዳደሙ፥ ወልድ ከአብ በመወለድ፥ መንፈስ ቅዱስም ከአብ በመውጣት የአምላካችን የሦስትነቱ መለኮት ይዋሐዳል።» ሊል ያብራራውን በጥንቃቄ ማስተዋል የሚገባ ነው። ሃ. አበው ባስልዮስ ዘቂሣር ገጽ 17 ክፍል 1 ቍጥር 6።

ስለዚህ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ በመውጣት ወይም በጸአት አንድ ሁናቴ ማሳየታቸውን ወይም መገኘታቸውን በባሕርየ መለኮት ያላቸውን አንድነት አስገንዝቦአል። እንዲሁም ከሆነ የጸአት /መውጣት/ አቋም በዚሁ ሁናቴ ረገድ የጨበጠው ቁም ነገር ላቅ ያለ መሆኑን በጭምትነት መመልከት ታላቅ ሙያ ነው። ይህም ሳይቀር በትምህርቱ አቀራረብ ደግሞ በየመልኩ ለይቶ ማየት የተገባ ይሆናል። ይህም በዚህ እንዳለ ይጠበቃል።

የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ከአብ አወጣጥ ልዩ ትርጕም አለው። ነገር ግን «ወልድና መንፈስ ቅዱስ በጸአት /በመውጣት/ ከተገናኙ ዘንድ በአወጣጥም ረገድ አንድ ናቸው? ወይም አወጣጣቸው አንድ ዓይነት ነው?» ብንል፣ አስቀድመን የአወጣጣቸውን ሁኔታ /ኩነት/ በገለጽንባቸው ምሳሌዎች የተነገረውን ዘንግተናል ወይም ልብ ሳንለው አልፈናል እንደማለት ይሆናል።

መቼም ቢሆን፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት /የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ጸአት/ በአወጣጡ ሁኔታ /ኩነት/ አንድ ዓይነት እንዳልነበረ ብናስታውስና ብናሰላስል ልናገኘው እንችላለንና ነው።

1ኛ፥ በቀላሉ ከነገረ ነፍስ በወሰድነው ምሳሌ የወልድ ጸአት / አወጣጥ፥/ ቃል ከልብ እንደወጣ የመንፈስ ቅዱስም ጸአት /አወጣጥ/፥ እስትንፋስ ከልብ እንደሚወጣ ተደርጎ መገለጹን።

2ኛ፥ ከፀሐይ ወይም ከመብራት በተወሰደው ምሳሌም፡- የወልድ ጸአት /አወጣጥ/ ፀዳል ወይም ነጸብራቅ ከፀሐይ ክበብ ወይም ብርሃን ከመብራት እንደሚፈነጥቅ አወጣጥ፣ የመንፈስ ቅዱስም ጸአት /አወጣጥ/ ሙቀት ወይም ግለት ከፀሐይ እንደሚወጣ አወጣጥ ተደርጎ መገለጹን።

3ኛ፥ ከእሳት በተወሰደው ምሳሌም፥ የወልድ ተረክቦ /መገኘት/ ወይም ጸአት /አወጣጥ/፥ ነበልባል ከእሳት እንደሚገኝ፣ የመንፈስ ቅዱስ ተረክቦም /መገኘትም/ ጸአት /አወጣጥም/፥ ዋዕይ /ትኩሳት እንደሚገኝ ተደርጎ መገለጹን እናስታውሳለን።

4ኛ፥ ከውኃ በተጠቀሰው ምሳሌ የወልድ ተረክቦ /ጸአት/ ወይም አወጣጥ ርጥበት ከውኃ እንደሚገኝ፣ መንፈስ ቅዱስም ተረክቦ /መገኘት/ ወይም አወጣጥ፥ ሁከት /አለመርጋት/ ከውኃ እንደሚገኝ ተደርጎ መገለጡን አይተናል።

እነሆም በዚህ ሁሉ አንድ በአንድ ትምህርቱን ከተከታተልን ከምሳሌዎቹ የታየው የአወጣጥ /የተረክቦ/ ሁኔታ የተለያየ እንጂ፣ አንድ ዓይነት እንዳልሆነ ልንገነዘብ እንችላለን።

እንግዲህ ጸአት በሳቢ ዘር አቋም ሲነገር፣ የሚያሳየው ምሥጢር አንቀጹ በሚሰጠው የዘይቤው ገለጻም «ቃል ተነገረ፣ እስትንፋስ ተተነፈሰ» ተብሎ በተለያየ አቋም መነገሩ ዐረፍተ ነገሮቹም የየራስ መሆናቸው ሲታይ፣ የቃልና የእስትንፋስ አወጣጥ እየቅል መሆኑን እንደሚያስገነዝብ የታወቀ ነው። ዳግም በፀዳልና /በነጸብራቅ/ በሙቀት መካከል የአወጣጥ ልዩነት እንዳለ ይታያል።

ለምሳሌ፡- «ፀሐይ በኃይልዋ ታበራለች» ተብሎ ሲነገር፣ ስለ ብርሃን አወጣጥ የተነገረ መሆኑን፣ «ፀሐይ በኃይል ያቃጥላል» ተብሎ ሲነገር ግን፥ ስለ ሙቀት /ስለ ግለቱ/ ተረክቦ /መገኘት/ ወይም አወጣጥ የተነገረ መሆኑን፣ ዘይቤው እየለየ ያስረዳል። ራዕ. 1፥16። ራዕ. 16፥8።

እንዲሁም በነበልባልና በዋዕይ መካከል የአወጣጥ ልዩነት እንደሚታይ ግልጽ ነው። ይኸውም በተሟላ ዐረፍተ ነገር «እሳቱ ይንበለበላል»። ተብሎ በሚነገር ጊዜ፣ የነበልባልንና የዋዕይን /የትኩሳትን/ ልዩነት ያሳያልና ነው። ኢሳ. 10፥17።

በውኃ ርጥበት በሁከት መካከልም ልዩነት እንዳለ ይታያል።

ይኸውም፡- የርጥበቱ ጠባይዕ ከጥጥርነት ውጪ መሆኑን ሲያሳይ፤ ሁከት ያለመርጋት ጠባይዕን ያሳያል።

በሌላ አቀራረብ እንደገና አተኩረን ብንመለከት፤ ቃል ስንልና እስትንፋስ ስንል ከአንድ የባሕርይ ምንጭ ከመለኮተ አብ ይውጡ እንጂ ከአወጣጣቸው /ከተረክቦአቸው ብቻ ሳይሆን፤ ከኩነታት ስሞቻቸውም የተለያየ ኩነት /አቋም/ መታየቱ ግልጽ ነው። ይኸውም «ቃል ቃል ነው፤ እስትንፋስም እስትንፋስ ነው»።

ስለዚህ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጡበትን የፀአታቸውን /የመውጣታቸውን/ ሁናቴ ስንናገር፤ በአንድ በኩል የባሕርይ ተረክቦን /መገኘትን/ በሚመለከት ሁናቴ «ጸአት/መውጣት/» በሚል ቃል ስንጠቀም፤ በሌላ በኩል ደግሞ አወጣጥን በሚመለከት ረገድ ከምሳሌዎቹ እንኳ የተለያየ ይዞታ መኖሩን ቅድሙንም ተረድተን አድረናል ማለት ነው።

ታዲያ፥ እንዲህ ከሆነ፥ ለይተን ለመግለጽ የምንችለው እንደምን ባለው ሁኔታ ነው? የሚል ጥያቄ ይኖራል። በእውነቱ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ኩነታዊን አወጣጥ በሚመለከት ረገድ መሠረት ተከትለው ቀጥታ በሚነገሩ ቃላት እንድንጠቀም በግድ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ ስለዚህ ነው።

ምዕራፍ ሃያ አንድ ።

የሥርዓተ ተሰምዮ ትምህርታዊ አቋም።

ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሚወጡበትን አወጣጥ በሚመለከት ሁናቴ ለአወጣጣቸው በሚመጥን ረገድ፥ የአወጣጡን ኩነታዊ አቋም እንደሚገልጹ ሊያስተማምኑ የሚችሉ የተለያዩ ሁለት ቃላት አሉ።

እነዚህም፡- የነገረ መለኮትን ምሥጢር ተሸክመው በሐዲስ ኪዳን ለሚገለጽ እሙን አምንታ፥ ምላሌንና ትንቢትን አዝለው በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ቃላት ናቸው።

እነርሱም ቃላት «ሠርቅና ሠርፅ» ይባላሉ። የተጠቀሱት ቃላት በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሠረቱበትን አቋም በቅድሚያ መመልከት ይጠቅማል።

ይኸውም በየረድፉ ለመግለጽ ያመች ዘንድ በየተራ እናቀርባቸዋለን።

ሀ፥ ሠ ር ቅ፡-

«ሠርቅ» የፀሐይ መውጣት፥ የፀሐይ ፀዳል ወይም ነጸብራቅ ከፀሐይ መፍለቅን፥ በፀሐይ በጮራ በመብራትና በብርሃን ያለውን ፀአታዊ አገባብ /አወጣጥ/ ወይም ተረክቦ / እያመለከተ የሚነገር ቃል ነው።

የፀሐይን መውጣት ሲያመለክት፡- «ወይሠርቅ ለክሙ ለእለ ትፈርሁ ስምየ ፀሐየ ጽድቅ ወሕይወት ታሕተ ክነፊሁ፡- ለእናንተ ስሜን ለምትፈሩ የጽድቅ ፀሐይ ይወጣላችኋል፤ ሕይወትም ከክንፎቹ በታች ነው።» ይላል ሚልክ. 4፥2።

የፀዳል ወይም የነጸብራቅ መፍለቅን ሲያመለክት፦ «በጽሐ ብርሃንኪ ወስብሐተ እግዚአብሔር ሠረቀ ላዕሌኪ፦ ብርሃንሽ ይወጣ ጀመረ፣ የእግዚአብሔርም ክብር አንጸባርቆልሻል» ይላል ኢሳ. 60፥1።

እንዲሁም፦ «ወሠረቀ ከመ ያርእዮሙ ብርሃኖ ለእለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት»።

«በጨለማና በሞት ጥላ ለሚኖሩ ብርሃኑን ይገልጥላቸው ዘንድ ወጣላቸው።» ይላል። ኢሳ. 9፥2። ሉቃ. 1፥79።

ይህም የባሕርይ ጸአትን /አወጣጥን/ እያመለከተ በአወጣጡ ይዞታ «የክብሩ ብርሃን ወይም ነጸብራቅ» ተብሎ የተነገረለት የወልድን ተረክቦ /መገኘት/ የሚያሳይ ነው።

ይህም ማለት ጥቅሶቹ የሚያመለክቱት ወልድ ከመገኛው ከአብ እንዴት እንዳንጸባረቀና ሲያንጸባርቅም በህልውና ረገድ ብርሃን ዘእምብርሃን እንደሆነ ነው።

እነሆም «ሠርቅ፥ /እርሱም ነጸብራቅ ወይም ብልጭታ/» ምሳሌንና ትንቢትን አዝሎ እስከ ሐዲስ ኪዳን መገለጽ መቆየቱ በዚሁ ይታያል።

ለ፥ ሠ ር ፅ ፦

«ሠርፅ ተብሎ ስለ ተነገረውም ቃል መነሻ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንመለከታለን። «ሠርፅ ሲባል፣ የቅጠል፥ የልምላሜ፣ የአበባ፥ የቍጥቋጥ፥ ከግንድ ወይም ከሥር መውጣትን ከጫፍ ከቅርንጫፍ መቈጥቈጥን፥ ማፈጥፈጥን ወይም መለምለምን ዳግም የጉም፥ የፍላት መትነንን ሲያስገነዝብ የሚነገር ቃል ነው።

«ከግንድ፥ ከሥር ስለ መውጣት ስለ ማቈጥቈጥ፦»

«ወይሠርፅ ሥርዎሙ ለእለ ተርፉ በይሁዳ ወይፈሪ ዘርዖሙ፦ በይሁዳ ለሚቀሩ ሥራቸው ያቈጠቍጣል ዘራቸውም ያፈራል።» ተብሎ ተገግሮአል። ኢሳ. 37፥31።

«ከቅርንጫፍ ከዘንግ ወይም ከበትር ሠርፅ ሲገኝ፦» «ወናሁ ሠረፀት በትረ አሮን እንተ ሌዊ አውፅአት ቈጽለ ወጸገየት ጽጌ ወፈረየት ከርካዐ፦ እነሆም ለሌዊ ቤት የሆነች የአሮን በትር አቈጠቈጠች፥ ቅጠልንም አወጣች፣ አበባንም አበበች፤ ለውዝንም አፈራች።» ተብሎ ተነግሮአል። ዘኍል. 17፥4፤8።

የአበባም አወጣጥ /ማበብ/ ሠርፅ ተብሎአል።

«ወይሠርፅ ከመ ጽጌ ወይጸንዕ ሥረዊሁ፦ እንደ አበባም ይወጣል ሥሩም ይጸናል።» ተብሎ ተነግሮአል። ሆሴዕ 14፥6።

ሥጋም ሲፋፋና ከክሳቱ ሲለመልም ሠርፅ ይባላል፦

«ወሠረፀ ሥጋየ፦ ለመለመ /ፋፋ/» ይላል። መዝ. 27፥7።

እነሆም ሠርፅ በዚህ ሁሉ ሲነገር ምሥጢሩ የባሕርይ ጸአት ሆኖ ያለ መለየት በህልውና አንድነት መገኘት እያመለከተ የሚያሳይ የባሕርይ ተረክቦ /መገኘት/ ነው። ኢሳ. 4፥2። አሞጽ 9፥13።

በተለይ «ሠርፅ በላህብና /በሙቀት/ በመዓዛ ዕጣን በተኑም ተርጕሞ የባሕርይ ተረክቦንና የመዓዛው አንድነትን አዛምዶ የሚገኝበት ጊዜ አለ።

ይኸውም፡- «ወባሕቱ ሠርፀ ጊሜ ዘተዐርግ እምድር ትሠቅያ ለምድር፥ ነገር ግን ከምድር የምትወጣ ጉም ምድርን ታጠጣት ነበር» ሲል ይገኛል። ዘፍጥ. 2፥6። /አብነት/

እንዲሁም፡- «እንተ ተዐርግ እምገዳም ከመ ሠርፀ ጢስ ዕጥንታ፡- እንደ መዓዛማ ጢስ /ምስሶ/ ከምድረ በዳ የምትወጣ» ይላል። መኃ. መኃ. 3፥6።

እንዲያውም «ሠርፅ» የሚል ቃል ከፀአተ እስትንፋስ የተዛመደበት አኳኋን የላህብን /የተንን/ አወጣጥ፥ ወይም የዕጣን መዓዛማ ተንን በምሥጢር ተጠግቶ ከመታየቱ ይመስላል። በተጨማሪ ኢሳ. 30፥28፣33። ኢዮብ 4፥9። አነጻጽር።

እነሆም «ሠርቅና ሠርፅ» የተባሉ ቃላት በቅዱሳት መጻሕፍት ገለጻ ምን ዓይነት ዘይቤያዊ አቋም ይዘው እንደተገኙ ተመለከትን።

እነዚህን አሥራወ ቃላት ምንም እንኳ በጸአት ረገድ አንድ እንደ መሆናቸው የባሕርይ ጸአት /መውጣት/ ቢገለጽባቸውም፣ በአወጣጥ ረገድ ግን የየቅል ትርጕምና ፍቺ እንዳላቸው በተለያየ የዘይቤ ገለጻና አቀራረብ ማንጸባረቃቸው የሚታይ ነው።

የሀገራችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድም፡- ንጉሥ ዳዊት በመዝሙሩ፡- «ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ፡- ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክ» ሲል የተናገረውን በዜማ ድርሰቱ፡-»

«እንዘ ሀሎነ ውስተ ጽልመት ሠረቀ ለነ ብርሃን ወሠረፀ ለነ ጽድቅ፥ ጨለማ ውስጥ ሳለን ብርሃን ወጣልን /አንጸባረቀልን/ ጽድቅ ሠረፀልን» ሲል ወስዶታል። /ድጓዘ ዘመነ ልደት፡-

መቼም «ሠረቀ» የሚል ግሣዊ አንቀጽ ብርሃንን ሲያይ መነገሩ በተለያዩ ክፍሎች ያወቅነው የተለመደ ቢሆንም፣ ቅዱስ ያሬድ «ሠረፀ ጽድቅ» ሲል ከዚህ ጋር አመሣጥሮ ለመናገር የበቃበትን ምክንያታዊ ነክ እንረዳ ዘንድ ያለን ጕጕት የሚደበቅ አይደለም።

ስለዚህ ቅዱስ ያሬድ «መንፈሰ ጽድቅ ዘይወፅእ እም ኀበ አብ፡-

ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ» የሚለውንና፡- ወይሠርፅ ጽድቅ በመዋዕሊሁ፡- ጽድቅም /እውነትም/ በዘመኑ ይሠርፃል /ያብባል/» የሚለውን በማገናዘብ አመሥጥሮ መናገሩን ልንረዳለት እንችላለን። ዮሐ. 15፥26። መዝ. 71/72/፥6።

«ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክ» ሲል ዳዊት በተናገረው ንባብ ላይ ቃል በቃል ሲነገር ተያይዞ ከወረደልን ብሂላዊ ትርጓሜም፡-

«አንድም «ፈኑ ብርሃነከ፥» ወልድን፥ «ወጽድቀከ» መንፈሰ ቅዱስን... ላክልን።» እያሉ ምሥጢሩን በማገናዘብ ብሔራውያን መተርጕማን መግለጻቸው የሚታመን ነው። /መዝሙረ ዳዊት ንባብ ከነትርጓሜው ገጽ 230።

ዘአህትም አባ ቴዎፍሎስ ጳጳስ ዘሐረር በ1950 ዓ.ም. አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

እንዲሁም በመሆኑ «ሠረቀ» የሚል ግሣዊ ዘይቤ፣ ብርሃን ለሚሰኝ ለእግዚአብሔር ቃል ወልድ፥ «ሠረፀ» የሚል ግሣዊ ዘይቤ ደግሞ ከአብ ለሚወጣ

ለመንፈሰ ጽድቅ እየተገሠጡ የሚነገሩና የየራሳቸውን አወጣጥ አቋም የሚገልጹ መሆናቸውን በማያሻማ ትርኢት ለመመልከት አስችለውናል።

አሁን ደግሞ ከሚዛመዱአቸው ቃላት ጋር በየወገናቸው ሆነው በተለያየ ዘይቤ የየራሳቸውን አቋም እንደጠበቁ፣ ወልድና መንፈሰ ቅዱስ ከአብ የሚወጣበትን አወጣጥ ወይም ተረክቦ እንዴት እንደሆነ ሲገልጹ ልናይ ነው።

1ኛ፥ «ሠረቀ፥ ተወልደ፥ ሠርቀ ልደት» አንድ ወገን ሆነው ወልድ ቃለ እግዚአብሔር ከአብ የወጣበትን አወጣጥ ወይም ተረክቦ፦

2ኛ፥ «ሠረፀ፥ ወፅአ፥ ወጣ፥ ወይም ሠርፀ፥ ጸአት /አወጣጥ» ተብለው የሚነገሩ ቃላት አንድ ወገን ሆነው እስትንፋሰ እግዚአብሔር መንፈሰ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ ወይም ተረክቦ ሲገልጽ፦

እንግዲህ በሁለት ወገን ወይም አቅጣጫ ሆነው የሚሰጡትን ትምህርት በሚቀጥለው ምዕራፍ ጠንቅቆ መረዳት ነው።

ምዕራፍ ሃያ ሁለት።

ሠርቅና ልደት በተዛመዱበት ዘይቤያዊ ፍች።

«ሠረቀ፥ ተወልደ፥ ሠርቀ፥ ልደት፥ እንዲሁም ወልድ» ተብለው በሚነገሩ ቃላት ወልድ ቃለ እግዚአብሔር ከአብ የወጣበትን አወጣጥ /ተረክቦ/ እንዴት ነው? መጀመሪያ ነገር «ሠርቅ የሚል ቃል «ልደት» በሚል ቦታ ገብቶና «ልደት» የሚል ቃልም «ሠርቅ» ተብሎ በሚነገር ቦታ ገብቶ ሲነገርና ሲጻፍ፣ ጸአትንና /አወጣጥን/ ተረክቦን /መገኘትን/ ሲገልጽ ይገኛል። ዘፍጥ. 8፥5፤13።

ይህም ሲባል «በሰዋሰው ደንብ ጥሬው ሠርቅ ሲል፣ አንቀጹ ሠረቀ ይላል። ጥሬው ልደት ሲልም፥ አንቀጹ ተወልደ ወይም እንደ አማርኛው «ተወለደ» ይላልና ጥሬውና አንቀጹ የአንድ ግሥ ዘር መሆናቸውን በማስታወስ በትምህርት አገላለጽ ጊዜ፣ ከሁለቱ አንዱን ወስደን የትምህርቱን ዓላማ ብቻ ለማሳየት የምንምክር መሆኑን አንባቢ ይገነዘብልናል።

ማሳሰቢያ፦

ተረክቦ ማለት መገኘት ማለት ነው። ነገር ግን ህሉና እግዚአብሔር ተገኘ ሲባል፥ ያለ ጊዜና ዘለዓለማዊ መሆኑን ጠንቅቀን መረዳት አለብን። ስለዚህ «ተረክቦ» በሚለው ቃል የምንጠቀመው እግዚአብሔራዊ ዘለዓለማዊ መሆኑን እያሰብን ነው።

እንግዲህ ሠርቅና ልደት በተዛመዱበት ዘይቤያዊ ፍቺ መሠረት፥ አንድ ወገን መሆናቸውን ነው።

የቤተ ክርስቲያን አበውም እንደነገሩ አመጣጥና እንደ ሆናቱው ይዞታ መጠን እያዩ ለገለጻው በሚያመች ስልታዊ አቀራረብ እነዚህን ተዛማጆችን ቃላት እያፈራረቁ የወልድን ባሕርያዊ ተረክቦን ለማስረዳት ተጠቅመውባቸዋል።

ይኸውም «ልደት» የባሕርይ ተረክቦ ወይም የባሕርይ ጸአት /መውጣት/ ዘይቤያዊ ፍቺ እንዳለው ላልገባቸው፤ ወልድ ከአብ የተወለደበት የባሕርይ ልደት፥ ተከፍሎና ተሌልዮ /መከፈልና መለየት/ ቅድምናና ተድኅሮ ቅደም ተከተል /እንደሚታይበት እንደማናቸውም የፍጡራን ጠባይዐዊ ልማድ /ግዕዘ ጠባይዕ/ እያደረጉ ለሚደናበሩ ለነጳውሎስ ሳምሳጢና ለመሰሎቹ በሚያብራሩላቸው ጊዜ፤ ደጋጎች መምህራን፡- «ሠርቅ፥ /መውጣት/ ወይም «ሠረቀ፥ አንጸባረቀ/» በሚል ቃል ሲጠቀሙ ተገኝተዋል።

እነሆም ሐዋርያ ጳውሎስ፡- «የክብሩ ነጸብራቅ» ሲል በገለጸው መሠረት «ሠረቀ» /አንጸባረቀ ፈነጠቀ» በሚል ገለጻ ቢነገር፤ ወልድ ከአብ የተወለደበትን ልደት የባሕርይ መለየት በሌለበት በብርሃን አወጣጥ ምሳሌ ለመግለጽ አመችቶ መገኘቱ ነው። ዕብ. 1፥3።

የዚህንም አቀራረብና አገላለጽ ለመመልከት ያህል፡- ቀጥሎ ያለውን የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያንና የኪራኮስን ዘአንጾኪያ ቃል አቅርበናል።

ባስልዮስ፡-

«እስመ ወልዱ ውእቱ ዘተወልደ እምኔሁ። ኢኮነ ፍጡረ ወኢተፈጥረ በትእዛዝ፤ አላ ሠረቀ ክሡተ እመለኮተ አብ ዘእንበለ ጥንት ወዘእንበለ ፍልጠት እንዘ ይትዋሐድ ምስለ አብ።

ከእርሱ የተወለደ ልጁ ነውና፤ ፍጡር አይደለም። በትእዛዝም የተፈጠረ አይደለም። ነገር ግን ከአብ ጋር ተዋሕዶ ሳለ፤ ያለ መነሻና ያለ መለየት ከአብ መለኮት /ባሕርይ/ ግሁድ ሆኖ ያንጸባረቀ ነው።» ይላል።

ሃ. አበው ባስልዮስ ዘቂሣርያ ገጽ 113 ክፍል 4 ቍጥር 32።

እንደሚታየው ሁሉ ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ «ተወልደ» ብሎ ሲያበቃ እንደገና «ሠረቀ ክሡተ ግሁድ ሆኖ አንጸባረቀ» ሲል መናገሩ፤ አስቀድመን እንደ ገለጽነው ቅደም ተከተልና መለየት በማይታይበት በብርሃን ወይም በነጸብራቅ አወጣጥ አነጻጽሮ ለማብራራት የሚያስችለው ቋንቋ /አነጋገር/ «ሠረቀ /አንጸባረቀ»/ ብሎ ቢናገር በማረጋገጡ ነው።

ኪራኮስ ዘአንጾኪያ፡- «ወእምኔሁ ሠረቀ ወልድ ቀዳማዊ ዘለዓለም ወተወልደ፡- ከእርሱ /ከአብ/ ቀዳማዊ የሚሆን ወልድ ከዘለዓለም አንጸባርቆአል ተወልዶማል» ብሎ ተናገረ። ሃ. አበ ዘኪራኮስ ገጽ 391 ክፍል 1 ቍጥር 4።

በዚሁም «ሠረቀ /አንጸባረቀ/ በሚል ቃል የተጠቀሙ አበው ሊቃውንት ብዙ ናቸው።

በሰፊው ለመረዳት ቢያስፈልግ «የክብሩ ነጸብራቅ» ስለመሆኑ በተነተነበት ክፍል መመልከት ነው።

እንዲህ ስለተባለም «ሠርቅ /ነጸብራቅ/» ተብሎ ሲነገር የሚያሰማውን ኃይለ ቃል ያህል «ልደት» ተብሎ ሲነገር ወልድ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ ለመግለጽ እንደሚያሰማ ኃይለ ቃል አድርጎ መቍጠር የዝቅተኛ አስተሳሰብ ግምት መሆኑ ይታወቃል።

1ኛ፥ ልደት በልማደ ፍጡራን /በግዕዘ ቡዙኃን/ ካልሆነ በቀር የባሕርይ ልደት መኖሩን ለማይገባው ለጳውሎስ ሳምሳጢ፦

2ኛ፥ ልደት ማለት መፈጠር ማለት እንደሆነ ለሚመስለው ለአርዮስ፦ ወልድ የአብ ነጸብራቅ መሆኑን ለመግለጽ በሚያመችና ወዲያና ወዲህ ለመዋዠቅ በማያስችልና በማያሰናዝር ቋንቋ /አነጋገር/ ለማሳወቅ ብቻ «ሠርቅ ሠረቀ፥ አንጸባረቀ/» በሚል ኃይለ ቃል ለመጠቀም ታስቦ እንዲነገር አስፈለገ እንጂ፤ በመሠረቱ ግን «ልደት» የሚል ቃል «ሠርቅ» ተብሎ ሲነገር ከሚገልጸው የዘይቤ ስሜት የተለየ አይደለም።

«ሠረቀና ተወለደ» የሚለያዩበት ጊዜ ቢኖር፦ «ሠረቀ ክሡተ እመለኮተ አብ ከአብ መለኮት ግሁድ ሆኖ አንጸባቀ» ተብሎ ሲነገር፤ በሚገኝበት ጊዜና «እጐዛን እሙንቱ በፅምረተ አሐዱ መለኮት ዘውእቱ አሐዱ ብርሃን ዘይሠርቅ እምኔሁ ሥላሴ።

በአንዱ መለኮት መገናዘብ የተያዙ ናቸው። እነርሱም ሦስትነትን የሚያንጸባርቅ አንዱ ብርሃን ነው»። ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ ነው። ልዩነቱንም አንባቢ ሊያስተውለው ይችላል።

እንዲህ ባለው አኳኋን ካልተነገረ በቀር «ሠርቅ» ተብሎ የሚነገር ቃል «ልደት» ተብሎ ከሚነገር ቃል ጋር ተዘምዶ ያለው በመሆኑ «ልደት ወይም ተወልደ» ተብሎ ሲነገር «ሠርቅ ወይም ሠረቀ» ተብሎ በሚነገርበት ቦታ ሁሉ እየገባ ወልድ ከአብ ስለወጣበት አወጣጥ ብቁዕ የሆነ ገለጻ ሲሰጥ መገኘቱን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

1፥ ልደተ ሕሊና ሲገለጽበት።

እነሆም ንጉሥ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ፦ «ወለድኩከ እምከርሠ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ፦ ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ» ሲል አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። መዝ. 109፥3።

ካለፉት ትምህርቶች እንደተገለጸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፦ ይህን ንጉሥ ዳዊት የተናገረውን ሲያብራሩ፦

«ዝኒ ይተረጐም በሥምረተ መለኮት መዝገበ ሕሊናሁ ለአብ፤ ወልድኒ ሕሊናሁ ለአብ ውእቱ... ወበእንተዝ ይቤ ወለድኩከ እምከርሠ ልደት ውሳጥያዊት ወአኮ አፍአዊት፦ ይህ የአብ የአሳቡ መዝገብ በሚሆን በመለኮት ሥምረት ይተረጐማል። ወልድ የአብ ሕሊና ነውና።... ስለዚህም ሚዳዊት /አፍአዊት/ ልደት በማትሆን ውስጣዊት በሆነች ልደት ከሆድ ወለድሁህና አለው።» ማለታቸው ይታወሳል።

የሐዋርያት ተከታይ የሆነው የሀገረ ኤዶም ኤጲስ ቆጶስ ጌራኔዎስም፥ ዳዊት የተናገረውን ቃል በሚከተለው ትርጓሜ ገልጾታል። /መጽሐፈ ምስጢር።/

«ዝንቱ ውእቱ ሕሊናሁ ለአብ ፍጹም ቃለ እግዚአብሔር ዘተወልደ እምኔሁ እምቅድመ ዓለም ወእምቅድመ ኮከበ ጽባሕ፦ የአብ ሕሊናው የሚሆን ፍጹም ቃለ እግዚአብሔር ይህ ነው። እርሱም ከዓለም አስቀድሞና ከአጥቢያ ኮከብ በፊት ከእርሱ የተወለደ ነው።» ብሎአል። /ሃ አበ ሄራኔዎስ ዘሀገረ ኤዶም ኤጲስ ቆጶስ ገጽ 629።

በዚህም ብሂላዊ ገለጻ «ከሆድ ተወለደ» ማለት «ሕሊና ከልብ ተወለደ የማለትን ትርጉም የሚያሰማ መሆኑንና የተወለደው የአብ ሕሊናም ወልድ መሆኑን ከመሠረቱ አየን።

«ተወለደ ወይም ልደት» በሚል ዘይቤያዊ አነጋር የሕሊናን ልደት እንዳየን ሁሉ፥ እንደዚሁም የቃልንም ልደት ሲነገርበት እናገኛለን።

2፥ ልደተ ቃል ሲገለጽበት።

ይኸውም ወንጌላዊ ዮሐንስ፦ «ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ሀለወ። ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።» ሲል የጻፈውን፥ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ መሠረት አድርጎ በምዕማዱ ላይ፦

«ወፈድፋደሰ ውእቱ ነባቢ ሀላዊ ወእፎ ይትበሀል ኢተወልደ፦ ይልቁንስ በእግዚአብሔር ህልውና ነባቢ /ቃል/ ሲሆን አልተወለደም ለማለት እንዴት ይቻላል? ብሎ ቃልነቱና /ነባቢነቱ/ የህልውናው ተረክቦ ሆኖ «ተወለደ» እንደሚያሰኘው አብራርቶ አስረድቶአል»። ዮሐ. 1፥1። ሃ አበው አትናቴዎስ ገጽ 75 ክፍል 4 ቍጥር 10።

ይህም፦ «ወልድ ዋሕድ ዘሀሎ ውስተ ሕፅነ አቡሁ ውእቱ ነገረነ፦ በአባቱ እቅፍ ያለ አንዲያ ልጁ እርሱ «ነገረን» በሚል ንባብ ይበልጥ ጐልቶ ሊታይ ይችላል። ዮሐ. 1፥18።

ከሊቃውንት ወገን ቴዎዶጦስ ዘዕንቈራም፦ «ወአንተሂ ለቃልከ ዘይትወለድ እምልብከ»... ህልው ውስቴትከ ተወሊዶ እምልብከ። አንተ ብያ ከልብህ የሚወለድ ቃል... ከልብህ ተወልዶ በአንተ ውስጥ ይኖራል።» ሲል የምሳሌውን ምዕማድ አደላድሎ ካበቃ በኋላ፦

«ወህየንተ ልብ ዘዝየ ነአምሮ ለአብ ህየ፤ ወህየንተ ቃል ዘዝየ ነአምሮ ለቃለ እግዚአብሔር ከመ ቦቱ ህላዌ... እስመ ወልዱ ውእቱ ለአብ፦ ከዚህ በምናውቀው ልብ አብን እናውቀዋለን። ከዚህ በምናውቀው ቃልም የእግዚአብሔር ቃል ህላዌ /ባሕርይ/ ያለው መሆኑን እናውቀዋለን... የአብ ልጅ ነውና።» ሲል ተናግሮአል። ሃይማ አበ ቴዎዶጦስ ገጽ 174 ክፍል 1 ቍጥር 10።

እነሆም ቴዎዶጦስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ ተወለደ» በሚል ዘይቤ እንደዚህ አድርጎ ገልጾት እናገኛለን።

3፥ ልደት ቀጥታ «ወልድ» በሚል ስያሜ ሲነገር፦

እንዲሁም ደግሞ፦ «ተወለደ ወይም ልደት» የሚል ዘይቤያዊ አነጋገር ወልድ «በቃልነቱ» የወጣበትን አወጣጥ ብቻ የሚተረጉም ሳይሆን፤ በብርሃን ምሳሌ የተወሰደውን የወልድን አወጣጥ የሚገልጽ ሆኖ ይገኛል።

ይኸውም ቴዎዶጦስ ዘዕንቈራ ወልድ ከአብ ስለ ወጣበት አወጣጥ በሚናገርበት ጊዜ፤ የብርሃንን አወጣጥ ለመግለጽ፥ ዘወትር በሚገሠሥበት «ሠረቀ /አንጸባረቀ/» ተብሎ በሚነገር ቃል ሳይጠቀም፤ ቀጥታ «ተወለደ» በሚል ኃይለ ቃል ጠቃሚ ምሥጢር ያቀርብልናል። ቃሉም፦

«ወወልደ አብ ዋሕድ ይሰመይ ብርሃነ እስመ ብርሃን ዘተወልደ እምብርሃን ኢይትበሀል ተወልደ እምድኅረ ብርሃን፤ አላ በጊዜ ዘኮነ ቦቱ ውእቱ ብርሃን ይትረከብ ብርሃን ዘተወልደ እምኔሁ። ወብርሃንኒ ያጤይቀከ አምሳለሊሁ ለወልድ ዘውእቱ ህልው ምስለ አብ በኩሉ ጊዜ፥ እምቅድመ ኩሉ ዓለም»

የአብ አንዲያ ልጅም ብርሃን ተብሎ ይጠራል። ከብርሃን የተወለደ ብርሃን ከብርሃን በኋላ ተወለደ አይባልምና። ነገር ግን ብርሃን በተገኘበት የጊዜ ተረክቦ፥ የተወለደው

ብርሃንም ከአስገኚው ብርሃን ጋር አብሮ ይገኛል። ምንግዜም ቢሆን ከእርሱ ጋር ህልው ነው። ብርሃንም በዘለዓለማዊነት ከዓለም ፍጥረት አስቀድሞ ከአብ ጋር ህልው ሆኖ ለሚኖር ለወልድ ምሳሌው መሆኑን ያስረዳሃል።» የሚል ነው። /ሃ አበ. ቴዎዶሶስ ገጽ 172 ክፍል 1 ቍጥር 10-11።

ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ፦ «ወልድኒ ተወልደ እምአብ ከመ ብርሃን ዘእምብርሃን» ብሎአል። /ሃ አበ ገጽ 449 ቍጥር 3 ክፍል 1። እላይ እንዳየነው «ልደት ወይም ተወልደ» ተብሎ የሚነገር ቃል፦ «ሠርቅ ወይም «ሠረቀ ተብሎ ሲነገር፣ ወልድ ከአብ ስለ ወጣበት ባሕርያዊ አወጣጥ ሊገልጸው የሚችለውን ያህል እንደሚገልጽ ለመረዳት ያበቃል ይመስለኛል።

ከዚህ ግሥ ዘርና አንቀጽ በተያያዘ ሁኔታ የወጣው «ወልድ» የሚል ስያሜም ራሱን ችሎ ምሳሌን ሳይሻ፥ አብ ከሚያሰኝ ስያሜ ጋር ግዕዘ ጠባይዕንና ባሕርይን ሊያሳይ በሚያስችል አቋም ኅብረት ወይም አንድነት እንዳለው ያስረዳልና።

ወንጌላዊ ዮሐንስ፦ «ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ አሐዱ ዋሕድ ለአቡሁ፦ አንድ ልጅ በአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።» ሲል የተናገረውን በቅድሚያ እንመልከት።

ምዕራፍ ሃያ ሦስት።

አንዱ ልጅ በአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።

ይህ ጥቅስ ያዘለውን ኃይለ ቃል በጥንቃቄ መርምሮ ማወቅ የተገባ ነው። ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ይህን ቃል በሚተረጉምበት ጊዜ፣ «ዝንቱ ውእቱ ዘተወልደ እምአብ እስመ ወልድ ዋሕድ ኅቡረ ህላዌ በመለኮት ውእቱ፤ ወቦቱ ኩሉ ዘአቡሁ። እስመ ወልድ ዋሕድ ውእቱ ወኩሉ ቦቱ ኮነ። ወአልቦ ዘይትከፈል ምንትኒ ማዕከሌሁ ወማዕከለ አቡሁ። ወዝንቱ ስም ዘውእቱ ወልድ ያጤይቅ ኅብረተ ህላዌሆሙ። እስመ ወልዱ ውእቱ ወኢኮነ ፍጡረ ወኢተፈጥረ በትእዛዝ፦

ከአብ የተወለደ እርሱ ነው። እርሱ ወልድ ዋሕድ /ተቀዳሚ ተከታይ/ የሌለው በመለኮት የባሕርይ አንድነት ያለው ነውና። የአባቱ ሁሉ ገንዘቡ ነው። አንዲያ ልጅ /ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው ልጅ /ነውና። ሁሉም በእርሱ ሆኖአልና፣ በእርሱና በአባቱ መካከል የሚለይ ምንም ነገር የለም። ይህም ስም እርሱም ወልድ የመባል ስም የባሕርያቸውን አንድነት ያስረዳል። ከእርሱ የተወለደ ልጁ ነውና። ፍጡር አይደለም። በትእዛዝም የተፈጠረ አይደለም።» ሲል ተንትኖ ገልጾታል። ሃ አበ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ገጽ 113፥ ክፍል 4 ቍጥር 31፤32።

ሊቁ የቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ ኤጲፋንዮስም፦ መወለድ የባሕርይ አወጣጥን ይዞታ ሊገልጽ የሚችል ብቁዕ ማስረጃ መሆኑን ቀጥሎ ባለው አቀራረብ ገልጾአል።

«እርኑ ተፈጥረ እንዘለሊሁ ዘተወልደ። እመሰ ተፈጥረ እምኢተወልደ። ወእርኑ ይትፈጠር እንዘ ውእቱ ቀዳማዊ። ወንሕነኒ ለዘንወልዶ አኮ ዘንፈጥሮ፣ ወዘኔ ዘንፈጥሮ

አኮ ዘንወልዶ። ንሕነሂ ለዘንወልዶ አኮ ዘንፈጥሮ፣ ወዘኒ ዘንፈጥሮ አኮ ዘንወልዶ። ንሕነሂ ፍጡራን ወዘሂ ንወልዶሙ ዓዲ ፍጡራን እሙንቱሂ። ወእግዚአብሔርሰ ቃል ዘኢተፈጥረ፣ ወአኮ ልደቱ እምአብ ፍጡር። ወኢለሊሁ ፍጡር። ወእመሰ እምድኅረ ተፈጥሮቱ ተወልደ፣ እፎኑ ተፈጥረ ቅድመ ወካዕበ እምድኅረዝ ተወልደ።»

እርሱ ራሱ የተወለደ ሲሆን እንዴት ተፈጠረ ሊባል ይቻላል? ቢፈጠርስ ኖሮ ባልተወለደም ነበር። እርሱ ቀዳማዊ ሲሆን፣ እንዴት ይፈጠራል? እኛ እንኳ የምንወልደውን የምንፈጥረው አይደለንም። የምንሠራውንም /የምንፈጥረውንም/ የምንወልደው አይደለም። መቼም እኛ ፍጡራን ነን። የምንወልዳቸው ደግሞ ፍጡራን ናቸው። እግዚአብሔር ቃል ግን ያልተፈጠረ ነው። ልደቱም /መወለዱም/ ፍጡር ከሚሆን አባት አይደለም። ራሱም ፍጡር አይደለም። እንኪያስ ከመፈጠሩ በኋላ ከተወለደ፣ አስቀድሞ እንዴት ተፈጠረ ሊባል ይቻላል? ከዚያ በኋላስ እንደገና ተወለደ? ለማለት እንዴት ይቻላል?» ብሎአል።

እነሆም ሊቁ ኤጲፋንዮስ በዚሁ ሐተታ መወለድ የባሕርይ አወጣጥን ይዞታ ሊገልጽ መቻሉን ከማስረዳቱ በላይ፥ ወልድ ከአብ የተወለደበት ቀዳማዊነት ዘለዓለማዊነት ያለው የባሕርይ ልደት ሆኖ፥ «መፈጠር» ከሚል ቃል ጋር ፈጽሞ የማይገናኝና የራቀ የማይስማማ መሆኑን አስገንዝቦአል። ሃ አበ ኤጲፋ 186 ክፍል 5 ቍጥር 18፣ 19።

በዚህ ጉን ሐዋርያ ጳውሎስ «ነገረነ በወልዱ፡- በልጁ ነገረን» ያለውንና፡- «ለመኑ እመላእክቲሁ ይቤሎ ወልድየ አንተ። ከመላእክትስ አንተ ልጀ ነህ ያለው ማንን ነው? እንዲሁም፡-

«ወበእንተ ወልዱሰ ይቤ መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም፡- ስለ ልጁ ግን አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው ብሎአል» ሲል የተናገረውን ዮሐንስ አፈ ወርቅ በተረጕመበት ጊዜ፣ የሚከተለውን ምሥጢር አብራርቶአል። ዕብ. 1፥21 51 8።

«እስመ ብሂለ ወልድ ይኤምር ኀበ ግዕዘ ጠባይዕ ወከዊነ ዘመድ፡- «ወልድ /ልጅ/ የሚል ስያሜ ግዕዘ ጠባይዕንና የባሕርይ ተዘምዶን ያመለክታል። ሲል ተናግሮ በዚሁ ምዕግድ ላይ፡-

«ሶበሰ ኤኮነ ወልደ ዘበአማን፥ እምኢአዔረዮ ምስሌሁ በክልዔ ፍና በግዕዘ ጠባይ ወበባሕርይ አላ እምይቤ ፈጠሮ አሐዱ ለካልዑ።»

በእውነት ልጁስ ባይሆን ኖሮ፥ ከራሱ ጋር በሁለቱም መንገድ ይኸውም አንዱ ሁለተኛውን ፈጠረው ሲል በተናገረ ነበር።

ዳግም «ሶበሰ ኢኮነ ወልዱ ዘበአማን እምኢተናገረ በእንተ ባሕርያት ወክብሮሙ።

እውነተኛ /የባሕርይ/ ልጅስ ባይሆን ኖሮ፥ ስለ ባሕርይ ግብራትና ስለ ክብራቸው ባልተናገረም ነበር» እያለ የወልድ ልደት ባሕርያዊ መሆኑን ተንትኖ አስረድቶአል። /ድርሳን ዘዮሐንስ አፈ ወርቅ ገጽ 4 ክፍል 1 ቍጥር 47።

ቴዎዶጦስ ዘዕንቁራም፡- «ወለከሂ ወልድከ ኮነ ወልደ እም አሐዱ ህላዌ ዚአከ። ወዝንቱ ነገር ይከሥት ለከ ዘንተ አሐደ ህላዌ ዘአብ ወወልድ። ወንብል ከመ ውእቱ ወልደ አብ ዋሕድ ዘተወልደ እምኔሁ... ንነግረከ ወናሌብወከ ዘንተ ስመ ዘውእቱ ወልድ ከመ ውእቱ አሐዱ ህላዌ ምስለ አብ፡-

ያንተ ልጅ እንኳ ከአንዱ ከባሕርይህ ምንጭ ተገኝቶ ልጅ ሆኖሃል። ይህም ነገር የአባትና የልጅ አንድ ባሕርይ መሆን ይገልጥልሃል። በዚሁ መሠረትም ከአብ የተወለደ ወልደ አብ አንዲያ ልጅ እንደሆነ እንናገራለን።... ይህን ስም እርሱም «ወልድ» ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ መሆኑን እንነግርሃለን፤ እናስገነዝብህማለን።» ሲል አስረዳ። ሃ. አበ. ቴዎዶጦስ ገጽ 172 ክፍል 1 ቍጥር 7።

ዮሐንስ አፈ ወርቅ «እስመ አብ ለእመ ይሰመይ አበ በእንተ አብናሁ፥ ከማሁ ይደሉ ይሰመይ ዘወፅአ እምኔሁ በከዊነ ወልድ ወልደ፦

አብ ስለ አብነቱ አብ ተብሎ እንደሚጠራ ሁሉ፥ እንዲሁም ልጅ በመሆን ከእርሱ የወጣውም «ወልድ /ልጅ/» ተብሎ እንዲጠራ አገባብ ነው»። ሲል ተናገረ። /ድርሳን ዘዮ አፈ ወርቅ ገጽ 32 ቍጥር 19።

ሠለስቱ ምእትም፦ «ወኢይትከሀል የሀሉ አብ ዘመነ እንበለ ወልዱ አብ ያለወልድ /ያለ ልጁ/ ሊኖር የማይቻል ነው» ሲሉ የተናገሩን ከዚህ የተነሣ ነው። /ሃ. አበ ገጽ 52 ም. 19 ቍጥር 19።

ከዚህ በፊት ወደ ተመለከትነው መለስ ብለን ከመጽሐፈ ምሳሌ ባጎር ወደ ተናገረው ዓይነ ልቡናችንን ብናቀና፦

«መኑ ስሙ ወመኑ ስመ ወልዱ፤ ስሙ ማነው የልጁስ ስም ማን ነው?» የሚለውን ቃል እናያለን። ይህ ጥቅስ በታተተ ጊዜ፤ የልጁ ስም ቀጥታ ተጠርቶ ከመገኘቱ የተነሣ፤ ለልጅ አባት እንዳለው ለመጠቆም ለማመልከት እንዳስቻለ፤ እንዲሁም «ስሙ ማነው?» የተባለው የልጁ አባት እንደሆነ አቅርቦ ማስገንዘቡን ልናስታውስ እንችላለን። ምሳሌ 30፥4። ራዕ. 14፥1።

ይህም ጥቆማ ወይም ማመልከት የተደበቀውን ምሥጢር የሚያስጨብጥ ከትምህርተ መለኮት መመሪያዎች አንዱ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝበ አይሁድ፦ «ኢኪያየ ተአምሩ ወኢአቡየ ሶበሰ ኪያየ አእመርክሙ እምአእመርክምዎ ለአቡየሂ፦

እኔን አታውቁ አባቴንም አታውቁ፤ እኔንስ ብታውቁ ኖሮ አባቴንም ደግሞ ባወቃችሁ ነበር» ሲል በገለጸው የትምህርተ መለኮት ማስገንዘቢያ ተረጋግጦአል። ዮሐ. 8፥19።

እነሆም ባስልዮስ ዘቂሣርያ «ይህም ስም እርሱም «ወልድ» የመባል ስም፥ የአብና የወልድ የባሕርያቸውን አንድነት ያስረዳል። ከእርሱ የተወለደ ልጁ ነውና» ሲል ጐላ አድርጎ እንደተናገረ፥ የልጁ ስም ሲታወቅ፤ የአብ ስም ይታወቃል። የአብ ስምም ሲታወቅ፤ የልጁ ስም ይታወቃል። አብ ያለ ልጁ ልጁም ያለ አብ አይኖርምና ነው። ሃ አበ ባስል ዘቂሣርያ ገጽ 113 ክፍል 4 ቍጥር 32።

ይልቁንም በዮሐንስ ራዕይ ባጎር በተናረው አንጻር፦ «እለ ጽሑፍ ውስተ ፍጽሞሙ ስሙ ወስመ አቡሁ፦ በግምባራቸው ስሙና የአባቱ ስም የተጻፈባቸው» ተብሎ ይገኛል። ራዕይ 14፥1።

እዚህ ላይ «ልጅ ተብሎ ባይነገርም «አባቱ» ሲል፥ ስሙም ዝርዝሩም ልጁን እንደሚያመጣ የተሠወረ አይደለም።

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ገብርኤልም፦

«ወልድኒ ኢኮነ ካልዐ አምላክ፤ ወባሕቱ ቃለ እግዚአብሔር ዋሕድ ባሕቲቱ ወለሊሁ ይትአመር በአብ፥ በከመ ይትአመር አብ በወልድ፡- ወልድ ሌላ አምላክ አይደለም። ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንዱ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እነሆም አብ በወልድ እንደሚታወቅ ሁሉ እርሱ ራሱም በአብ ይታወቃል።» ሲል እያብራራ ተናግሮአል። ሃ አበው ገብርኤል ዘእስክንድርያ ገጽ 412 ክፍል 1 ቍጥር 5።

ይህን የተባለውን ሁሉ በማወቅና በማጠናቀቅ፡- «መኑ ስመ አቡሁ ወመኑ ስመ ወልዱ፡- የአባቱ ስም ማነው? የልጁስ ስም ማነው?» በማለት የሁለቱንም ስሞች አንድ ላይ በማቅረብ የተናገሩ ሊቃውንት አሉ። ቅዳሴ ዘዮ አፈ ወርቅ ገጽ 161 ቍጥር 82።

ምክንያቱም ጌታችን እንደተናገረው «ወልድን» ካወቀ አብን ማወቅ፥ አብንም ካወቀ ልጁን ማወቅ ባሕርያዊ መከሥት መሆኑን ከመረዳታቸው የተነሣ ነው። ምሳ. 30፥4። ራዕይ 14፥1። ዮሐ. 8፥19።

እነሆም የእግዚአብሔር ቃል ከአብ የወጣበት አወጣጥ ወይም ተረክቦ ሠርቅ፥ /ፀዳል/ «ሠረቀ/አንጸባረቀ/» በሚል ዘይቤያዊ ቃል ብቻ ሳይሆን፤ «ተወለደ፥ ልደት፥ ወልድ» በሚሉ ዘይቤያውያን ቃላት ሊገለጹ መቻሉን፤ ይልቁንም «ወልድ» የሚል ስም «አብ» ከሚል ስም ጋር ሳይለይ የባሕርይ አንድነትን እያስገነዘበ ቅደም ተከተል የሌለበት ዘለዓለምነትን ሊያሳየን መብቃቱን ተገንዘብን።

ይህም ሁሉ ኒቅያ ላይ በተሰበሰቡ አበው በ318 የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፡-

«ወልደ አብ ዋሕድ ዘህልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ። ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር የነበረ የአብ አንዲያ ልጅ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ» በሚል መግለጫ ተወስኖና ጸድቆ በሃይማኖት ሥርዓት /በጸሎተ ሃይማኖት/ በመገኘት የሚታወስ ነው። ሃይ አበ ዘሠለስቱ ምእት ገጽ 50 ም 18 ቍጥር 16-18።

አትናቴዎስ ሐዋርያዊም፡- ይህን ቃል ከሠለስቱ ምእት ጠቅሶ ምን ለመግለጽ አስበው እንደተናገሩ ሲያብራራ፡-

«ይቤሉ ዘንተ በእንተ ኅብረተ ህላዌ ወልድ ምስለ አቡሁ፤ ወልድ፡- ከአባቱ ጋር ስላለው ኅብረታዊ የባሕርይ አንድነት ይህን ተናገሩ» ብሎአል።

ይኸውና «ልደት ወይም ተወለደ፥ ወይም ወልድ» የሚሉ ቃላት ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ ወይም ተረክቦ ፍጹም ባሕርያዊ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በዚህም ብቻ ሳይሆን ወልድ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወጣበት አወጣጥ /ተረክቦ/ ልዩ አቋም ያለበት መሆኑን ገልጸው የሚያስረዱ የትምህርተ መለኮት አሥራው ቃላት ሆነው ተገኝተዋል። ይህም እየተከታተልነው ከመጣነው ማስረጃ ጋር ከብሔራውያን ሊቃውንት ከተዘጋጀው መጽሐፈ ምዕላድ ቀላልና ብሩህ በሆነ አገላለጽ የተጻፈውን አቅርበን እንመለከታለን።

ጥያቄ፡- «እመቦ ዘይብል ለምንት ይሰመይ አብ አበ ኀበ ወልድ ወኢይሰመይ አበ ኀበ መንፈስ ቅዱስ፡- ንብሎ እስመ አውፅኦ ለወልድ በከዊነ ቃል ወበእንተ» ይሰመይ አበ ኀበ ወልድ፤ ለመንፈስ ቅዱስሰ እስመ ኢያውፅኦ በከዊነ ቃል። በእንተዝ ኢይሰመይ አበ ኀበ መንፈስ ቅዱስ። እመቦ ዘይብል በእንተ ምንት ይሰመይ ወልድ ወልደ ኀብ አብ፤ ወኢይሰመይ ወልደ ኀበ መንፈስ ቅዱስ፤

ንብሎ እስመ ወልድ ዘወፅአ እምአብ በከዊነ ቃል። ወበ እንተዝ ይሰመይ ወልድ ወልደ ጎበ አብ። እመንፈስ ቅዱስሰ እስመ ኢወፅአ ዳዕሙ ቃሉ ውእቱ ዘወፅአ እምአብ። ወበእንተዝ ኢይሰመይ ወልደ ጎበ መንፈስ ቅዱስ»።

ሐተታ፡- «ተሰምዮተ አብሂ አኮ በእንተ አውፅአ ባሕቲቱ፤ አላ በእንተ አውፅኦት ቃለ። እመሰ በእንተ አውፅአ ባሕቲቱ ይሰመይ አበ እምተሰምየ አባሁ ለመንፈስ ቅዱስ እስመ አውፅአ። ተሰምዮተ ወልድኒ አኮ በእንተ ጸአት ባሕቲቱ፤ አላ በእንተ ጸአት በከዊነ ቃል ውእቱ። እመሰ በእንተ ጸአት ባሕቲቱ ይሰመይ ወልደ፤ መንፈስ ቅዱስኒ እምተሰምየ ወልደ እስመ ውእቱ ወፅአ እምአብ»።

ጥያቄ፡- ስለምን አብ በወልድ ዘንድ አብ ይባላል? ስለምን በመንፈስ ቅዱስ አብ አይባልም? የሚል ይኖራል።

መልሱ፡- ወልድን በከዊነ ቃል ስላወጣው፤ በወልድ ዘንድ አብ ተብሎ ይጠራል። መንፈስ ቅዱስን ግን በከዊነ ቃል ስላላወጣው በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ አብ አይባልም።

ጥያቄ፡- ስለምን ወልድ በአብ ዘንድ ልጅ ይባላል? በመንፈስ ቅዱስ ዘንድስ ስለምን ልጅ አይባልም?

መልስ፡- ወልድ እኮ ከአብ የወጣበት በከዊነ ቃል ነው። ስለዚህም በአብ ዘንድ ወልድ ተብሎ ይጠራል። ከመንፈስ ቅዱስ ግን አልወጣም። ነገር ግን ከአብ የወጣ ቃል ነውና ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ልጅ አይባልም።

ሐተታ፡- አብ ተብሎ መጠራት በማውጣት ምክንያት ብቻ የተገኘ ስም አይደለም። ቃልን ማውጣቱ ሲታይ ብቻ ነው። ማውጣትን ብቻ በመመልከት አብ ተብሎ የሚጠራ ቢሆንማ ከራሱ አውጥቶታልና የመንፈስ ቅዱስም አባት ሊባል በተቻለ ነበር። ነገር ግን እንዲህ አይደለም፡-

ዳግም ወልድ ተብሎ መጠራቱም መውጣቱን ብቻ ታይቶ የተሰጠው ስያሜ አይደለም። ነገር ግን መውጣቱ በከዊነ ቃል በመሆኑ ብቻ ነው። መውጣትን በማየት ብቻ ወልድ ተብሎ መጠራት የሚችል ቢሆን ኖሮማ፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ወጥቶአልና፤ ልጅ ወይም ወልድ ተብሎ በተጠራ ነበር። ይህ ግን አልሆነም።» ምዕላድ ዘዐቃቤ ሰዓት ከብቴ ገጽ 18፤19።

እንደሚታወቀው ሁሉ ከደጋጎች የቤተ ክርስቲያን መምህራን መካከል «ሠረቀ፤ ተወለደ፤ ሠርቅ፥ ልደት ወይም ወልድ በሚያሰኙ ቃላት መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ /ልዩ ተረክቦ/ ለመግለጽ የሞከሩ ሆነ የተናገሩም ወይም የጻፉ አይገኙም። እንዲያውም ለዚሁ ተቃራኒ በሆነ ገለጻ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ «ተወለደ፥ ልደተ ወልድ» በሚሉ ቃላት መናገር የማይገባ መሆኑን ከነምክንያቱ ጭምር በማብራራት አጥብቀው ሲከላከሉና ጎሳቡን ሲቃወሙ ተገኝተዋል።

ስለዚህም ማስረጃ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የተናገረውን መመልከት ይጠቅማል። «ወዓዲ መንፈስ ቅዱስሂ ተፈነወ ለነ እምጎበ እግዚአብሔር አብ ወኢይትከሀል ይበልዎ ግሙራ ለዘኢተወልደ ከመ ውእቱ ወልድ ዘተወልደ እምአብ እስመ ኢኮነ አሐዱ ግብሩ ለዘተወልደ ወለዘኢተወልደ። እስመ አሐዱ ሊሉይ እምካልዑ በግብረ ልደት። እስመ ወልድ ዋሕድ ቅዱስ ተወልደ እምእግዚአብሔር አብ።

ዳግመኛም መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብ ተላከልን። ከአብ ያልተወለደውን የተወለደ ወልድ ነው ሊሉት ፈጽሞ /አካቶ/ የማይቻል ነው። የተወለደና ያልተወለደ ግብሩ አንድ አይደለምና በመወለድ ግብር አንድ ከሌላው ልዩ ነውና። ተቀዳሚ ተከታይ

የሌለውና ልዩ የሆነ ወልድ ከአንድ ከእግዚአብሔር አብ ተወልዶአልና» ብሎአል። ሃ አበ ገጽ 75 ክፍል 1 ቊጥር 11፣12።

በዚህ ማስጠንቀቂያ መጠቀም የተገባ ነው።

እንግዲያውስ፦ «ቃለ እግዚአብሔር ወልድን ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው በሥርዓተ ወልድናው ተለይቶ የሚታወቅ ወልድ ዋሕድ የሚያሰኘው ምሥጢር ይኸው አይደለምን?» ዮሐ. 1፥14። 1ዮሐ. 4፥9።

እንግዲህ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደወጡ ሲነገር፣ የአወጣጣቸው ሁኔታ የተለያየ እንደመሆኑ መጠን፥ በማያሻማ የዘይቤ ትርኢት የየራሳቸውን የአወጣጥ ለይተው የሚገልጹና የሚወስኑ በብቁዕነት እንደ የአገባቡ የሚነገሩ ቃላት አሉዋቸውና እነርሱን መከተል ይገባል።

ምዕራፍ ሃያ አራት።

«ሠረፀ፥ ወጣ፥ ሠርፅ፥ መውጣት» በሚሉ ቃላት መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ /ተረክቦ/ እንዴት ነው?

ወልድ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ ወይም የወልድ ተረክቦ «ሠረቀ /አንጸባረቀ/ ሠርቅ/ነጸብራቅ/ ወይም ተወለደ፣ ልደት፥ ወልድ» በሚሉ የቃላት ዘይቤ ተተርጉሞ ወይም ተተክቶ እንደመገኘቱ መጠን፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ተረክቦ ደግሞ «ሠረፀ፥ ሠርፅ /ወጣ፥ አወጣጥ/» በሚሉ ዘይቤያውያን ቃላት ተተርጉሞ ወይም ተተክቶ ይገኛል።

ስለዚህ ወልድ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ /ተረክቦ/ «ሠረቀ፥ ተወለደ ወይም ሠርቅ፥ ልደት፥ እንዲሁም ወልድ» በሚሉ ቃላት እንደሚገለጽ ዕውቅ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ /ተረክቦም ደግሞ «ሠረፀ ወፅአ /ወጣ/ ሠርፅ /አወጣጥ/» በሚሉ ቃላት እንደሚገለጽ ዕውቅ ሆኖአል።

ይህም እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ የመጣ አዲስ አሳብ ሳይሆን፥ በቅዱሳት መጻሕፍት ተለይቶ መነገሩ የሚታመን ነው።

እንግዲህ አሁን ስለ መንፈስ ቅዱስ አወጣጥ በምንወስደው ትምህርት «ሠረፀ፥ ወፅአ /ወጣ/ ሠርፅ፥ ጸአት /አወጣጥ/» የሚል ዘይቤያዊ ቃል ምንን ሲገልጽ እንደተነገረ፣ ሥረ ነገሩን እያሰላሰልን ዓይነተኛ ምሥጢሩን ወደምንረዳበት ትምህርታዊ ግብ እናዝማም፦

እነሆም ጌታ በወንጌል ስለ መንፈስ ቅዱስ ጸአት የሚከተለውን ቃል በተናገረ ጊዜ፦

«መንፈስ ቅዱስ ዘይወፅእ እምኀበ አብ። ከአብ የሚወጣ መንፈስ ቅዱስ» ወዳለው ጥቅስ መጀመሪያ እናተኵራለን። ዮሐ. 15፥26።

በተጨማሪም ይህን መሠረት በማድረግና ምሥጢሩንም በመመልከት፥ በቤተ ክርስቲያን አበው መጀመሪያ በኒቅያ ዳግመኛም በቁስጥንጥንያ ጉባኤዎች ወደ ወሰኑት

ቀኖናዊ የሃይማኖት ሥርዓት /ጸሎተ ሃይማኖት/ ዓይነ ልቡናችንን ብናቀና ትምህርታዊ አሰካኩ እንደምን እንደተገናዘበ ለማየት በቀላሉ እንረዳለን።

ይኸውም፡- «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረፀ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት፡-

ጌታ ሕይወት ሰጭ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በነቢያት በተናገረ ከአብና ከወልድ ጋር እንሰግድለትና እናመሰግነው ዘንድ ባለን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።» የሚል ነው። ሃ አበ ሠለስቱ ገጽ 47 ክፍል 1 ቍጥር 11። ኢጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ ሃ. አበ ገጽ 193 ክፍል 11 ቍጥር 30።

እነሆም «መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሚወጣ» ሲል ጌታ በወንጌል የተናገረውን ጉባኤ ኒቅያና ጉባኤ ቁስጥንጥንያ «ከአብ የሠረፀ» ሲሉ በድንጋጌ መቀየሳቸውን ጠንቅቆ ማስተዋል የተገባ ነው።

ጉባኤ ኒቅያና ጉባኤ ቁስጥንጥንያ ወፅአ /ወጣ/ የሚለውን ግሣዊ አንቀጽ «ሠረፀ» በሚል ዘይቤ ተርጕመው ተከተው ሊናገሩ የበቁት ቀዋሚ ምክንያት አላቸው።

አምን፥ ምንም እንኳን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጡበትን ጸአት /መውጣት/ ይኸው መውጣት /ጸአት/ ራሱ በባሕርያዊ ተረክቦ አንድነታቸውን የሚያስገነዝብ ቢሆንም፣ በአወጣጥ ረገድ ግን፣ የተለያየ ኩነታዊ አቋም ያላቸው መሆኑን እንዳሳወቀ አይዘነጋም።

የኒቅያና የቁስጥንጥንያ ጉባኤያት አወጣጣቸውን እየተመለከቱና እየተከታተሉ ለየቅል ትርጕም የሚሰጡ ዘይቤያውያን ቃላት ሊተኩ ግድ መሆኑን በሚገባ ስላመኑበትና መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ «ወጣ» የሚለውን ቃል «ሠረፀ» በሚል ቃል ለይተው ለማሳየት ስለፈለጉ እንደሆነ፣ በትክክል ሊገባን ይችላል።

ወዲሁም «ሠረፀ» የሚል ቃል አብዛኛውን ጊዜ ከኃዳሪና ከማኅደር የሚታየውን የአወጣጥ ዓይነት ይኸው ማለት ቡቃያነትን ሲያሳይ ከሚነገርበት የኃዳሪና የማኅደር ይዞታ በቀር የባሕርይን አወጣጥ፥ የባሕርይን ተረክቦ ጕላ አድርጎ ሲያሳይ የሚገኝ ዘይቤያዊ ትርጕም መሆኑ የማይረሳ የማይገደፍ ትምህርት ነው።

እንዲሁም ደግሞ በግዕዝ ዘይቤ «ሠረፀ» የሚል ቃል አወጣጥን ይኸውም ማለት ከአንድ ነገር መውጣትን እንጂ፣ ወደ አንድ ነገር መግባትን፥ ወይም መውሰድን ሆነ መቀበልን አይገልጽም። መጽ. ሰዋስው ወግሥ ኪዳነ ወል. ክፍሌ ገጽ 679።

በትምህርተ መለኮትም ረገድ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ /ተረክቦን/ እያመለከተ ሲነገር፣ ይህ የተናገርነውን የግዕዙን መሠረታዊ ገለጻ ተከትሎ ከመሠመሩ ዝንፍ ሳይል ይነገራል ይብራራል።

በአማርኛ ግን በተለይ በአሁን ጊዜ በሚነገር አማርኛ ለግዕዙ መሠረታዊ ዘይቤና ለትምህርተ መለኮት ቀዋሚ አሳብ ተቃራኒ ሆኖ ሲነገር ይሰማል።

ለምሳሌ በአማርኛ «የተነገረው ቃል በልቤ ሠርፆአል» ተብሎ ቢነገር» ቃሉ ወደ ልቤ ገባ ጠልቆ ተሰማኝ ተቀበልሁት ተገነዘብሁት» እንደማለት ባለው ዘይቤ ይነገራል። ይህም፡- ግዕዙ ለሚገልጸው ዘይቤና ለትምህርተ መለኮት ቀዋሚ አሳብ ተቃራኒ ሆኖ መነገሩ በጥንቃቄ ሊያስተውሉት ይገባል።

በትምህርተ መለኮት «ሠረፀ የሚል ቃል መውጣትን እንጂ የአሁኑ አማርኛ እንደሚያሰማው ወደ ሌላ መግባትን ወይም ከሌላ መውሰድን፥ ከሌላ መቀበልን የሚተረጉምና በእነዚህ ቃላት የሚተካ ወይም የሚወከል አይደለም።

ያለ ተቃርኖ የሚገኙና ጐን ለጐን የሚሄዱ ቃላት የየራሳቸው ግብር በሚያስታውቅበት ዘይቤ ይነገራሉ።

ለምሳሌ፦ «ስማ» ተብሎ የሚነገር ቃል «አየን» ተብሎ ከሚነገር ቃል የተለየ ፍቺና አቋም አለው። ይኸውም እነዚህ ቃላት የየራሳቸውን ግብር የሚያስታውቁበት ዘይቤ ስላላቸው ነው። በዘይቤያቸውም ተለይተው ስለሚታወቁ፤ አንዱ ሌላውን አይወርሰውም። በቦታውም ተተክቶ በሌላው ግብር ራሱን ሊገልጽ አይችልም። ነገር ግን «ሰማ» ሲባል የመስማትን ግብር ብቻ ይገልጻል። «አየ» ሲባልም የማየትን ግብር ብቻ ይገልጻል። በዚህ ሁኔታ በየአቋማቸው እንደሆኑ የየራሳቸውን ግብር ብቻ ይገልጻሉ እንጂ፣ አይወራረሱም። ይወራረሳሉ ቢባልም፤ በቅኔ ፈሊጥ ብቻ ነው። በቅኔ እንደምን ይወራረሳሉ? ቢሉ? «አዕይንት ይስምዓ ኩሎ ነገረ ወአዕዛን ይርአያ አህጉረ» ተብሎ በምፀት መንገድ ይነገራል። «ዓይኖች የሚነገረውን ንግግር ይስሙ ጆሮችም አገሮችን ሁሉ ይዩ» እንደማለት ነው።

እንደዚሁም ሁሉ «ሠረፀ» ተብሎ የሚነገር ቃል «ወጣ» የማለትን ፍቺ ይዞ፥ የጸአትን /የመውጣትን/ ግብር ብቻ በሚያሳውቅ ዘይቤ ጸንቶ በመቆም ይነገራል እንጂ፤ የጸአትን /የመውጣትን/ ግብር ለመግለጽ ተዘምዶ ከማይኖራቸው ነሥአ፥ /ወሰደ ተቀበለ፥ ተገነዘበ፥/ በሚል ፍቺ አይነገርም። «ሠረፀ» ተብሎ በሚነገር ቃል ቦታ ገብቶ፥ ወይም ተተክቶ ግብራቸውን ለመግለጽ አይቃጣም። አይወርሳቸውም። በእነርሱም ተወርሶ አይነገርም። «ሠረፀ» ሲባል «ወፅአ /ወጣ/» በሚል ፍቺ ብቻ ተተርጕሞ የጸአትን /የመውጣትን/ ግብር ይገልጻል። እሙን ዘይቤው ከመቀበል፥ ከመገንዘብ የተለየ ግብር ስላለው በእነርሱ ቦታ አይገባም። በራሱ አቋም እንደሆነ ብቻ የራሱን ግብር ይገልጻል።

ይህ የትምህርተ መለኮት አባባል ከሰው አሳብ የፈለቀ አይደለም። ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን አወጣጥ በወንጌሉ ሲገልጽ፦

1፥ «መንፈስ ቅዱስ ዘይወፅእ እምኀበ አብ፦

መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሚወጣ» አለ። ዮሐ. 15፥26።

2፥ በአንጻሩ መንፈስ ቅዱስ ከራሱ /ከቃልነቱ/ መገናዘብ ሲገልጽ ግን «መንፈስ ቅዱስ እምዚአየ ይነሥእ፦

መንፈስ ቅዱስ ከእኔ ይወስዳል ይገነዘባል» አለ። ዮሐ. 16፥13፤ 14።

በእነዚህ ጌታችን በተናገራቸው ጥቅሶች አሳቦቻችንን ሰብስበን በጥንቃቄ ብንመረምር፤ ግሣውያን አንቀጾቹ በተለያየ ዘይቤ ግብር ግብራቸውን እያሳወቁ የቆሙና ፍችዎቻቸውንም እየቅል የሚታዩ መሆናቸውን ከኃይለ ቃሉ ለመገንዘብ እንችላለን።

ይኸውም «መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይወጣል፤ ሲልና «መንፈስ ቅዱስ ከእኔ ይወስዳል» ሲል የሚታየው ኃይለ ቃል በማያሻማ ይዞታ ተጠብቆ መነገሩ ነው።

እንዲሁም በመሆኑ «ነሥአ፥ ወሰደ፥ ተቀበለ፥ ተገነዘበ» ተብሎ የሚነገርን ቃል «ወፅአ /ወጣ/ ሠረፀ» በሚል ቃል ለመተካት በዚሁ ፍቺ እንዲተረጐም አለቤቱና አለቦታው በግድ እንዲገባ ለማድረግ መጣጣር ተገቢ አይመስልም። ከዚሁ ይልቅ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማያሻማ ገለጻ የተናገረውን ቃል በገርነት መቀበል ኃይለ ቃሉ እየጠቆመና እያመለከተ የሚያሳየንን የኃይለ ምሥጢሩን መልክዓዊ አቋምና ስልት በየአቅጣጫው ማየት ይገባናል። የሚገባበት ቦታ እንኳ ቢታጣ፣ የት እናድርሰው በተባለ ነበር።

የኃይለ ምሥጢሩ መልክዓዊ አቋምና ስልት በየአቅጣጫው ማየት ስንልም፦

1፥ የተከሥቶ ህልውናን ትምህርት በሚመለከት አቋም «መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይወጣል» ማለቱን ሲሆን፣

2፥ ፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብን በሚመለከት አቋም «መንፈስ ቅዱስ ከእኔ ይወስዳል ይገነዘባል» ማለቱን ነው።

እንደዚህ ሆኖ የሚገባበት መደበኛ ቦታ እያለ፣ ምን ያስጨንቃል? ለልማዱ የት እናድርሰው የሚባል ቦታ ሲታጣ ነው። ያም ሆኖ ከማይመስለው ቦታ ማግባት ዝም ብሎ ነው።

ስለዚህ ከጌታ በተነገረው ኃይለ ቃል መሠረት በሁለቱ አሥራው ቃላት የተገለጸውን የትምህርተ መለኮት የተለያየ ይዞታና የአቀራረብ መልክ ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት ይገባል።

መቼም ቢሆን ለዚሁ ትምህርት መሠረቱ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ ተለይቶ የተነገረ የማይታበል አምላካዊ ቃል ነው እንጂ፣ ከቤተ ክርስቲያን መምህራን መፈላሰፍና ውሳኔ አይደለም፣ ያልንበት ምክንያት ከዚህ ግልጽ ሆኖ እንደሚታይ /እሙን ነው።/ አንጠራጠርም።

እነዚህ ይወፅአና /ይወጣል፥ ይነሥእ/ ይወስዳል ወይም ይገነዘባል/ የተባሉ አሥራው ቃላት በየዘይቤአቸው አቋም ተለይተው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አፍ ሲነገሩ፣ የኃይለ ምሥጢራቸውም ዓምዱ በማይታበል በቃሉ መሠረት ተዋድዶ ቆሞአል።

እያንዳንዳቸውም በምሥጢር የሚገቡበትን ቦታና የሚገለጹበትን የትምህርተ መለኮት ሙያን ፍጹም አድርገው ለማስገንዘብ የበቁ ናቸው።

መምህራኑ በድርሻቸው ያበረከቱት ነገር ያየን እንደሆነ ግን፣ መጀመሪያ ከጌታችን ቃል በቃል የተነገረውን የአሥራው ቃላቱን አቅዋም በገርነት መቀበላቸው፥ ዳግመኛም ኃይለ ምሥጢሩም ምንን እያመለከተ እንደተናገረ በቀና መንፈስ መረዳታቸው ሲሆን፣ በመሠረቱ ጸንተው ይህን በየመልኩ እንደሚገባ እያብራሩ ለመግለጽ መብቃታቸው ብቻ ነው።

ይህም ይታወቅ ዘንድ፦ የአንጾኪያ ሊቅ ሊቀ ጳጳሳት ባስልዮስ፦ «ወልድ ተወልደ እምኔሁ /አምአብ/ ወውእቱ ወልድ ዋሕድ ቃል ቀዳማዊ፣ ወመንፈስ ቅዱስሂ ወፅአ እምአብ ጥዩቀ በከመ ይደልዎ ለመንፈስ ቅዱስ ወልድ። ወልድ ከአብ ተወለደ እርሱም ቀዳማዊ ቃል የሚሆን አንዲያ ልጅ ነው። መንፈስ ቅዱስም በተረጋገጠ ሁኔታ ከአብ ወጣ፣ ለመንፈስ ቅዱስ እንደሚገባ።» ሲል ተናገረ፦ ሃይ አበ ባስልዮስ ዘአንጾኪያ ገጽ 419 ክፍል 1 ቍጥር 3።

ኪራኮስም «ወለሊሁ ዓዲ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ውእቱ፣ አኮ ውእቱ ተወላዲ እምአብ ዘከመ ወልድ፣ አላ ወፅአ እምአብ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢክልአት ዘከመ ይደሉ ለመንፈስ ቅዱስ፦ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው፤

እርሱም እንደ ወልድ የሚወለድ አይደለም። ነገር ግን ያለ መለየትና ያለ መገታት ለመንፈስ ቅዱስ እንደሚገባ ከአብ ወጥቶአል» ብሎአል። ሃይ አበ ኪራኮስ ዘአንጾኪያ ገጽ 398 ክፍል 1 ቍጥር 6።

ይህም መንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣቱ ወይም መሥረፁን ሲያይ፦ «በከመ ይደልዎ እንደሚገባው» በሚል ገለጻ ከየሊቃውንቱ የተነገረው መመሪያ «መንፈስ ቅዱስ ከአብ ወጣ» ማለት እንደሚገባ የተነገረ ቃል ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ወጣ ተብሎ የሚነገር ቢሆን ግን፣ የማይገባ መሆኑን እያነጻጸረ የሚያስታውቅ ማስጠንቀቂያ ነው።

መቼም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ቃልነትን ይገኝዘባል /ይነሥእ/ ቢባል እንጂ፣ ከወልድ ይወጣል /ይወፅእ÷/ አይባልምና ነው።

ይህም የቤተ ክርስቲያን መምህራን በጕላ በተረዳ አኳኋን ያስተማሩበት መሆኑን ከዚህ ቀጥሎ ይታይ ዘንድ እናቀርባለን።

1÷ ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ፦ «ከመዝ ነአምን ከመ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ መንፈሰ እግዚአብሔር መንፈስ ፍጹም ጸራቅሊጦስ እምአብ ዘይወፅእ። ወእምወልድ ዘይነሥእ።

እንደዚሁም ይህ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ፣ ጸራቅሊጦስ የሚባል ፍጹም መንፈስ እንደሆነና፣ ከአብ የሚወጣ ከወልድም የሚነሣ /የሚወስድ/ እንደሆነ እናምናለን» ሲል አስተማረ።

ሃይ አበው ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ ገጽ 193 ክፍል 11 ቍጥር 30።

ብሔራውያን ሊቃውንትም መዝገበ ሃይማኖት በተባለው በእምነት መግለጫቸው፦ «ወቅዱስ ወንጌል ይቤ በእንተ ጸራቅሊጦስ» እምአብ ዘይወፅእ» ያሌቡ በዝየ ሥርፀቶ እምባሕቲቱ አብ፣ ወኢይቤ ይወፅእ እምአብ ወእምኔየ፣ ከመ ኢንበል ከልዔቱ እሙንቱ አሥራፅያን አትለወ ቃለ ወይቤ ወእምኔየ ይነሥእ» በአማን መንፈስ ቅዱስ ይወፅእ እምአብ፣ ወይነሥእ ቃለ እምወልድ ወይነብብ በነቢያት ወሐዋርያት።

ቅዱስ ወንጌልም ስለ ጸራቅሊጦስ ሲናገር፣ ከአብ ይወጣል ይላል። በዚህም ከአብ ብቻ መሥረፁን ያስገነዝባል። ከአብና ከእኔ ይወጣል አላለም። ይኸውም ሁለት አሥራፅያን አሉት እንዳንል ነው። ቃልንም በማስከተል ከእኔ ይወስዳል አለ። በእውነት መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይወጣል። ከወልድም ቃልነት ይወስዳል በነቢያትና በሐዋርያትም ይናገራል» ሲሉ በማያሻማ ገለጻ አስረዱ። /መዝገበ ሃይማኖት ገጽ 57 ቍጥር 9።/

እነሆም መንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣቱን ወይም መሥረፁን ሲመለከት «ለመንፈስ ቅዱስ እንደሚገባ» እየተባለ የተጠቆመው ከዚህ በጕልህ ተገልጾ መብራራቱን አየን።

ምናልባትም እኛ ጌታችን፦ «እምዚአየ ይነሥእ፦ ከእኔ ይወስዳል ወይም ይገኝዘባል» ብሎ ሲናገር፣ ነሚእ /መውሰድ ወይም መገንዘብ /ሳይኖር ይነሥእ /ይወስዳል/ ብሎ የተናገረ መስሎን÷ የአንቀጹ ዘይቤ የመውሰድ÷ ወይም የመገንዘብ÷ ግብር እንደሌለው በመገመት ይነሥእን÷ /ይወስዳልን/ ይወጣል ወይም ይሠርፃል በሚል በተውሶ ፍቺ ተርጕመን ለመናገር እንቃጣ ዘንድ እንሞክር ይሆናል።

ዳሩ ግን ይህ ከመሆኑ አስቀድሞ፥ ጌታ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ከእኔ ይወሰዳል /ይነሥእ/ በሚልበት ጊዜ፣ ነሢእ /መውሰድ/ ቢኖር እንጂ፣ ነሢእ /መውሰድ መገንዘብ/ ባይኖር ይነሥእ /ይወሰዳል/ ብሎ እንዳልተናገረ ከቃሉ መረዳት አስፈላጊ ነው።

ይህንም ጌታ በወንጌል ስለ መንፈስ ቅዱስ አውሥቶ ሲናገር፥ «እምዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ፡- ከእኔ ይወሰዳል ይነግርችሁማል» ብሎ ወደ ተናገረው ጥቅስ ብናተኵርና በየረድፉ አቅርበን ብንመረምር የምናገኘው ነው። ዮሐ. 17፥14፣ 15።

ሀ፥ «ይነግራችሁማል» የሚለውን በቅድሚያ እንውሰድ፡-

እነሆም ይህን ቃል የሚናገር ወይም ለዚሁ ቃል ተናጋሪው ማነው? ብለን ብንጠይቅ፣ «ይነግራችኋል» የተባለው ተናጋሪው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በግልጽ እንረዳለን።

ለ፥ ይህ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው ቃል ከማን የወሰደው ነው ብለን ብንጠይቅ፡- ጌታ «ከእኔ ይወሰዳል፣ ይነግራችሁማል» ብሎአልና፣ ከወልድ የተወሰደ ቃል ሆኖ እናገኘዋለን።

ይህም መንፈስ ቅዱስ የወልድን ቃልነት መውሰዱን፥ መገንዘቡን እሙን እንደሆነ የሚያስረዳ ገለጻ ነው። እዚህ ላይ፡-

ታዲያ፡- ወልድ መንፈስ ቅዱስን የባሕርይ ሕይወቱን /አስትንፋሱን/ አድርጎ ከመገኘት ወዲያ፥ መንፈስ ቅዱስም ደግሞ፣ ወልድን የባሕርይ ቃልነቱን አድርጎ ከመገኘት ሌላ፣ ዘለዓለመዊና ባሕርያዊ ነሢእ /መገንዘብ/ ከየት ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል?

ጉዳዩ እንደዚህ መሆኑ በግልጽ እየታየ፥ መንፈስ ቅዱስ የወልድን ቃልነት ገንዘብ ማድረጉ ወይም መውሰዱና መቀበሉ ነሢእ አይደለም ይባላልን?

ይበልጥ ለመረዳት፡-

«ነሢእ» የሚል ቃል በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ብቻ የተለየ አቋም እንዳለው መገንዘብ በቅድሚያ አስፈላጊ መሆኑን፣ ማስተዋል ይኖርብናል።

ይህን በአእምሮአችን ውስጥ ዘግበን «ነሢእ» ተብሎ ሲነገር «ጸአት /መውጣት/ ወይም መሥረፅ» በሚል በተውሶ ፍቺ አይነገርም እንጂ፣ ፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብን ሲመለከት፥ በሚሰጠው ክፍለ ትምህርት በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ብቻ የሚገኝ ሳይሆን፣ በጠቅላላው ሦስቱን አካላት የሚያገናዝብ መሆኑን በተጨማሪ መመልከት ነው።

ይህንም ከዚህ በፊት ፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብን በሚመለከት ክፍለ ትምህርት በሰፊው ታትቶ መቅረቡን ልብ ያደርጓል።

ሆኖም በዚህም ቦታ «ወፅአ /ወጣ/ና ነሥአ /ተገነዘበ/» ተብለው በሚነገሩ ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት አበጥረን ለማየት እንችል ዘንድ እንደገና ብናቀርበውና ብናነጻጽርበት የሚከፋ አይደለም።

ጌታችን በወንጌል «አነ በአብ ወአብ ብየ፡- እኔ በአብ ነኝ አብም በእኔ ነው» ሲል የተናገረውን መሠረት አድርጎ የእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት አባ ዮሐንስ፡-

«ንሕነሰት አመነ ከመ አሐዱ አሐዱ እምአካላተ ሥሉስ ቅዱስ ይነሥኡ እምተዋሕዶተ አሐዱ መለኮት ወአካላትኒ ይነሥኡ እምኒሁ እንበለ ማኅለቅት። እስመ አብ ህልው በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ፣ ወወልድ ህልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ ህልው በአብ ወወልድ።

እኛም እያንዳንዱ የሥሉስ ቅዱስ አካላት ከአንዱ መለኮት ተዋሕዶ እንደሚገናዘቡ እናምናለን። አካላቱ ሁሉ ያለ መጨረሻ ከእርሱ ይገናዘባሉ። ይኸውም አብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። ወልድም በአብና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ ህልው ነው።» ሲል ገልጾታል።

ይልቁንም «ወአካላትኒ ይነሥኡ እምኔሁ ዘእንበለ ማኅለቅት፡- አካላቱም ሁሉ ያለ መጨረሻ ከእርሱ /ከአንዱ መለኮት ተዋሕዶ/ ይገናዘባሉ።» ያለውን ሲያብራራ፣ «እስመ አብ ህልው በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስኒ ህልው በአብ ወበወልድ፡-

አብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። ወልድም በአብና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው። መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ ህልው ነውና» በመለኮቱ፥ «ነሚኡ /መገናዘቡ/» ራሱ ፅምረተ ትሥልስት ወይም የአካላውያን ኩነታት በህልውና መገናዘባቸው መሆኑን ገልጾ አስረድቶአል። ሃ አበ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክ ገጽ 320 ክፍል 1 ቍጥር 11። በዚህ መንገድ እየለዩ የተናገሩ ሊቃውንት ብዙ ናቸው።

የህልውና መገናዘብ ሲባል ውስጣዊ ይዞታውን ለመረዳት የሚሻ ይኖራል። ይህንም እንደሚከተለው አቅርበን እናሳያለን።

እነሆም ሊቁ አቡልዲስ፡-

«ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ። መንፈስ ቅዱስኒ እስትንፋሶሙ ለአብ ወወልድ ወበእንተዝ አእመርነ ከመ አሐዱ ውእቱ መለኮተ ሥላሴ፡- ወልድ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው። መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው። ስለዚህም የሥላሴ መለኮት አንድ እንደሆነ ዐወቅን።» ሲል በብሩህ ገለጻ ተናግሮአል። ሃይ አበ አቡሊዲስ ገጽ 139 ክፍል 2 ቍጥር 8።

ይኸውና በህልውና መገናዘብ ሁናቴ ወልድ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው መሆኑ በነሚእ ወይም በመገንዘብ መንገድ አይደለምን? መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው መሆኑ በነሚእ ወይም በመገንዘብ ረገድ አይደለምን? አብም ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልቡናቸው ዕውቀታቸው መሆኑን በሚያስገነዝብ ማስረጃ አስቀድመን በሰፊው ተመልክተናል። እነሆም ልቡናቸው ዕውቀታቸው መሆኑ በነሚእ በመገንዘብ ረገድ አይደለምን? የህልውና መገናዘብ ውስጣዊ ይዞታ እንዲሁ ቅልብጭ ብሎ ይታያል።

በዚያ ሆነ በዚህ «ነሚእ /መገንዘብ/» ጐልቶ ይታያል። ተገናዛቢው ወይም ተገናዛቢ ኩነቱም አለ። በዚህ አለመቸገር ነው። ሳይቸገርም የተውሶ ወይም የብድር ቃል መፈለግ አያሻም። ነሚእ /መገንዘብ/፥ መውሰድ/ ሳይኖር ነሥአ፥ ተገነዘበ አልተባለምና።

እንኪያስ «ነሚእ ነሥአ» ሲባል የመቀበል የመገንዘብ የመውሰድ ትረጉምን ይዞ ይነገራል እንጂ፣ «ወጣና ወረፃ» የማለትን ፍቺና ትርጉም ነጥቆና ቀምቶ ግብሩን ሊገልጽ በማይችል ዘይቤ የሚነገር አይደለም።

ነሚእ /መውሰድ፥ መገንዘብ/ ፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብን በሚመለከት አቋም ራሱን ችሎ ይነገራል።

ጸአትም /መውጣት፥ መሥረፅ/ የተከሥቶ ህልውናን ትምህርት በሚመለከት አቋም ራሱን ችሎ ይነገራል። አንዱ ሌላውን አይውጠውም።

እንግዲህ ነሚእ /መውሰድ/ ወይም መገንዘብ/ ሳይኖር፣ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ይወስዳል ይገነዘባል አለ መባሉን ካየን፣ መንፈስ ቅዱስ በነሚኡ /መገንዘቡ/ መሠረት መንፈሰ አብ ሆኖ እንደተገኘ ሁሉ፥ መንፈሰ ወልድም ሆኖ ይገኛል።

ይህንም በቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚከተለው ተነግሮአል። እነሆም ሐዋርያ ጳውሎስ «መንፈሰ ወልዱ፡- የልጁ መንፈስ» ብሎ መናገሩ ይታወሳል። ገላ. 4፥5።

ሐዋርያው ጴጥሮስ፡- «ዘነገረ በእንቲአሁ ላዕሌሆሙ መንፈሱ ለክርስቶስ፡- በእነርሱ ላይ ስለ እርሱ የተናገረ የክርስቶስ መንፈስ» ብሎ ይጽፋል። 1ጴጥ. 1፥11።

ይህም «እምዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ። ከእኔ ይወስዳል ይነግራችሁማል» ሲል ጌታ ባለቤቱ ከተናገረው ጋር አንድ ነው። ዮሐ. 16፥13፤14።

በሌላ አቀራረብ መንፈስ ቅዱስ የአብ መንፈስ እንደሆነ፣ መንፈሰ ወልድ መሆኑን የሚናገሩ ጥቅሶች ይገኛሉ። እነዚህን እያወጣህ ተመልከት፡- ማቴ. 10፥20። ኢሳ. 11፥4። 2ተሰ. 2፥8። ሮሜ 8፥9።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን አበውም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትንና የሚያሰሙትን ድምፅ ተከትለው ይህን እያተቱ በሰፊው ተናግረዋል።

ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፡-

«ወመንፈስ ቅዱስሂ የይነሥእ እምክልዔሆሙ በከመ ለሊሁ ይቤ እግዚእነ እምዚአየ ይነሥእ ወይነግረክሙ፡-

ከእኔ ይወስዳል ብሎ ራሱ ጌታችን እንደተናገረ መንፈስ ቅዱስም ከሁለቱ ይወስዳል ወይም ይገነዘባል። /ይነሥእ/» ብሎአል። ሃ አበ. ባስልዮስ ዘቂሣ. ገጽ 117 ክፍል 5 ቍጥር 8።

በዚህም ጊዜ ቅዱስ ባስልዮስ እዚህ ላይ ከሁለቱ ይወጣል ሳይል ከሁለቱ ይነሥእ /ይገነዘባል/ በሚል ቃል መጠቀሙን ልብ ያደርጓል።

ለመሆኑ ባስልዮስ «ወከመዝ ንሜልስ ባህለ ነአምን በመንፈስ ቅዱስ ወንለቡ ፀአቶ እምአብ። እንደዚሁም በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ማለትን እንሠልሳለን። እርሱ ከአብ መውጣቱንም ማስተዋል አለብን» ሲል መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መውጣቱን ለይቶ ያሳወቀ ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ከሁለቱ ከአብና ከወልድ ይወጣል ለማለት አለመቃጣቱን ገልጾ በማያመነታ ሁኔታ መስክሮአል። ሃ አበ ባስልዮስ 107 ክፍል 2 ቍጥር 8።

ይልቁንስ «ነሚእ /መውሰድ» የህልውና መገናዘብ መሆኑን እያብራራ፡- «ወውእቱ ኩለንታሁ ህልው በእግዚአብሔር አብ ወበእግዚአብሔር ወልድ መንፈሶሙ ውእቱ፡-

ራሱ /መንፈስ ቅዱስ/ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ ህልው ነው። እርሱ መንፈሳቸው ነውና» በማለት ከሁለቱ ይገነዘባል። /ይወስዳል/ ያለበትን ምሥጢር ጕልህ አድርጎ ከዚሁ ተርጕሞታል። ሃይ አበው ባስልዮስ ዘቂሣ. ገጽ 116 ክፍል 4 ቍጥር 54።

ሊቁ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ፦

«እስመ መንፈስ ቅዱስ ዚአሁ ውእቱ በህላዌ መለኮት፦ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት ህልውና ገንዘቡ ነውና» ሲል ጌታ «ዘቦቱ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ። ለአባቴ ያለው ገንዘቤ ነውና» ሲል የተናገረውን አስጠግቶ ተናግሮአል። ሃ አበ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ ገጽ 376 ክፍል 9 ቍጥር 8፣10። ገጽ 376 ክፍል 9 ቍጥር 18፣21።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ አርጋኖን በተባለው ድርሰታቸው፦ «እስመ አልቦ ካልዕ መንፈስ ለከ ወካልዕ ሎቱ እስመ መንፈሰ ዚአሁ መንፈሰ ዚአከ። በከመ አሰፈውኮሙ ለአርድዕት እንዘ ትብል እፈኑ ለከሙ መንፈስ ቅዱስ ዘእምአብ ይወፅእ ወእምኔየ ይነሥእ፦

ለእርሱ /ለአብ/ ካለው ለአንተ ሌላ መንፈስ የለህም። የእርሱ መንፈስ የአንተ መንፈስ ነው። ራስህ ለደቀ መዛሙርትህ ከአብ የሚወጣ ከእኔም የሚወለድ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ ብለህ እንደሰጠኻቸው ተስፋ ሲሉ ነሚእ /መውሰድ/ የህልውና መገናዘብ ምሥጢር መሆኑን ገልጸዋል። አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ አርጋኖን።

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ዘካርያስ ደግሞ፦ «እስመ ለተዋሕዶተ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት ምስለ አብ ወወልድ ለሌሁ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሠቶ ለነ በወንጌሉ ቅዱስ ጎበ ይብል፥ እፈኑ ለከሙ ጰራቅሊጦስሃ እምዚአየ የነሥእ ወይነግረከሙ ይሜህረነ በዝንቱ ሱታፌ ተዋሕዶተ መለኮት፦

መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በመለኮት ስለ መዋሐድ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌሉ ገልጾአልና። ከእኔ የሚወለድና የሚነግራችሁ ጰራቅሊጦስን እልክላችኋለሁ ብሎአልና፤ ይኸውም በዚሁ የተዋሕዶተ መለኮት አንድነት ያስተምረናል።» ሲል መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ያለው የመለኮት ተዋሕዶ፥ ጌታ ከእኔ ይወስዳል ብሎ በተናገረው መሠረት በነሚእ አቋም መገለጹን አስገንዝቦአል።

/ሃ አበ አባ. ዘካርያስ ሊቀ ጳጳስ ዘእስ. ገጽ 439 ክፍል 2 ቍጥር 26።

የቤተ ክርስቲያን ደጋጎች መምህራንም ይህን ሁሉ ለይተው እንደ ይዘታው መጠን ተመራምረው በመገንዘባቸው፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይወጣል ወይም ይሠርፃል ከማለታቸውም ጋር፥ መንፈስ ቅዱስ ይወስዳል፥ ይገነዘባል /ይነሥእ/ በማለት እምነታቸውን አጸኑ። ሁለቱ ይወጣልና ይገነዘባል የሚሉ ቃላት የየአቋማቸውን ግብር በሚገልጹበት ዘይቤያዊ ፍቺ መሠረት የሚገቡባቸው ቦታዎችም ልዩ ልዩ ናቸው።

1፥ አዎን፥ «ነሥአ /ወሰደ፤/ተገነዘበ/» የሚል ቃል የፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብን በሚመለከት ራሱን በቻለ ከፍለ ትምህርት ሊነገር መደበኛ ቦታ አለው።

2፥ «ወፅአ /ወጣ/ ወይም ሠረፀ» ተብሎ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ስለ መውጣቱ በሚነገር ጊዜም፤ የተከሥቶ ህልውናን ትምህርታዊ አቋም በሚመለከት ራሱን በቻለ ክፍለ ትምህርት ሊነገር መደበኛ ቦታ አለው።

እንግዲህ ነሚእን /መገናዘብን/ ሲያመለክት የሚነገር ትምህርት፥ ፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብ ሲያይ የሚወሰድ ነው እንጂ፣ የተከሥቶ ህልውናን ሲያይ የሚወሰድ መሆን እንደሌለበት አይተናል።

ነገር ግን እንደዚህ መሆኑ በግልጽ ታውቆ ሳለ፣ ፅምረተ ትሥልስትን የሚገናዘቡ ቃላት በሚገቡበት ሠንጠረጃዊ ዐውድ ላይ፥ ተከሥቶ ህልውናን የሚያሳዩ ቃላት በማናለብኝ ስሜት ገብተው እንዲነገሩበት ቢደረግ፣ የትምህርተ መለኮት መሠረታዊ አቋምና ሙያን ፈራሽ ያደርጉታል። ይህንም በሚከተለው አቅርበን ለመመዘን እንችላለን።

እነሆም «ይነሥእ» የሚል ቃል ይቀበላል፥ ወይም ይወስዳል፥ ወይም ይገነዘባል በሚል እሙን ፍቺውና ትርጕሙ ፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብን እያሰረዳ፥ አብ ልብነት ሆኖ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ህልው መሆኑን፥ ወልድም ቃልነት ሆኖ በአብና በመንፈስ ቅዱስ ህልው መሆኑን፥ መንፈስ ቅዱስም እስትንፋስነት ሆኖ በአብና በወልድ ህልው መሆኑን በሚገባ ሊያብራራልን ችሎአል።

እንግዲህ ይነሥእ /ይወስዳል/ የሚል ቃል ይወጣል ወይም ይሠርፃል በሚል ፍቺ ተተርጕሞ እየተነገረ በላይኛው ሠንጠራጃዊ ዐውድ ቢገባ የሚያስከትለውን መዘዝ ልናይ ነው።

«አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ያወጣል፥ ያሠርፃል። ወልድም አብንና መንፈስ ቅዱስን ያወጣል ያሠርፃል። መንፈስ ቅዱስም አብንና ወልድን ያወጣል ያሠርፃል» ሊባል ነው።

ይኸውና ፅምረተ ትሥልስትን ወይም የህልውና መገናዘብን የሚያስረዱ ቃላት በገቡበት ሠንጠረጃዊ ዐውድ፥ የተከሥቶ ህልውናን የሚያስረዱ ይወጣል ይሠርፃል የሚሉ ቃላት መግባቱን ገብተዋል። በገቡበት ሁኔታ ሲነገሩ ያሳዩት ግን፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጪ የሆነ ፈሊጥና የትምህርተ መለኮትን አቋም የሚያደባልቅ የሚያፈርስ ውጤት አይደለምን?

እንደዚህ ያለውን መዘዝ ሊያመጣና ሊያስከትል የቻለው ምን እንደሆነ እንድንጠይቅ እንገደዳለን።

እንደዚህ ያለውን መዘዝ ያስከተለው ፅምረተ ትሥልስትንና የህልውና መገናዘብ በሚያስረዳ ራሱን በቻለ ሠንጠረጃዊ ዐውድ ሊነገር የሚችል ነሚእ ወይም መገናዘብ ሲሆን ሳለ፣ የጸአትን /የመውጣትን የመሥረፅ ፍቺ ለነሚእ /ለመውሰድ/ ተሰጥቶ፥ መውጣት ወይም መሥረፅ ፅምረተ ትሥልስት ወይም የህልውና መገናዘብ ሲብራራበት በሚገኝ ሠንጠረጃዊ ዐውድ የግድ እንዲገባ ሲደረግ ነው።

የዚሁ ድርጊት መዘዝ በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም። መሥረፅ ወይም መውጣት የሚል ቃል ፅምረተ ትሥልስት ወይም የህልውና መገናዘብ ሲብራራበት በሚገኝ መደበኛ ሠንጠረጃዊ ዐውድ፥ የግድ የሚገባ ከሆነ፣ ወልድ ከአብ የወጣበት ባሕርያዊ ጸአትም /አወጣጥም / መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወጣበት ባሕርያዊ ጸአት /አወጣጥ/ የሚለየው «ተወለደ» በሚል ቃል ነውና፣ መወለድም በዚሁ ሠንጠረጃዊ ዐውድ የግድ መግባት አለበት እንደማለት ነው።

ይህ ሁሉ ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት አሳብ ውጪ በመሆን የራሱን ግብር ብቻ ለይቶ በሚገልጽና በሚያስታውቅ ዘይቤ የሚነገር ቃል አለቦታው ገብቶ ግብሩ

ያይደለውን ዘይቤያዊ ግብር እንዲገልጽና እንዲነገር በመዶሻ እንደመምታት ያህል የሚቈጠር ይሆናል።

ስለዚህ ነገር በአጼ ዘድንግል ዘመነ መንግሥት እምነታቸውን ለመመርመርና በኢትዮጵያዊነቱ አቋም ለማጽናት ከያገሩ ተሰብስበው የነበሩት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ውሣኔያቸውን ባሰፈሩበት መዝገበ ሃይማኖት በተባለው በእምነት መግለጫቸው መልስ ተሰጥቶበት እናገኛለን።

ይኸንም፦ «ኢትበሉኬ ከመ መናፍቃን እለ ያስሕቱ ወይብሉ መንፈስ ቅዱስ ሠረፀ እምአብ ወወልድ። ዘኢተረክበ ውስተ መጻሕፍት። ወኢነጎድጎሙ ያማስኑ ሃይማኖተ። አላ ንሌአሎሙ ወንብል፦ እመሰ ሠረፀ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ወወልድ ናሁኬ አጥረየ ክልዔተ አሥራፅያነ። ወልድኒ ይደልዎ ያጥሪ ክልዔተ ወላድያነ ዘውእቶሙ አብ ወመንፈስ ቅዱስ። ወይመርሀነ ዝ ቃል ንበል አብ ወወልድ አሥረፅዎ ለመንፈስ ቅዱስ። ወዓዲ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወለድዎ ለወልድ። ንሕነሰ ንቤ በከመ ኢይደልዎ ለመንፈስ ቅዱስ ይለዶ ለወልድ ከማሁ ኢይደልዎ ለወልድ ያሥርዖ ለመንፈስ ቅዱስ፦

ኢንቶስሕ ከመ ኢይኩን ሕውሰ፤ ወኢንፈልጦ ከመ ኢይኩን ብውደ... ወቅዱስ ወንጌል ይቤ በእንተ ጳራቅሊጦስ፦

«እምአብ ይወፅእ» ያሌቡ በዝየ ሥርፀቶ እምባሕቲቱ አብ። ወኢይቤ ይወፅእ እምአብ ወእምኔየ ከመ ኢንበል ክልዔቱ እሙንቱ አሥራፅያን።

ከመጻሕፍት ያልተገኘውን «መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሠረፀ» እያሉ እንደሚያስቱ መናፍቃን አትበሉ። ሃይማኖትን ያጠፉ ዘንድም አንታገሣቸውም። እንደዚህ እያልን እንጠይቃቸዋለን። «እንኪያስ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ከሠረፀ ሁለት አሥራፅያንን አግኝቶአል ማለት ነው። እርሱ ሁለት አሥራፅያንን ካገኘም፤ ወልድም ደግሞ ሁለት ወላድያን፥ /ወላጆች/ አብንና መንፈስ ቅዱስን አገኘ ማለት ነዋ! ይህ አባባል አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስን አሠረፁት፥ ዳግመኛም አብና መንፈስ ቅዱስ ወልድን ወለዱት እንል ዘንድ የሚመራን ይሆናል። እኛ ግን መንፈስ ቅዱስ ወልድን ይወልደው ዘንድ እንደማይገባው ሁሉ፥ እንደዚሁም ወልድ መንፈስ ቅዱስን ያሠርፀው ዘንድ አይገባም እንላለን። እንዳይቀላቀልብን አንደባልቀውም። እንዳይፈራቀቅብንም አንለየውም።...

ቅዱስ ወንጌልም ስለ ጳራቅሊጦስ «ከአብ ይወጣል» ይላል። በዚህም ከብቻው ከአብ መሥረፁን ያስገነዝባል። አሥራፅያን ሁለት ናቸው እንዳንልም፤ ከአብና ከእኔ ይወጣል አላለም።» ብለዋል።

እነሆም የራሱን ብቻ ለይቶ በሚገልጽና በሚያስታውቅ ዘይቤያዊ ቃል ግብሩ ያይደለውን እንዲገልጽ ሌላ በሚገባበት ሠንጠረጃዊ ዐውድ በግድ እንዲገባ ቢያደርጉት፤ በትምህርተ መለኮት መደበላለቅና መፈራቀቅ እንደሚያስከትል ተገልጾ መቅረቡን ተመለከትን። /መዝገበ ሃይ ገጽ 56፤ 57። የመርጌታ ዳርጌ መጽሐፍ የእጅ ጹሑፍ።

ይህም አባባል ከዱሮ ሊቃውንትም ኪራኮስ ዘአንጾኪያ ብሩህ አድርጎ ገልጾት ይታያል።

«ወለሊሁ ዓዲ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ውእቱ፤ አኮ ውእቱ ተወላዲ እምአብ ዘከመ ወልድ፤ አላ ወፅአ እምአብ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢከልአት በከመ ይደሉ

ለመንፈስ ቅዱስ፦ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው። እርሱም እንደ ወልድ ከአብ የሚወለድ አይደለም። ነገር ግን ያለመለየትና ያለ መገታት ለመንፈስ ቅዱስ በሚገባ ኩነት ከአብ ወጥቶአል።» ብሎአል። ሃ. አበ. ኪራኮስ ዘአንጾ ገጽ 398 ክፍል 1 ቍጥር 6፣7።

እንዲሁም ለዚሁ አጠቃላይ የሆነውን መግለጫ ብሔራውያን መተረጕማን ከጻፉት ምዕላድ ቃል በቃል አምጥተን አቅርበናልና በማስተዋል መመልከት ነው።

ሐተታ፦ «እመቦ ዘይብል፦ በእንተ ምንት ይሰመይ አብ አሥራዔ ኀበ መንፈስ ቅዱስ ወኢይሰመይ አሥራዔ ኀበ ወልድ፣

ፍካሬ፦ ንብሎ እስመ አውፅአ ለመንፈስ ቅዱስ በከዊነ እስትንፋስ፣ በእንተዝ ይሰመይ አሥራዔ ኀበ መንፈስ ቅዱስ። ለወልድሰ እስመ ኢያውፅአ በከዊነ እስትንፋስ፣ በእንተዝ ኢይሰመይ አሥራዔ ኀበ ወልድ።

ሐተታ፦ እመቦ ዘይብል በእንተ ምንት ይሰመይ መንፈስ ቅዱስ ሠርፀ ኀበ አብ ወኢይሰመይ ሠርፀ በኀበ ወልድ።

ፍካሬ፦ ንብሎ እስመ ወፅአ መንፈስ ቅዱስ እምአብ በከዊነ እስትንፋስ፣ በእንተዝ ይሰመይ ሠርፀ ኀበ አብ። እምወልድሰ እስመ ኢወፅአ ዳዕሙ ውእቱ መንፈሱ ለወልድ ዘወፅአ እምአብ። ወበእንተዝ ኢይሰመይ ሠርፀ ኀበ ወልድ። ወተሰምዮ አሥራዒ አኮ፣ በእንተ አውፅአ ባሕቲቱ አላ በእንተ አውፅአ እስትንፋስ።

እመሰ በእንተ አውፅአ ባሕቲቱ ይሰመይ አሥራዔ፤ እምተሰምየ አብ አሥራዔ ወልድ እስመ አውፅአ። ዝሰ አልቦ ውስተ መጻሕፍት።

ተሰምዮተ ሠርፅሂ አኮ በእንተ ጸአት ባሕቲቱ፣ አላ በእንተ ጸአት በከዊነ እስትንፋስ፥ እመሰ በእንተ ጸአት ባሕቲቱ ይሰመይ መንፈስ ቅዱስ ሠርፀ፥ እምተሰምየ ወልድ ሠርፀ አብ እስመ ወፅአ እምአብ። ዝሰ አልቦ ውስተ መጻሕፍት፦

ሐተታ፦ አብ ስለምን አሥራዔ መንፈስ ቅዱስ ተባለ? ስለምንስ አሥራዔ ወልድ አልተባለም ወይም አይባልም? ብሎ የሚጠይቅ ይኖራል።

ፍካሬ፦ መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋስነት ሁናቴ፥ አብ ያወጣው በመሆኑ አሥራዔ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል። ወልድን ግን በእስትንፋስነት ሁናቴ አላወጣውምና አሥራዔ ወልድ አይባልም ብለን እንመልሳለን።

ሐተታ፦ መንፈስ ቅዱስ የአብ ሠርፅ ተበሎ መጠራቱ፥ የወልድ ሠርፅ ተብሎ አለ መጠራቱ ስለምን ነው? የሚል ይኖራል።

ፍካሬ፦ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበት አወጣጥ በከዊነ እስትንፋስ ነውና፣ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የአብ ሠርፅ ይባላል። ከወልድ ግን አልወጣምና ስለዚህ የወልድ ሠርፅ አይባልም። ይህም ሳይቀር ከአብ የወጣ የወልድ መንፈስ መሆኑ ዕውቅ ነው። አሥራዔ ተብሎ መጠራትም ደግሞ በከዊነ እስትንፋስ በማውጣት የሚጠሩበት ነው እንጂ፣ በማውጣት ብቻ የሚጠሩበት አይደለም።

አሥራዔ መባልስ በመውጣት ብቻ ቢሆን ኖሮ ወልድን አብ አውጥቶታልና አሥራዔ ወልድ በተሰኘ ነበር። ዳሩ ግን እንዲህ ያለ አባባል በመጻሕፍት አይገኝም።

ሠርፅ ተብሎ መጠራትም ደግሞ በከዊነ እስትንፋስ በመውጣት እንጂ፣ በማውጣት ብቻ የሚጠሩበት አይደለም። ስለ መውጣት ብቻ መንፈስ ቅዱስ ሠርፀ አብ ቢባል ኖሮ፥ ወልድም ከአብ ወጥቶአልና ሠርፀ አብ ቢባል ኖሮ፥ ወልድም ከአብ ወጥቶአልና ሠርፀ አብ ሊባል በበቃው ነበር። ዳሩ ግን ይህ አባባል በመጻሕፍት የለም።» በሚል ገለጻ ተብራርቶአል። ምዕ. ዘዐ. ሰዓት ከ. ገጽ 20።

በዚህ አጭር ገለጻ ሁሉም ተብራርቶበታል፤ ይህን ካየን ዘንድ መዝገበ ሃይማኖት በተባለው በብሔራውያን ሊቃውንት መግለጫ የተሰጠውን ማጠቃለያ እንመልከት፦

«ወበዝ አእመርነ ወጠየቅነ ከመ ኢወለዶ መንፈስ ቅዱስ ለወልድ ወኢያሥረየ ወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አላ መንፈስ ቅዱስ ሠረፀ ወእምአብ ተወልደ ወልድ። በዚህም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ወልድን እንዳልወለደው ወልድም መንፈስ ቅዱስን እንዳላሠረፀው ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደሠረጸና፣ ወልድም ከአብ እንደ ተወለደ ዐውቀናል ተረድተናልም።» ተብሎ ተነግሮ አናገኛለን።

ወልድ ከአብ የወጣበትን ጸአት /አወጣጥ/ «ሠረቀ፥ ተወለደ፥ ሠርቅ፥ ልደት ወልድ» በሚሉ፥ ቃሉ ተብራርቶ መነገሩን መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣበትን ጸአትም /አወጣጥም/ «ወጣ፥ ሠርፀ አወጣጥ» በሚል ቃል ጐልቶ መገለጹን በሰፈው ስናትት እንደመቆየታችን መጠን፥ ውስጣዊ የትምህርተ መለኮት አስተሳሰቡን በተብራራ ሁኔታ የተመለከትን ይመስለኛል።

ለምሳሌ፦

1ኛ፥ መለኮት በአብ መዋሐዱ የሚታወቀው ወልድ ከአብ ሲወለድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ሲሠርፅ መሆኑን ተመልክተናል።

2ኛ፥ በቅዱስ ወንጌልም በጸአት ቃል /ቃል ከልብ በሚወጣበት/ ምሳሌ የተገለጸው የወልድ መወለድ ሲሆን፣ በዐአቱ እስትንፋስ /እስትንፋስ ከልብ በሚወጣበት/ ምሳሌ የተገለጸው የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረፅ መሆኑን ተገንዝበናል።

3ኛ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይወጣል ሲባል መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ይነሥእ /ይወስዳል/ ተብሎ በቅዱስ ወንጌል በመነገሩ፤ እነዚህ ዘይቤያውያን ቃላት የየራሳቸውን ግብር ስለገለጹ አንደኛው ሁለተኛውን ሊወርሰው አለመብቃቱን አስተውለናል።

4ኛ፥ ይወጣልና /ይሠርፃል/ ይወስዳል /ይነሥእ/ የሚሉ ቃላት የየአቋማቸውን ግብር በሚገልጹበት ዘይቤያዊ ፍቺ መሠረት የሚገቡባቸው የትምህርተ መለኮት ልዩ ልዩ ቦታዎች ልዩ ልዩ መሆናቸውን ዐውቀናል።

5ኛ፥ ይወፅእና ይነሥእ /ይወጣል፥ ይወስዳል/ የተባሉ አሥራው ቃላት በምሥጢር የሚገቡበት ሙያና የሚገልጹት ትምህርተ መለኮት ሙያ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጸው ከመነገራቸው የተነሣ እንጂ፣ ሊቃውንት የፈጠሩት ፈጠራ አለመሆኑን አይተናል።

ይህ ሁሉ ወልድ ከአብ የወጣበት አወጣጥ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወጣበት አወጣጥና ልዩ አድረጎት ሊያሳየን መብቃቱን ተረድተን፥ የዚህን ሐተታ እዚህ ላይ እንደመድማለን። ዮሐ. 16፥26።

እንግዲህ አሁን ተዋሕዶተ መለኮት በሁለቱም የትምህርት አቋሞች /በህልውና/ መገናዘብ ትምህርትና በተከሥቶ ህልውና ትምህርት መገኘቱን አየን፦ ለማጠቃለልም ያህል መሠረታዊ አቋሙን ባጭር ረገድ እናነጻጽር፦

በህልውና መገናዘብ ትምህርት ያለው የተዋሕዶተ መለኮት አቅዋም በከዊነ ልብ በከዊነ ቃል በከዊነ እስትንፋስ ለከዊነ ሕይወት መገናዘብ /ወይም የህልውና መገናዘብ አቋም/ ሆኖ ይታያል።

በተከሥቶ ህልውና ትምህርት ያለው የተዋሕዶተ መለኮት አቋም ደግሞ፦- ተግህዶተ ትሥልስት ወይም የሥሉስ ቅዱስ ግብረ ጻአት እየተገለጸበት ሳለ፣ ተከፍሎና ተመትሮ የሌለበት የባሕርይ ህልውና ይታያል።

1፥ ተዋሕዶተ መለኮት በህልውና መገናዘብ ትምህርት ያለው አቋም የልዑለ ባሕርይ ከዊነ ሕይወት መሠረትነትን የማሳወቅ ግብር ስለሆነ፣ በትሥልስተ አካላት ጠባይዐት ወይም ኩነታት፥ ይኸውም በአብ ልብነት በወልድ ቃልነት በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት በተተካከለ ድርሻ የመገናዘብ ህልውና ሆኖ ይታያል።

2፥ ተዋሕዶተ መለኮት በተከሥቶ ህልውና ትምህርት ያለው አቋም ደግሞ ጻአትን /መውጣት/ በሚመለከት ረገድ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ አስገኝ አብ ስለመሆኑ፥ መነሻነቱን የማሳወቅ ግብር እንደመሆኑ ሁሉ የወፃእያኑ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ህላዌ /ባሕርይ/ ከሌላ ወይም ከየግላቸው ሳይሆን ቅድምና ተድኅሮ /ቅደም ተከተል/ ተከፍሎ ተመትሮ በሌለበት በአብ የባሕርይ ህልውና ወይም ከአብ ህላዌ መለኮት ሆኖ ይታያል።

አሁንም የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ህልውና /ህላዌ መለኮት/ በአብ መገኘቱ፥ ሦስቱ በእኩልነት የሚኖሩበት የጋራ ባሕርያቸው ወይም መለኮታቸው ነውና፣ በጊዜያት ቅደም ተከተል ለማስገኘት እንዳልቻለ ሁሉ፥ የታላቅና የታናሽ መለኮት መኖርን አያሳይም።